ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይታተም የታፈነው እትም

ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ፍኖተ ነፃነት ህዳር 18 ቀን 2005

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 63 | ዋጋው፦ 6 ብር

## አምባገነኖችን እንዴት እንታገል?

“ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ከ250 በላይ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች በግልፅ ተለይተው ይታወቃሉ፡ ፡ እነዚህ ዘዴዎች ጠቅለል ባለ መልኩ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚመደቡ ሲሆን ፤እነርሱንም ሰላማዊ ተቃውሞና ማግባባት ፣ ትብብር መንፈግ እና ሰላማዊ ጣልቃ መግባት ናቸው፡፡ ”

2

## “በምርጫው እንሳተፋለን የሚል አቋም ላይ አልደረስንም”



9

አቶ ገብሩ ገ/ማርያም (የመድረክ አመራር)



## በሞት “ሌጋሲ” የተዋጡት ጠ/ሚኒስትር

10

### ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ መወዳደሪያ ምልክት ላለመውሰድ ወሰኑ

17

### መንግስት ያመቻቸው የሞት መንገድ

12

### የአንድነት ብሔራዊ ም/ቤት ለሁለት ቀናት ከፍተኛ ግምገማ አካሄደ

17

### ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አፈና በስተጀርባ!

16

### ከምርጫው በፊት የምርጫ መደላድሉ ይስተካከል

4

# አምባገነኖችን እንዴት እንታገል?

ከበትረ ያዕቆብ

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው ትልቅ የአመራር ክፍተትና አሁንም ድረስ ውስጥ ውስጡን የቀጠለው የስልጣን ሽኩቻ አምባገነኑን ስርአት ክፉኛ አዳክሞታል። በኢህአዴግ ቤት ውስጥ የተፈጠረው መጠላለፍ እና በጥርጣሬ አይን መተያየት ከውጫዊው ጫና ጋር ተዳምሮ ዛሬ የ21 ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረውን አንባገነናዊ ስርዓት ለማስወገድ ከምን ግዜውም በላይ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህዝቡ አገዛዙን ለማስወገድ ለትግል መነሳት እንዳለበት ደግመው ደጋግመው ጥሪ እያስተላለፉ ይገኛሉ። ምንም እንኳን ብዙዎቹ እንዲሁ በደፈናዉ "ለሰላማዊ ትግል ተነሱ" ከማለት በስተቀር ብዙም በታቀደ እና ዘርዝር ባለመልኩ እንዴት መታገል እንዳለበት ለህዝቡ ሲናገሩ እና አቅጣጫ ሲሰጡ ባይደመጥ።

ባለፈው አመት አጋማሽ "መንግስት በሐይማኖታችን ጣልቃ መግባት ያቁም!" በሚል በሙስሊሙ ህብረተሰብ የተጀመረው ሰላማዊ ትግል አሁንም እንደቀጠለ ነው። ትግሉ እስካሁን በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዙሪያ ብቻ የተወሰነ ቢሆንም ህዝባዊ መሰረቱ በፍጥነት እየሰፋ እና ሙስሊም ካልሆነው ህብረተሰብም የሞራል ድጋፍ በማግኘት የበለጠ እየተጠናከረ ይገኛል። እንዲያውም በቅርቡ መንግስት ህገ-መንግስታዊ ጥያቄያችንን ለመመለስ ዝግጁ ሆኖ ባለመገኘቱ ከዚህ በኋላ ትግላችንን የምናካሂደው የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ጭምር ይሆናል በማለት ማስጠንቀቂያ ያሉትን ቢጫ ካርድ ለመንግስት በአደባባይ እስከ ማሳየት ደርሰው ነበር።

እንግዲህ እነዚህን እና ሌላም መሰል በሀገራችን እየታዩ ያሉ ወቅታዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ስንመለከት በእርግጥም አሁን ላይ ስለ ሰላማዊ ትግል በዝርዝር መነጋገር እና መወያየቱ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን። ለመሆኑ ሰላማዊ ትግል ምን ማለት ነው? ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንፃርስ ምን ያህል አዋጪ ነው? ቀጣዩ ጽሁፍ በሰላማዊ ትግል ዙሪያ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይሞክራል።

## የሰላማዊ ትግል ምንነት

ሰላማዊ ትግል ትልልቅ የአለማችን የፖለቲካ ምሁራን ጭምር "ትክክለኛው አንባገነኖችን የማስወገጃ መሳሪያ ነው" ሲሉ የሚመሰክሩለት ትልቅ ህዝባዊ መሰረት ያለው የትግል ስልት ነው። ስልቱ ከትጥቅ ትግል በተለየ ሁኔታ ብዙ የህይወት መስዋትነት ሳያስከፍል ፣ ዜጎችን ለስደት ሳይዳርግ ፣ በንብረት ላይ ውድመት ሳያስከትል አንባገነኖችን ማስወገድ በማስቻሉ ተመራጭ ለመሆን በቅቷል።

ከሰላማዊ ትግል ጋር በተያያዘ በፃፋቸው መፅሐፎቹ ዓለም አቀፍ እውቅናን ማትረፍ የቻለው የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪው ጅን ሻርፕ "From Dictatorship to Democracy" በተሰኘው መፅሐፍ ላይ በግልፅ እንዳብራራው ፤ሰላማዊ ትግል በዋናነት ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስልቶችን አጣምሮ በመጠቀም ሰላማዊ በሆነ

> ማህበራዊ ትብብር መንፈግ በሚለው ስር የመንግስት ባለስልጣናትን እና ደጋፊዎቻቸውን ማግለል፣ ማውገዝ፣ ከማህበራዊ ግንኙነት መነጠል፣ ማኩረፍ እና ግላዊ ትብብርን ለባለስልጣናት እና ደጋፊዎቻቸው መንፈግና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ከመንፈግ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም መዋጮዎችን ማቆም ፣የስርአቱ ባለሚሉችና አጋፋሪዎች ንብረት በሆኑ የንግድ ድርጅቶችና ምርቶች ያለመገልገል፣ የገንዘብ ተቀማጭን ከመንግስትና ከመንግስት ደጋፊዎች ባንክ ማውጣት እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ

መንገድ የሚካሄድ ትግል ነው። ጅን ሻርፕ አፅኖት በመስጠት አንደገለፀው፤ በራሱ የሚተማመን ህዝብ፣ ብልህነት የተሞላበት ስትራቴጅ፣ ስነ-ስርዓታዊ እና ደፋር እርምጃ በጥምረት ካሉ ከላይ የተጠቀሱት ስልቶች ማንኛውንም ዓይነት አንባገነን ስርዓትን በቀላሉ ማፈራረስ የሚችሉ ናቸው።

ጅን ሻርፕን ጨምሮ ብዙ የፖለቲካ ምሑራን እንደሚስማሙበት ሰላማዊ ትግል ከሌሎች የትጥቅና የአመፃ የትግል ስልቶች በተሻለና አንድን ህዝብ ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ማሸጋገር የሚያስችሉ ናቸው የትግል ስልት ነው ። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም "ስልጣን ፣ ባህልና አገዛዝ..." በሚለው መፅሐፋቸው "በእኔ አስተሳሰብ የትጥቅ ትግል ለብዙ ዓመታት ስንተላለቅ የኖርንበትና የምናውቀው ነው ፤ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ግን በጭራሽ አዲስ ነው ፤ በትጥቅ ትግል አንዱን ጨቋኝ በሌላው እየለወጥን የአገዛዝን ባህል አጠነከርነው እንጂ ስልጣንን ለመግራት አልቻልንም..." በማለት የኢትዮጵያውያንን ያልተሳካ የትግል ታሪክ በመጥቀስ ሰላማዊ ትግል ለዲሞክራሲ ግንባታ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ያስረዳሉ።

በሰላማዊ ትግል ውስጥ ዜጎች የስልጣን ምንጭ የመሆናቸውን ታላቅ ሚስጥር ከመረዳት ባሻገር በተግባር ስለሚተገብሩት በቀጣይነት ስልጣን ላይ የሚወጣው አካል አንባገነን የመሆን እድል አይኖረውም ፤ ልሁን ቢል እንኳን ህዝቡ ፍፁም ያን የሚሸከም ትከሻ ስለማይኖረው ውጤቱ ፈጣን ውድቀት መሆኑ አያጠራጥርም።

እንደሚታወቀው ግብፃውያን የጦር መሳሪያ ታጥቀው ግዙፉን አንባገነናዊ የሙባረክ አገዛዝ ለመታገል አልሞከሩም። ይልቁንም በመላ ሀገሪቱ የስራ ማቆም አድማ በማድረግ ሰላማዊ የተቃውሞ ድምፃቸውን እያሰሙ እጅ ለእጅ ተያይዘው አደባባይ መውጣትን ነበር የመረጡት። ይህንም በማድረጋቸው ግዙፉን አገዛዝ በትንሽ መስዋዕትነት ማስወገድ የቻሉ ሲሆን ፤ በምትኩም በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመረጡትን አካል ስልጣን ላይ ማውጣት ችለዋል። እዚህ ላይ የግብፃውያን ትግል የቅርቡ ጊዜ ክስተት በመሆኑ ለሁሉም ሰው በቀላሉ ሊታወስ ይችላል በሚል እሳቤ እንደምሳሌ ይጠቀስ እንጂ በዓለማችን የበርካታ ሀገራትም ይህን መሰሉ ህዝባዊ ድል ብዙዎችን አስፈንጥሯል። ይህንን የትግል ስልት በመጠቀም በወቅቱ እንኳን ለማስወገድ ለመነቅነቅ ይከብዳሉ የተባሉ ሃያላን አንባገነኖችን በትንሽ መስዋትነት አንኮታኩተው በማስወገድ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ገንብተዋል። ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል፡- ህንዳውያን በጋንዲ መሪነት በወቅቱ የነበረውን የእንግሊዝ አንባገነናዊ ቅኝ አገዛዝ ማስወገድ የቻሉ ሲሆን ፤ ፊሊፒንሶችም በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1986 የፈርዲናንድ ማርኮን አገዛዝ አፈራርሰውበታል። በተመሳሳይም በሰርቢያ ፣ በጆርጅያ እና በዩክሬን ዜጎች ይህን የትግል ስልት በመጠቀም ስኬታማ የሚባል የስርዓት ለውጥ አካሂደዋል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስለ ሰላማዊ ትግል ሲሰበክ በርካታ አመታት ቢነጉዱም፣ በትግል ስልቱ ታግለው ለማታገል በተነሱት ዘንድ እናኳን የጠራ ግንዛቤ እንደሌለ ለማስተዋል አይከብድም። 21 ዓመታት ያስቆጠረው የኢህአዴግ ጨቋኝ አገዛዝ በሰላማዊ ትግል ሊወገድ እንደሚችል መገንዘብ የግድ ይላል። ስለ ሰላማዊ ትግል ምሉዕ ግንዛቤ መያዝ ብቻ ግን አንባገነኑን ስርአት ሊያስወግደው አይችልም፤ በመሆኑም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በቀላሉ ሊዋሀድ የሚችል የሰላማዊ ትግል ዘዴ በጥናት መምረጥ አስፈላጊ ነው።

## የሰላማዊ ትግል ዘዴዎች

ብዙ ጊዜ ስለ ሰላማዊ ትግል ሲነሳ ብዙ ሰዎች ወደ አዕምሯቸዉ ቶሎ የሚመጣላቸው ሰላማዊ ሰልፍ ፣ የስራ ማቆም አድማ እና የመሳሰሉ በጣም ጥቂት በተለምዶ የሚታወቁ የትግሉ ዘዴዎች ብቻ ናቸው። ሆኖም ግን ሰላማዊ ትግል በርካታ የትግል ዘዴዎችን በስሩ አቅፎ የያዘና በጥናት የሚመራ የትግል ስልት ነው። በአሁኑ ወቅት የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በዓለማችን ከ250 በላይ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች በግልፅ ተለይተው ታውቀዋል። እነዚህ ዘዴዎች ጠቅለል ባለ መልኩ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚመደቡ ሲሆን ፤እነርሱንም ሰላማዊ ተቃውሞና ማግባባት (Nonviolent protest and persuasion) ፣ ትብብር መንፈግ (Noncooperation) እና ሰላማዊ ጣልቃ መግባት (Nonviolent intervention) በመባል ይታወቃሉ።

ተቃውሞና ማግባባት፡- ይህ የሰላማዊ ትግል ዘዴ 53 ዓይነት ዝርዝር ዘዴዎችን በስሩ ይዟል። ለምሳሌ፡- የተቃውሞ ጉዞ እና ሰልፍ ማካሄድ፣ የስራ ማቆም አድማ ፣ የተቃውሞ ፊርማ ማሰባሰብ ፣ የመማፀኛ ፊርማ ማሰባሰብ ፣ የአንባገነኖችን ኢ-ፍትሀዊ እርምጃ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማውገዝ ፣ የተቃውሞ አርማዎች እና ምልክቶች የታተሙባቸውን ልብሶች መልበስ ፣ የተቃውሞ ተምሳሌታዊ ቁሳቁሶችን ማሳየት ፣ በየሀይማኖቱ ሕዝባዊ የፀሎተ ምህላ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ፣ ወካይ ተምሳሌታዊ የተቃውሞ ድምፆችን ማውጣትና መጠቀም ፣ በተለያየ መልኩ የባለስልጣናትን መጥፎ ተግባር ማጋለጥ ፣ ባለስልጣናትን መንቀፍ፣ ማሸማጠጥ፣ መዘለፍ፣ በአንባገነኖች የተገደሉ ሰዎችን በማሰብ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ፣ መንግስታዊ ስብሰባዎችን ረግጦ መውጣት እና የመሳሰሉት ናቸው። ቶማስ ዌበር "Nonviolence: An Introduction" በሚለው ዕሑፉ እንዳብራራው እነዚህ ዘዴዎች የአገዛዙን ወንጀልና በደል አጉልተው የሚያሳዩ እና ለውጥ መፈለጋችንን ለዓለም ህብረተሰብ መልዕክት የሚያስተላልፉ እንዲሁም አገዛዙ ከወዲሁ የተጠየቀውን እንዲፈፅም የሚያግባቡ ዘዴዎች ናቸው።

ጅን ሻርፕ ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደገለፀው ዘዴዎቹ ግልፅ የተቃውሞ መልዕክት ማስተላለፋ ከማስቻላቸው ባሻገር ምልዓተ ህዝቡን ያሳተፈ ከባድ ትብርር ነፈጋን ለማካሄድ እንዲሁም ቀጣይ ተቃውሞዎችን ለማድረግ በእጅጉ ይረዳሉ።

ትብብርን መንፈግ፡- ይህ ዘዴ ለአገዛዙ ፣ በአገዛዙ ስር ላሉ ማንኛውም ተቋማት ፣ ለባለስልጣናቱ ፣ ለአፋኝ ህጎቻቸው ፣ ለተግባራቸው... የሚደረግን ማንኛውም አይነት ትብብር የመንፈግ ተግባርንን የሚመለከት ነው። ይህን ዘዴ ጅን ሻርፕ ማህበራዊ ትብብር መንፈግ ፣ ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ እና የፖለቲካ ትብብር መንፈግ በሚሉ ሶስት ንዑሳን ክፍሎች የከፍሎ ተንትኖታል። ማህበራዊ ትብብር መንፈግ በሚለው ስር የመንግስት ባለስልጣናትን እና ደጋፊዎቻቸውን ማግለል፣ ማውገዝ፣ ከማህበራዊ ግንኙነት መነጠል፣ ማኩረፍ እና ግላዊ ትብብርን ለባለስልጣናት እና ደጋፊዎቻቸው መንፈግና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ከመንፈግ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም መዋጮዎችን ማቆም ፣የስርአቱ ባለሚሉችና አጋፋሪዎች ንብረት በሆኑ የንግድ ድርጅቶችና ምርቶች ያለመገልገል፣ የገንዘብ ተቀማጭን ከመንግስትና ከመንግስት ደጋፊዎች ባንክ ማውጣት እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። የፖለቲካ ትብብር ከመንፈግ ጋር በተያያዘ ደግሞ ለወጉ የሚደረጉ ምርጫዎችን መቃወም፣ የመንግስት ተቋማትን መተው ፣ በመንግስት የሚደገፉ የተለያዩ ድርጅቶችን መተው/የንግድ ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል/ ያጠቃልላል። በአጠቃላይ ህዝቡን ያሳተፈ ትብብር መንፈግ በአንባገነኖች ላይ ትልቅ የሚባል ተፅዕኖ ማድረስ የሚችል የትግል ዘዴ ነው ። ይህ ዘዴ አንባገነኖች ያላቸውን የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ የበላይነት እንዲያጡ በማድረግ ለማንበርከክ ይረዳል።

ጣልቃ መግባት፡- ጅን ሻርፕ "The Politics of Nonviolent Action, Boston, Porter Sergeant" በሚለው መፅሐፉ እንዳብራራው ዘዴው የአገዛዙን ተቋማት ፣ ፖሊሲዎች ፣ አሰራሮች ፣ መርሆች ፣ ግንኙነቶች... ፋይዳ በማሳጣት አንባገነናዊውን አገዛዝ እንዲንኮታኮት የሚያደርግ ነው። ይህ ዘዴ በስሩ ተከታታይ ሁሉን አቀፍ አድማ (የሰራተኞች ፣ የተማሪዎች ፣ የመምህራን ፣ የነጋዴዎች ፣ የላባደሮች...)፣ህጋዊነት ለሌላቸው ሕጎች ሙሉ በሙሉ አለመገዛት፣ ህገወጥ ፍርድን አለመቀበል ፣ አማራጭ ተቋማትን ማቋቋም...የሚሉ በርካታ ዝርዝር ዘዴዎችን ይዟል።

## የሰላማዊ ትግል ዘዴዎች አመራረጥ እና አተገባበር

የተለያዩ የፖለቲካ ምሁራን እንደሚናገሩት በማንኛውም መልኩ አንድ ህብረተሰብ ወደ ሰላማዊ ትግል ከመግባቱ በፊት በአካል በመገናኘት ወይም ደግሞ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ምን አይነት የትግል ዘዴዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለበት በሰፊው በመወያየት፣ ወጥ አቋም መያዝ እና ጥሩ እቅድ ማቀድ አለበት። እዚህ ላይ ይህን ውይይት በማስተባበር እና በመምራት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና/ወይም የሲቪክ ማህበራት እና ልዩ ልዩ የህዝብ አደረጃጀቶች የአንበሳውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

የሰላማዊ ትግል ዘዴዎች የአንባገነኖችን ድክመት ከግምት ውስጥ በማስገባት እና በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ባገናዘ በመልኩ ሲተገበሩ ይበልጥ በተሳካ መልኩ አንባገነኖችን በፍጥነት ማስወገድ ያስችላሉ። በተመሳሳይ ክርስቶፐር ኤ.ሚለር "STRATEGIC NONVIOLENT STRUGGLE" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው የስልጠና መመሪያ ላይ ይህን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ አፅኖት ሰጥቶ ፅፏል። እዚህ ላይ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ባገናዘበ መልኩ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ግልፅ ለማድረግ የሀገራችንን የፖለቲካ ምህዳር መገለጫ የሚሆን አንድ ምሳሌ በማንሳት መመልከት እንችላለን።

እንደሚታወቀው በሀገራችን ኢትዮጵያ በቀላሉ አደባባይ በመውጣት ተቃውሞን ማሰማት ወይም የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄድ አስቸጋሪ ነው። እዚህ ላይ በ97 የታየው ዘግናኝ የመንግስት የሐይል እርምጃ ለዚህ ዓይነተኛ ማሳያ ነው። እንዲህ አይነት ጠባብ የፖለቲካ ምህዳር ባለበት ሀገር የትግል ዘዴዎችን እንዲሁ በጅምላ ሳይሆን ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ መምረጥ እንዲሁም አጠቃላይ ትግሉን ስልታዊ በሆነ መንገድ ማካሄድ ያስፈልጋል። አለበለዚያ አንባገነኖች የሚወስዱት የአፀፋ እርምጃ ብዙ መስዋትነት ሊያስከፍለን ይችላል። ክርስቶፐር ኤ.ሚለር እንደሚጠቁመው እንዲህ አይነት ጠባብ የፖለቲካ ምህዳር ባለበት ሁኔታ እንደ ፀሎተምህላ፣ ባንዲራን እና ወካይነት ያላቸው የተቃውሞ ምልክቶችን ማሳየት ፣ የስራ ማቆም አድማ..... ያሉ ብዙም ለአደጋ የማያጋልጡ ዘዴዎችን መርጦ በእነርሱ ተቃውሞን መጀመር ብልህነት ነው። በመቀጠልም ማንኛውንም ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ትብብሮችን ሙሉ በሙሉ በመንፈግ ስርዓቱ በሂደት ሲዳከም ጠንከር ወዳሉት ሰላማዊ ሰልፍ እና የመሳሰሉ የትግል ዘዴዎች መግባት ይቻላል። እንደ ክርስቶፐር ኤ.ሚለር ማብራሪያ ከዚህ በተጨማሪም ብዙ ህዝብን በአንድ ላይ የሚያሰባስቡ የተለመዱ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ስነ ስርዓቶችን በመጠቀም ተቃውሞን በአደባባይ መጀመር ይቻላል።

ከላይ ካነሳነው ሀሳብ ጋር በተያያዘ ደቡብ አፍሪካውያን የአፓርታይድ ስርዓትን ሲታገሉ የተቃውሞ ድምፃቸውን በአደባባይ ለማሰማት የተጠቀሙበትን ዘዴ እንደ ምሳሌ እንመልከት። በወቅቱ በደቡብ አፍሪካ የነበረው መንግስት ሰላማዊ ሰልፍ ማካሄድን በጥብቅ ከልክሎ ነበር። ስለሆነም ደቡብ አፍሪካውያን የተቃውሞ ድምፃቸውን በአደባባይ ለማሰማት ከሰላማዊ ሰልፍ የተለየ ሌላ ዘዴ መፈለግ ነበረባቸው። በመጨረሻ ጥሩ " ዘዴ አገኙ። ዘዴውም የቀብር ስነስርዓት ለመፈፀም በሚሰባሰቡበት ጊዜ ተቃውሞን ማሰማት ነበር። ከዚያም ደቡብ አፍሪካውያን የወዳጃቸውን አስከሬን በክብር ተሸክመው በትልልቅ ጎዳናዎች ላይ እየተንጎራደዱ የተቃውሞ ድምፃቻን ማሰማት ጀመሩ ፤መንግስትም አትቅበሩ ብሎ መከልከል ስለማይቻል ዝም ብሎ ለመመልከት ተገደደ።

በተመሳሳይ ብዙም ሳንርቅ እዚሁ በሀገራችን የመንግስትን በሐይማኖት ጣልቃ መግባት የተቃወሙ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ድምፃቸውን በአደባባይ ለማሰማት እየተጠቀሙት ያለው ዘዴ ሌላው በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ኢትዮጵያውያኑ ሙስሊሞች ፍፁም ሰላማዊ ሆነው በእጅ ምልክት፣አፍን በመሸፈን፣ ታላቅ የተቃውሞ ድምፅ በማሰማት እንዲሁም የተለያ የትርጉም ያላቸውን ቀለሞች በማሳየት ከአምልኮ ስፍራቸው ብዙም ሳይርቁ(በርግጥ ሐይማኖታዊ በአሎቻቸውን ሲያከብሩ በከተማዋ ዋና ዋና ክፍሎች ተቃውሟቸውን አሰምተዋል) ያሳዩት ተቃውሞ ብዙ ትምህርት ሊቀሰምበት የሚገባ ነው። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ቃሊቲ የታሰሩ መሪዎቻቸውን በነቂስ ወጥተው በመጠየቅ መንግስትን የሚቃወሙበት መንገድ የተቃውሞ ሂደታቸውን በሳልነትና እያደገና እየሰፋ መምጣት፣ በተጨማሪም ከአምልኮ ስፍራዎች ባሻገር መተግበር መጀመሩን የሚያመላክት ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሰላማዊ የትግል ዘዴ በጠባብ የፖለቲካ ምህዳርን መሰረት በማድረግ የትግል ዘዴዎችን በስልት በመምረጥ እራስን ከአንባገነኖች ጨካኝ የአፀፋ እርምጃ መከላከል እንደሚቻል እና እንዴት የተለመዱ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ስነስርዓቶችን በመጠቀም ጠንካራ ተቃውሞ በአደባባይ ማሰማት እንደሚቻል ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው።

ጅን ሻርፕ እንደሚያስረዳው የሀገርን የፖለቲካ ምህዳር መሰረት ባደረገ መልኩ የትግል ዘዴዎችን መምረጥ እና የትግል ስልትን መንደፍ ብቸኛ ከአምባገነኖች የሚሰነዘርን ዘግናኝ የአፀፋ እርምጃ መከላከያ ስልት አይደለም። ከዚህም ባሻገር ለፖሊስ እና መከላከያ ሰራዊት አባላት በግልፅ የትግሉን አላማ በማስረዳት፣ ለትግሉ ቀና እይታ እንዲኖራቸውና ሰላማዊነቱን እንዲረዱ የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ በመስራት የአንባገነኖችን እርምጃ በጉልህ መቀነስ ይቻላል። ያም ሆኖ ግን ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ለነፃነት እና ለዲሞክራሲ በሚደረግ ሰላማዊ ትግል ውስጥ ከአንባገነኖች የሚሰነዘርን ጥቃት ሙሉ በሙሉ ማስወገድ የሚቻል አለመሆኑን ነው። አንባገነኖች የትግሉን እንቅስቃሴ ለማፈን ሲሉ እርምጃ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ
ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ።
ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ።

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው። ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው።

ዋና አዘጋጅ፡- ነብዩ ኃይሉ
አድራሻ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10
የቤት ቁ. 320
ኢሜይል፡-nebiyuhailu@gmail.com

አዘጋጆች፡- ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል
ሰለሞን ስዩም

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን

አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ደረጀ መላኩ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትልና ስርጭት፡-
ወንድወሰን ክንፈ
0911-65 46 69
አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ
አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07
የቤት ቁ. አዲስ
አታሚ፡-
አድራሻ፡-
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-
01 11249659 - 0923 50 45 75
09 22 11 17 62 -0926 81 46 81
09 23 11 93 74 - 09 13 05 69 42
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

## ርእሰ አንቀጽ

# ከምርጫው በፊት የምርጫ መደላድሉ ይስተካከል

ለረጅም ጊዜ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተደብቆ የቆየው የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ በቅርቡ ይፋ ተደርጓል። በኢህአዴግ ጓዳ ተቦክቶ የተጋገረው ይኸው የጊዜ ሰሌዳ በአሳላፊው ምርጫ ቦርድ ይፋ ከመደረጉ አስቀድሞ ገዢው ፓርቲ ለምርጫው ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል። ለዝግጅቱም እንዲረዳው ከወራት በፊት በትምህርት ላይ የነበሩ ካድሬዎቹ ትምህርታቸውን አቋርጠው በድርጅታዊ ስራ ላይ እንዲያተኩሩ ትዕዛዝ እስከማስተላለፍ መድረሱ መዘገቡም አይዘነጋም። ዘንድሮ ስለሚካሄደው ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ተማክረው ይፋ ያደረጉት ኢህአዴግ እና ምርጫ ቦርድ ከምርጫው በፊት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች አሉ የሚል ምላሽ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች አግኝተዋል። ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ያነሷቸው የምርጫ መደላድሉ እንዲስተካከል የሚሞግቱት ጥያቄዎች መሠረታዊና የህዝቡን ፍላጎት የሚያንፀባርቁ ናቸው።

ውጤቱ በታወቀ ምርጫ የመሳተፍ ትርጉም አልባነት የገባቸው በርካታ ፓርቲዎች ፊርማ በማሰባሰብና ኮሚቴ በማቋቋም ቅሬታቸውን ለምርጫ ቦርድ ማቅረባቸው ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ፓርቲዎቹ አሁን የያዙትን አቋም ይዘው የት ድረስ ይዘልቃሉ? የኢህአዴግ ረጅም እጅስ ምን ያክሉ ፓርቲዎች በአብሮነት እንዳይዘልቁ የመነጣጠል ስራ ትሰራለች? የሚሉት አሳሳቢ ጥያቄዎች በጊዜ ሂደት ምላሽ የሚያገኙ ይሆናል። ያምሆኖ ፓርቲዎቹ ወደ ምርጫ ከመግባታቸው አስቀድሞ መሠረታዊ የሆኑ የምርጫ መደላድሎች መስተካከላቸው የኢህአዴግም ሆነ ለሌሎቹ ተፎካካሪዎች የሚበጅ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ምርጫ ቦርድም ራሱን ከኢህአዴግ ጣልቃ ገብነት በማላቀቅ ሁሉንም ፓርቲዎች በእኩልነት ለማገልገል የቀረበለትን ጥያቄ መቀበል ይገባዋል ። መንግስትም በበኩሉ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ጥያቄ በመቀበል ለነፃ ምርጫ የሚመች መደላድል መፈጠር እንዲችል የድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል። በተለይም ተፎካካሪ ፓርቲዎች አላማቸውንና ፕሮግራማቸውን የሚያስተዋውቁበት እንዲሁም በሀገራቸው ወቅታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አቋማቸውን ለህዝብ የሚገልፁባቸው መድረኮች ክፍት እንዲሆኑ መፍቀድ ይሆርበታል። እንደሚታወቀው በመንግስት አይን ያወጣ አፈና ዛሬ መንግስትን የሚተቹም ሆነ መንግስት ከሚያቀርበው የተለየ መረጃ የሚያቀርቡ ጋዜጦች ብርቅ ሆነዋል። በመሆኑም ተፎካካሪ ፓርቲዎች የመንግስትን ብዙሃን መገናኛዎች ሙሉ በሙሉ ተቆጣሮ ለፕሮፓጋንዳ ማሽንነት ከሚጠቀመው ኢህአዴግ ጋር ለመፎካከር አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ልሳን የሆነችው ጋዜጣችን ፍኖተ ነፃነትም የመንግስት ቀጥታ ጥቃት ደርሶባታል። ፓርቲው በሀገሪቱ ያለውን የነፃ ፕሬስ አፈና በማስተዋል ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ከልሳንነት ባለፈ የህዝቡን የመረጃ ክፍተት ለመድፈን እንድታግዝ በማሰብ እንደ ነፃ ሚዲያ እንድታገለግልና ኢህአዴግን ጨምሮ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ክፍት ማድረጉ ጋዜጣዋ በመላ ሀገሪቱ ተወዳጅነትን እንድታገኝ አድርጓታል። ይህ ሰናይ ተግባር ያበሳጨው ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ግን ጋዜጣዋ እንዳትታተም የተለያዩ እንቅፋቶችን ዛሬም ድረስ በማድረስ ላይ ነው። ይህ ተግባር አንድነት/መድረክ ወደ ምርጫ እናዳይገባ ታስቦ የተደረገ መሆኑ በአስቸኳይ በፍትሄ ሊበጅለት ይገባል።

የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሌላው መሰረታዊ ችግር ህዝብን በተለያዩ ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለማወያየት አለመቻላቸው ነው። ኢህአዴግ ለሚያደርጋቸው ስብሰባዎች በቀላሉ የሚገኙት አዳራሾች ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲሆን በተለያዩ ሰናካላ ምክንያቶች ይከለከላሉ። ስለሆነም በፓርቲዎቹና በህዝቡ መካከል ተከታታይ ግንኙነት ለመፍጠር እንዳይቻል እንቅፋት ተፈጥሯል። ይህ ችግር በዘላቂነት ሳይፈታ ወደ ምርጫ ለመግባት የማይታሰብ በመሆኑ ከመንግስት ዘላቂ መፍትሄ ይጠበቃል።

ለምርጫ የማይመች ሁኔታ ከፈጠሩት የመንግስት ተግባራት መካከል የሚጠቀሰው ሌላው ዋንኛ ችግር የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው የፓርቲ አመራሮችንና ጋዜጠኞችን ጨምሮ በሺ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በተለያዩ የሀሰት ክሶች በየወህኒ ቤቱ ይገኛሉ። ህዝብን ወግነው ከመንግስት ጋር በመጋፈጣቸው ብቻ ባልሰሩት ወንጀል ወህኒ የተጣሉት እነዚህ ዜጎች ነፃነታቸውን ሳያገኙ በምርጫ መሳተፍ አስቸጋሪ ነው። ከላይ በጥቂቱ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ካልቻሉ በኢትዮጵያ ነፃ ምርጫ ማካሄድ እንደማይቻል እናምናለን። ምርጫ ቦርድም ሆኑ ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ያነሱት የህዝቡን መሰረታዊ ጥያቄ እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። ለጥያቄዎቹ ቀና ምላሽ በመስጠትና በቶሎ ወደ ድርድር መግባት ካልተቻለ ግን ለሚፈጠረው ውስብስብ ችግር ኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ በጋራ ኃላፊነቱን ለመውሰድ ይገደዳሉ።

ምርጫዎች ደግመው ደጋግመው በመጭበርበራቸው ህዝቡ "በምርጫ ካርድ ለውጥ አይመጣም" ወደ ሚል ተስፋ አስቆራጭ ድምዳሜ ሊደርስ እንደሚችልም ለመገመት አይከብድም። ይህ በምርጫ ተስፋ የመቁረጥ ስሜትና ለዘመናት የዘለቀው የለውጥ ፍላጎት ተዳምረው ህዝቡን ወዴት እንደሚገፋት ግን በእርግጠኝነት ለመናገር ይከብዳል።

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ሲከናወኑ የቆዩት ምርጫዎች ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና የአቶ መለስ መንግስት በህገ ወጥ መንገድ እንዲያሸንፍ ተደርገው የተቀነባበሩ ነበሩ። እነዚህ ምርጫዎች ለመጭበርበራቸውና ያንንም ተከትሎ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለተከሰቱት ግዙፍ የህይወትና የንብረት ጥፋቶች ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ወቅቶች በስልጣን ላይ የነበሩት የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችም ከተጠያቂነት አይድኑም። ለገዢው ፓርቲ ጥቅም ሲል ለፓርቲዎች ጥያቄ ምላሽ መስጠት የተሳነው እንዲሁም ለሁሉም የሚመች መወዳደሪያ መፍጠር የማይችል የምርጫ አስፈፃሚ አካል ሁሉንም ፓርቲዎች በእኩል አይን መመልከት አይቻለውም። ስለሆነም የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ እኩል ማስተናገድ ካልቻሉ ኃላፊነታቸውን ህግን አክብሮ ለሚሰራ አካል ማስረከብ ይገባቸዋል እንላለን።

*ጋዜጣችንን "ፍኖተ ነፃነት" ብለናታል "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው።*





# ኃይለማርያምን ፍለጋ

ሰለሞን ስዩም

በተለያዩ ጊዜያት ስለጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ፅፌያለሁ። ይህን ያደረግሁት ስለ ሰውዬው መከታተል ከጀመርኩ ከረዥም አመታት በኋላ ነው። ጠ/ሚ/ሩ ወደ ስልጣን ከመጡ ከረዥም አመታት በኋላም። ወደ ስልጣን ከመምጣታቸው በፊትማ እንኳን እርሳቸውን ራሴንም አላውቅም ነበር። ስለ ጠ/ሚ/ር ኃይለ ማሪያም ደሳለኝ ለመሞገት ግን እድል በእጄ ላይ ጥላቸዋለች፡ ፡ ሰውዬውን ከደቡብ ብሔረ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፕሬዚዴንትነታቸው ጀምሮ ስለማውቃቸው። በነገራችን ላይ ስለ ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊና ኢህአዴግ ሙሉ ሀተታ የያዘ ወጥ መፅሐፍ (አሁን እንደተለመደው ጋዜጣ ላይ ከወጡ ፅሁፎቼ የተወደ አይደለም) በቅርብ ቀን እንደማስነብባችሁ ቃል እየገባሁ ለዛሬ በተወሰነ መልኩ ብቻ ከኃ/ማሪያም ጋር እያወዳደርኩ ካልሆነ ትኩረት አላረጋቸውም።

አቶ መለስ ሀሳባቸውን በመግለፅ አይታሙም፡ ፡ ሀሳባቸው ግን ከራሷ ግዛት ውጭ የሆኑትን ነገሮች በግድ ለመጠቅለል የምትጥር ነበረች። የመለስ ሀሳብ አብዛኛውን ጊዜ መሬት ካለው ነገር የበዛ ነበር። ይህ ማለት ጀርመናዊው ፈላስፋ ሄግል ‹‹በሀሳቤና ሀሳቤ በቆመለት ነገር መካከል ያለውን ልዩነት›› በማለት ለማስታረቅ ካደረገውን ጥረት በተቃራኒ ማለት ነው፡ ፡ አቶ መለስ ሀሳባቸው መሬት ካለው ነገር አልፎ የሚሄደው በሁለቱ መካከል (በሀሳቡና እውነታው) መካከል ያለው ልዩነት ባብዛኛው ወደሀሳቡ ስለሚያደላ ነበር። ሆኖም ግን፣ ሰውዬው ይህንንም ለማድረግ ብዙ ማሰባቸው ስለማይቀር የዘመናዊ ፍልስፍና አባት የሚባለው ዴካርተስ "I think hence I'm" ያለውን የሚያሟላ ይመስላል። ዴካርተስ "ስለማስብ እንዳለሁ አረጋገጥሁ" ያለው ቁምነገር በአቶ መለስ እና ተከታዮቹ ዘንድ ግን ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ወርዷል።

ኢህአዴግ በፖሊሲዎቹ ሁሉ ቁሳዊ ልማት የማረጋገጥ ጥረት ላይ ያጠነጥናል። የኢህአዴግ ፖሊሲ በተቻለ መጠን ሰዎች በልተው ስለማደራቸው ብቻ እንዲያስቡ የሚያትት ነው፡ ፡ ሆኖም ግን፣ በልቶ ስለማደር መወትወት መልካም ነው እንኳ ብንል መንገዱ የተበላሸ ይመስለኛል። ሊረጋገጥበት የሚችለው ጥራት ያለው ትምህርት ሲኖር ነውና። ኢህአዴግ ግን ‹‹እንብላ›› የሚለው የትምህርትን እናት ቀብሮ ነው። "የሰው ልጅ የሚያጠነጥነው በሆዱ ዙሪያ ነው" የሚለው ካርል ማርክስ የኢህአዴግን ፖሊሲ ተንብዮ መሆን አለበት። አሊያም መለስ/ ኢህአዴጎቹ በሰውዬው ሀሳብ ከመጠን በላይ ተመስጠዋል ማለት ነው። ይህ ማለት አቶ መለስ ከላይ ያሰፈርነውን የዴካርተስ "I think hence I'm" ሲያነብ "I eat thus I'm" (በልቼ ስለማድር መኖሬን አረጋገጥኩ) ብሎ ነው ማለት ነው። እኔ ግን መብላት የመኖር ትርጉም ነው አልልም። ከዚህ ሁሉ ግን፣ ብሉይ ቢሆንም "I'm certain that I'm, because I think" ብል ይቀለኛል። ጠ/ሚ/ር ኃ/ማርያም ደሳለኝ እንደ መለስ ዜናዊ በቃላት አይጫወትም። በቃላት መጫወት የምለው ልክ እንደ ሶፊስቶች አሊያም ዲያሌክቲስቶች የቃላት ሰርከስ በመስራት ለእውነት ግን ግድ ማጣትን ነው።

አቶ መለስ አንድ ከተሰጣቸው ዓረፍተ ነገር አሊያም ራሳቸው ከሰሩት ዓረፍተ ነገር (premise) ሌሎችን እያራቡ በመጨረሻ የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር የሚቃረን ሀሳብ ጋር ሊወስዱን የሚችሉ መሪ ነበሩ። በከፍተኛ ምክንያታዊነት የደረሰበት የሚመስለው የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ግን የእውነቱ ተቃራኒ ነው። ይህ የ ‹‹Dialectics›› ጥበብ ነው።

> ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ስሀ/ማሪያም ስለ ኢህአዴግ ብዙ ነገር ይነግሯቸው ነበር ብዬ እገምታለሁ፡ ፡ ጠ/ሚ/ር ኃ/ማሪያምም ያለ መጠራጠር እንዳሉ ይውጧቸዋል፡ ፡ ይህን ለምን ያነሳሁ መሰላችሁ፡ ፡ ዴካርቴስ ‹‹ከማሰቡ›› በተጨማሪ ሁለተኛው የመኖሩ ማረጋገጫ ያደረገው ‹‹መጠራጠሩን›› ስለነበር ነው። ዝም ብሎ መስማትማ እንስሳትም ይሰማሉ።

ሶፊስቶች ደግሞ አሉ። ሶፊስቶች እንጀራቸውን የሚያበስሉት ምክንያታዊነትን ያለ አግባብ በመጠቀም ነው። አግባብ ያልሆነ አመክኒዮ በመጠቀም እውነትን በማድማት ኑሯቸውን የሚመሩ ናቸው። አሊያም ደግሞ የተሰጣቸው ደረጃ፣ ደረጃውን ለሰጧቸው ቡድኖች እውነትን ባደሙላቸው መጠን ነው። ነገር ግን ይህን ሲያደርጉ እውነተኛ ለመምሰል በቃላት ጨዋታ የተካኑ መሆን አለባቸው። የግላቸው ዋና አላማ ደግሞ በየትም ብለው የተመኙትን ቦታ መያዝ ነው። እነዚህን ለመዋጋት ፍልስፍና እንደጀመረ የሚነገርለት ታላቁ ፕላቶ የሶፊስቶችን መንገድ "unreal wisdom" /እውነተኛ ያልሆነ ጥበብ/ ይለዋል።

የመለስ ዜናዊ እንጀራ ስልጣን ላይ ረዥም ጊዜ ለመቆየት ከሆነ ሶፊስትም ነበሩ ልንል ነው፡ ፡ ኃ/ማሪያም ግን ሶፊስትም ዲያሌቲክስትም ሳይሆኑ እንደምን የመለስ አልጋ ወራሽ ሆኑ? ይህ ማለት ኃ/ማሪያም ለእውነት የቆሙ ናቸው ብዬ አይደለም። ይልቅ እንደ መለስ የቃላት ጫካ መሃከል ሳይደበቁ በግልጽ እውነትን ስለሚያጠቁ ብዬ ነው። መለስ ዜናዊ ንግግር አዋቂ ናቸው እንላለን። ‹‹እውነት›› አዋቂ ግን አልነበሩም። ንግግርም እውነትም የማያውቁት አቶ ኃይለማሪያም ታዲያ እንዴት ለመለስ ተተኪ ሆኑ ነው ጥያቄዬ።

የዛሬ አላማዬ መጠየቅ በመሆኑ ያለ መልስ እቀጥላለሁ። አቶ ኃ/ማሪያም የኢህአዴግ ፕሮግራም ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር ይመሳሰላል ሲሉ ክርስትና ሊሰብኩን የሞከሩ እለት "እውነት እኚህ ሰው ኢህአዴግን ያውቃሉ?" ብያለሁ፡ ፡ አንድ አብነት እንኳ ባነሳ የኢህአዴግ / ህወሓት ህገ መንግስት ሰዎችን በብሔራቸው፣ በብሔረሰባቸው አሊያም በህዝባቸው በኩል ካልሆነ እንደማይቀበል ሳያውቁ በእንደምን ጠ/ሚ/ር ሆኑ እላለሁ። መፅሐፍ ቅዱስ በክርስትና መስፋፋት ላይ ስኬት ያገኘው ሰዎችን ከቡድናቸው ውጭ እኩል በማየቱ ነው። ኃ/ማሪያም ግን የመንግስታቸው ህገ መንግስት መግቢያ የሚለውን ሳያነቡ (ቢያነቡ ያንን አይሉም ነበር) ጠ/ሚ/ር መሆናቸው እንቆቅልሽ ይሆንብኛል። መግቢያው "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች . . ." ከማለት የዘለለ "በምርጫዬ ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለውን ክላውድ ሳምነር፣ ህይወቱን ሙሉ ኢትዮጵያን ያገለገለውን ሪቻርድ ፓንክረስት . . . አያጠቃልልም። "ዘሬ ክርስቶስ ነው" የሚለኝ ፕሮቲስታንት ጓደኛዬን ‹‹ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር ይመሳሰልብኛል›› የሚሉት የኢህአዴግ ፕሮግራም የት ያውቀዋል? ኃይሌ የኢህአዴግን ፕሮግራም እንደማያውቁ ግን መልስ አግኝቻለሁ። መልሴንም መጠየቅ (quesstion) ብትችሉም ቅሉ። "አንድን ነገር" ማወቅ ምንነቱን መተንተን፣ መዘርዘርና መናገር ነው። ነገር ግን በተመሳሳይ ሰዓት "አንድ ነገር" ምን እንዳልሆነ መተንተን፣ መዘርዘር እና መናገር ይጠይቃል። በዚህ መስፈርት መሰረት ኃ/ማሪያም ኢህአዴግ ምን እንደሆ እንጂ ምን እንዳልሆነ አያውቁም። ይህ ሌላኛው ገጽ ዋነኛው የኢህአዴግ ገጽ ነበር፡ ፡ ዴሞክራሲያዊ ያለመሆኑ፣ ክፍት ያለመሆኑ፣ ሆደ ሰፊ ያለመሆኑ። ማወቅ ግልጽና ልዩ (clear & distinct) የሆነ ፀባይ መተንተንን ይጠይቃል፡ ፡ ስለዚህ አቶ ኃይለማሪያም ኢህአዴግን አያውቁም።

ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ለሀ/ማሪያም ስለ ኢህአዴግ ብዙ ነገር ይነግሯቸው ነበር ብዬ እገምታለሁ። ጠ/ሚ/ር ኃ/ማሪያምም ያለ መጠራጠር እንዳሉ ይውጧቸዋል። ይህን ለምን ያነሳሁ መሰላችሁ፡ ፡ ዴካርቴስ ‹‹ከማሰቡ›› በተጨማሪ ሁለተኛው የመኖሩ ማረጋገጫ ያደረገው ‹‹መጠራጠሩን›› ስለነበር ነው። ዝም ብሎ መስማትማ እንስሳትም ይሰማሉ። አይመርጡትም፣ አይጠረጥሩትም፡ ፡ ይህ አርስቶትል "Animals are true machines" ብሎ ከዘረዘረው ከግዑዝነት ትንሽ ብቻ ከፍ ማለት መስፈርት ጋር ይጣጣማል፡ ፡ እንስሳት የሚመጣውን መረጃ /ሁነት ከማስተናገድ ውጭ የገባውን አያመዛዝኑም፣ አይሰልቁም። የገባውን ሁነት ካላመነዠኩት እንደሚያስቡ እንዴት እናረጋግጣለን?

ለሰው ግን እንዲህ መሆን ባልተገባው። የኃ/ማሪያም ሁሉን መዋጥ ግን መጠራጠሩንና ማሰቡን እንድጠራጠር አድርጎኛል። ታላላቆቹ የሀሳብ ሰዎች "A mind can't cease to think unless cease to be"/አዕምሮ መኖር(መሆን) ካላቆመ ማሰብ አያቆምም / ከሚለው ሀሳብ ጋር እየተጣረሰብኝ ነው። ለዚህም ነው "እውን ሰውየው አሉ?" ስል ፍለጋ የጀመርኩት። እውን ሰውየው አሉ?

# የኢትዮጵያ ምርጫ የምር ወይስ ለምዕራባዊያን ዕጅ መንሻ?

ዳንኤል ተፈራ

በጊዜው ደርሰህ (ሥሙ የተቀየረ) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳንይንስ ምሩቅ ነው:: ተፈጥሯዊ ፍላጐቱና የተማረው ትምህርት ተደምሮበት በፖለቲካ ፍቅር እንዲወድቅ ወይም እንዲለከፍ እንዳደረጉት ይናገራል:: ለፖለቲካ ጆሮውን ያልሰጠበት ግዜ እንደሌለ ይነገራል:: የፖለቲካ መነቃቃትና ፍትጊያ ከሚካሄድባቸው ወቅቶች ደግሞ የምርጫ ወቅቶች ዋንኞቹ ናቸው:: በጊዜው ደርሰህ ከቦክስ መልስ የሚካሄድ የጦፈ ክርክር የሀገሩ ባህል እንዲሆን ይመኛል:: ተስፋ ያደርጋል:: ግን ደግሞ ተስፋው ቀረብኩህ ሲለው እየራቀበት ይቸገራል:: ምርጫ በኢትዮጵያ የተሰቀለ የተስፋ ዳቦ ነው ይላል::

በጊዜው ራሱን ከሸሸገበት የመምህርነት ሙያ ውስጥ ሆኖ ተለክፌበታለሁ የሚለውን ፖለቲካ አጮልቆ ይመለከታል:: አንዳንዴ ሲቪክስ ለሚያስተምራችው ተማሪዎቹ ሁሉንም አፍረጥርጦ ለመናገር እንደሚከጅለው ያስታውሳል:: ወዲያው የማስተማር ነፃነቱን (academic freedom) የነጠቀው ግምገማ የሚባል ት/ቤት ውስጥ ያለ ሰርጐ ገብ ፊት ለፊቱ ይገተርበታል:: እንጀራ የሚሉት ጣጣና ድህነት የተባለው በሽታ ጥፍራቸውን ያሳዩታል:: ከዚያ "ምርጫ በኢትዮጵያ . . ." ብሎ የጀመረውን ርዕስ ያለማወራረጃ ይውጠውና "እ . . . ማለቴ ምርጫ በአሜሪካ . . ." በማለት ምሳሌ ለማምጣት ከ13 ሺ ማይል በላይ ይጓዛል:: ከሩቅ ደክሞ ያመጣውን ምሳሌ ደግሞ እሳት የላሱ ተማሪዎቹ ከሚያነሱት ጥያቄ ጋር ለማጣመር ይቸግረዋል:: ይሄ የዕለት ተዕለት ህይወቱ ነው ይላል መምህር በጊዜው::

የፈረደበትን የአሜሪካን ምርጫ አንስቶ ለማስረዳት እወዳለሁ:: "ለምሳሌ በአሜሪካ ምርጫ ነፃ፣ ገለልተኛና ፍትሐዊ ነው ሲባል ባራክ ኦባማና . . ." ስል አንዳንድ ተማሪዎቼ አያስጨርሱኝም ይላል "ቲቸር! እኛም ሀገር እንደሱ ይባላል ግን ከቃል ባለፈ በተግባር ተጠርንፏል" ብለው ያፋጥጡታኛል:: ግን በጊዜው እንደሚናገረው ማምለጫ አላጣም ይላል:: "ዴሞክራሲ ሂደት ነው፣ ማለቴ የኛ ሀገር ዴሞክራሲ ጨቅላ ነው፣ ታዳጊ ነው" በማለት ነብሳቸውን ይማርና ከመለስ በሰማሁት ቃልና አሁን ደግሞ ጠ/ሚ ኃይለማርያም "ዴሞክራሲ ተበጥብጦ አይጋትም በሂደት ያድጋል" ካሉት ተውሼ ሾልኬ እወጣለሁ በማለት ይተርካል::

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም ባደረገው ኢ-ወጋዊ ዳሰሳ በርካታ ኢትዮጵያውያን ስለምርጫ ሲነሳባቸው የተሰላቸ ስሜት ያሳያሉ:: ከቃልነት ባለፈም ትርጉም መሰጠት አይፈቅዱም:: ርዕሱ ሲነሳባቸው "ሌላ ርዕስ የለህም!" ማለትን ያዘወትራሉ:: ህዝቡ ምርጫን ለማህበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ህይወቱ ቁልፍ ወይም ካርድ እንዲያደርገው ገዥው ፓርቲ የሚፈለግ አይመስልም:: በምርጫ የተፈጠረው መሰላቸትና ድብታ የተመቸው ይመስላል:: ስለዚህ ፍጆታነቱ የእርዳታ ዕጃቸውን ለሚፈልጋቸው ምዕራባውያን ብቻ ሆኖ እንዲያገለግል ተፈርዶበታል:: እንደዚህ ካልሆነ በስተቀር 21 ዓመት ሙሉ "ጨቅላ" እየተባለ የሚነገርለት ዴሞክራሲ ከኢትዮጵያ ውጪ ሌላ የት ይገኛል? በዚህ የሰለጠነ ዘመን 21 ዓመትን እንዴት ትንሽ ማድረግ ይችላል? ይህንን ማድረግ ያልቻሉት የስርዓቱ መስራቾች "ህዝቡ ለዴሞክራሲ አልደረሰም" እያሉ ዳቦ በቀደደው አፋቸው ይሰድቡናል::

አሁንም ኢ-ወጋዊ ዳሰሳዬ እንደጠቆመኝ በርካታ ወጣቶች የምርጫ ጥማታቸውን የዴሞክራሲ ናፍቆታቸውን በየ 4 ዓመቱ በሚካሄደው የአሜሪካ ምርጫ ያወራርዳሉ:: ከኢትዮጵያ ምርጫ ይልቅ ለአሜሪካ ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ ቅርበት አላቸው፤ የኢትዮጵያን ምርጫ ከመተንተን ይልቅ የአሜሪካን የምርጫ ሂደት አሳምሮ መተንተኑ ይቀላቸዋል:: በርካታ የሀገሬ ወጣቶች በሀገራቸው ያጡትን ፍትሐዊና አጓጊ ግብግብ ያለበት ምርጫ ብዙ ሺ ማይልስ ርቀው ይቀላውጡታል::

ባለፉት ሳምንታት የተከናወነውም ይሄው ነው:: ባራክ ኦባማና ሚት ሩሚኒ ባደረጉት ውድድር በርካታ ኢትዮጵያውያን ታድመዋል:: መታደማቸው አምሮታቸውን ለመወጣት ነበር:: በሀገራቸው ያጡትን ፍለጋ ነው:: ሚት ሩሞኒ ከተሸነፉ በኋላ ባደረጉት ንግግር ቀንተናል:: "ታድለው!" ብለናል:: ተቀናቃኞች እንደዚያ ተቃቅፈው መሳሳምን የኛ ባህል አያውቀውም:: የኛ ባህል የሚያውቀው ሰብስቦ እስር ቤት መክተትን ነው፤ መግደልንና ማሳደድን ነው:: ታዲያ ለምን አይቀናም?

የምረጡኝ ቅስቀሳው ራሱ በጥላቻ ቅራቅንቦ የተሞላ ነው:: ፀረ ምንትሴ የሚበዛውና ውሽልሽል:: የአሜሪካ ምርጫ በተካሄደ ማግስት ደግሞ በኢትዮጵያ ይሄው "ምርጫ" የሚሉት ቃል እየተሰማ ነው:: በ2005 ዓ.ም የሚካሄደው የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ ማለቴ ነው:: ይሄ ምርጫ ከዋናው ሀገራዊ ምርጫ ቀጥሎ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና ትልቅ የፖለቲካ ትርጉም ያለው ነው::

በ2005 ዓ.ም የሚካሄደውን ምርጫ የፖለቲካ ትርጉሙን ከፍ እንዲል ከሚያደርጉት መካከል ደግሞ አዲስ አበባ ዋነኛዋ ናት:: ይህችው 125ኛ ዓመት የሞላት ከተማ የፖለቲካ ከተማ ናት፤ የኢትዮጵያ እምብርት ናት፤ የክልሎች የልብ ትርታና የአፍሪካ አይን ናት:: ታዲያ መስተዳድሩን ለመረከብ የሚካሄደው ምርጫ መሆኑ ነው ትልቅ የሚያደርገው:: ቁልፉን በእጅ ለማስገባትና ቁልፍን ይዞ ለመቀጠል የሚደረገው ግብግብ ግን ያው በተለመደው የምርጫ ወጋችን የሄደ ነው:: ምርጫው እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው ነው ይላሉ በርከት ያሉ ታዛቢዎች::

ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ቁልፍ ላለመስጠት ውድድሩ የጦፈ እንዲሆን አልፈለገም:: ለዚህ ግሩም ማሳያ የሚሆነን በምርጫ ቦርድ ተባባሪነት ወይም ምርጫ ቦርዶች ስራ በዝቶባቸው መሆኑ በውል ሳይለይ ምርጫው መቼ እንደሚካሄድ ሳይታወቅ መክረሙን ለአብነት ማንሳት ይቻላል::

ገዥው ፓርቲም የመንግስት ስልጣኑን ጭምር በመጠቀም በዝግጅት ተጠምዷል:: ለምርጫው ትኩረት ያልሰጠ በመምሰል ውስጥ ውስጡን እንደፈለገው የሚቆጣጠረውን ሚዲያ በመጠቀም ከእኔ ውጭ ሌላ ላሳር የሚል መልዕክቱን ያዥጐደጉደዋል:: የአዲስ አበባን 125ኛ ዓመት አከብራለሁ በማለት ባለፈው ዓመት ህዳር ወር የተጀመረው ዝግጅትም ምርጫውን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም:: ስራ የፈቱ ቡልደዘሮች ሁሉ በየመንደሩ ያሉ ፒስታ መንገዶችን መቆፈር ይዘዋል:: በተጓዳኝም የምረቃ ጊዜያቸው ምርጫውን ታሳቢ ያደረጉ ፕሮጀክቶችም አይጠፉም:: የ40/60 ቤት ልማት ምዝገባም ይጀመራል . . . ግን ሁሉም በዚህ ፍጥነት ይቀጥላሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ አይመልሱም:: ከዚህ በፊት እንዳስተዋልነው ምርጫው ሲያልቅ "ፍሬን" ይያዛል::

ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ምርጫ ትልቅ ግምት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ምልክቶች አሉ:: እንደዚህ ሆኖም የምር ተቀናቃኝ አልፈለገም:: በተቃውሞ ጐራ ጉሮሮዬን ይተናነቁኛል ያላቸውን እንደ አንድነት/መድረክ ያሉ ፓርቲዎች ላይ የተለመደውን የመንግስትነት ስልጣን በመጠቀም አቅም የማሳነስ ሥራ ሰርቷል:: የአንድነት ፓርቲ ልሳን የሆነችው ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ውሃ በማይቋጥር ሰንካላ ምክንያት በብርሃንና ሰላም እንዳትታተም ሲያደርጉ ስናይ አዲስ አበባ ላይ ያላቸውን የስጋት ግዝፈት ያመላክተናል::

ከጋዜጣው አዘጋጆች እንደሰማነው የመንግስት የሆነውን ብርሃንና ሰላም መጠቀም አልቻሉም:: ጋዜጣዋን እንዲያትሙ የተጠየቁ የግል አታሚ ድርጅቶችን ሁሉ እየተከታተሉ በመግባትና በማደናቀፍ ለብቻቸው ተቃዋሚ ካባ ለባሽ ተለጣፊዎች ጋር "ተወዳድሮ" ለማሸነፍ ታቅዶ እንደሆነ መሳት አይቻልም::

አዲሱ ጠ/ሚ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ፓርላማ ቀርበው ስለ ጋዜጣዋ መዘጋት ሲናገሩ:- "ይሄ የማርኬቲንግ ጉዳይ ነው:: 34 አታሚዎች ስላሉ መርጣችሁ ማሳተም ትችላላችሁ . . ." ማለታቸውን አስታውሳለሁ:: ጠ/ሚንስትሩ ችግሩ ጠፍቷቸው አይደለም:: እግር እግር ስር እየተከታተሉ በደህንነት ስም የደህንነት መታወቂያ በማሳየት እንገልሃለን፣ እናርድሃለን የሚሉ ባለጥቁር መነፅር አስፈራሪዎች በርከት ብለው እንደተመደቡ አያውቁም ብዬ አላስብም:: ካላወቁ ግን ለጠ/ሚንስትሩ አንድ ሺ አንድ ማስፈራሪያ የደረሳቸው ወጣቶችን ላቀርብላቸው እችላለሁ:: ታዲያ ምርጫ በኢትዮጵያ የምር ወይስ ለምዕራባዊያን ዕጅ መንሻ?

ከላይ ለመጠቆም እንደሞክርኩት ለረጅም ጊዜ የአዲስ አበባ ምርጫ መቼ እደሚካሄድ ሚስጥር ሆኖ ከርሟል:: በያዝነው ዓመት 2005 ዓ.ም ግን ይፋ ተደረገ::

ጥቅምት 15 ቀን 2005 በናዝሬት በሚያዝያ ዓ.ም ለሚካሄደው የአካባቢ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ አፈፃፀምን ይፋ አደረገ:: 66 የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደተገኙ ተሰምቷል:: አንዳንዴ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ቁጥር መስማት ያቅለሸልሻል:: የቁጥራቸውን ብዛት ስሰማ በጭንቅላቴ የሚመጣው ጥያቄ ራሳቸውን የት ቀብረው እንደሚከርሙ ብቻ ነው:: ምርጫ ሲደርስ ከተፍ ይላሉ:: ግን የአዳማው ጉባኤ አስገራሚ ነገር ታይቶበታል:: በርከት ያሉት ምንም እንኳ ራሳቸውን ቀብረው ቢከርሙም





# አምባገነኖችን...

ከገፅ 3 የዞረ

ከመውሰድ ወደ ኋላ ላይሉ ይችላሉ:: ሆኖም ግን እንደ ጅን ሻርፕ ማብራሪያ መሰል እርምጃዎች አንባገነኖች በአለም አቀፍ ደረጃ ፍፁም እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል ፣ ትልቅ የዲፕሎማሲ ክስረት ይፈጥርባቸዋል፣ በሚታገለው ህብረተሰቡ ውስጥም እልህን እየፈጠረ ትግሉን የበለጠ ያቀጣጥለዋል:: እነዚህ ያልታሰቡ ውጤቶችም የኋላ ኋላ በእኩይ እርምጃቸው እንዳይቀጥሉበት ያደርጋቸዋል::

ጅን ሻርፕ እንደሚመክረው የህብረተሰቡ ቆራጥነት እና ስነ-ስርዓት የታከለባቸው ተቃውሞዎች እየተጋጋሉ በሚሄዱበት ወቅት በተመሳሳይ ሁሉን አቀፍ ትብብር የመንፈግ እርምጃዎች እየጨመሩ እና እየተጠናከሩ መሄድ አለባቸው:: ይህ ሲሆን የአንባገነናዊው አገዛዝ ውስጣዊ ድክመቶች እየጎሉ እና አገዛዙ እየተሽመደመደ ይሄዳል:: በዚህ ወቅት ግን ሊሰሩ የሚገባቸዉ ወሳኝ ጉዳዮች አሉ:: እነርሱም ነፃ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ተቋማትን ማቋቋም እና ያሉትንም ማጠናከርን የሚጨምሩ ናቸው:: እንደ ምሁሩ ማብራሪያ የእነዚህ ተቋማት ማቆጥቆጥ ለትግሉ አለም አቀፋዊ ተቀባይነትን የሚያስገኝለት ሲሆን ፤ በተጓዳኝ አንባገነናዊው አገዛዝ የሚደርስበት አለምአቀፋዊ ውግዘት እንዲጠናከር ያደርጋል::

## በሰላማዊ ትግል ውስጥ ያሉ ቁልፍ ነገሮች

በሰላማዊ ትግል ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን አፅኖት ሰጥተው እንደሚናገሩት አንድ ሰላማዊ ትግል የታቀደለትን ግብ ይመታ ዘንድ ብልህና ቆራጥ አመራር የሚያስፈልግ ቢሆንም በዋናነት በራሱ የሚተማመን ህዝብ ፣ ብልህነት የተሞላበት የትግል ስትራቴጂ እና ደፋር እርምጃ በጥምረት ሊኖሩት ይገባል:: እነዚህ ሦስት መሰረታዊ ነገሮች በጥምረት ባሉበት ሁኔታ ማንኛውም ሰላማዊ ትግል መጨረሻው ደማቅ ድል ነው:: አንባገነኖች ወደዱም ጠሉም አይናቸው እያየ የገነቡት እኩይ ስርዓታቸው መፈራረሱ እና እነርሱም በህዝብ እጅ ላይ መውደቃቸው የማያጠያይቅ ጉዳይ ይሆናል:: ሆኖም እነዚህ የተጠቀሱት ሦስት ነገሮች እንዳሉ ሆኖ ከእነርሱ ባሻገር ሌላ ተጨማሪ ለሰላማዊ ትግል ስኬታማነት ቁልፍ ናቸው ተብለው የሚጠቀሱ እና በማንኛውም ሰላማዊ ትግል ውስጥ ሊሟሉ የሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች አሉ::

ከእነዚህ በሰላማዊ ትግል ውስጥ ቁልፍ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ አንዱ እና ግንባር ቀደሙ አንድነት ነው:: "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንደሚባለው ሁሉ በሰላማዊ ትግል ወቅት የሁሉም ህብረተሰብ ክፍል በአንድነት መቆም አንባገነኖችን በፍጥነት ብዙ ጉዳት ሳያደርሱ እንዲንኮታኮቱ ያደርጋል:: ይህንን በተመለከተ ዶ/ር ሲንቲያ ቦአዝ "Nonviolent Revolution Clarified: Five Myths and Realities Behind Egypt's Uprising" በሚለዉ ፅሑፋቸው እንዳስነበቡት ከግብፃዊያን የሰላማዊ ትግል የስኬት ሚስጥሮች መካከል አንድነት አንዱ እና ዋናው ነበር:: ይህንን ቁልፍ የሰላማዊ ትግል ቁልፍ ነጥብ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን እንመልከት:: ኢህአዴግ የኢትዮጵያውያን አንድነት የስልጣን እድሜውን እንደሚያሳጥረው አስቀድሞ በመረዳቱ ህዝቡን በክልል፣በብሄር፣በሐይማኖት እና በተለያዩ መደቦች በመከፋፈል የልዩነትና የጥላቻ ዘርን ዘርቷል:: በተለያዩ ወቅቶችም የተደራጁ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ለማክሰም ከሚጠቀምበት የሃይል እርምጃ ጎን ለጎን አንዱን በአንዱ ላይ በጠላትነት በማስነሳት አንድነትን በማጥፋት የስልጣን እድሜውን ሲያራዝም ቆይቷል:: ስለዚህም ኢህአዴግን ለመጣል የሚደረግ ትግል በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የአንድት መንፈስን ማኖርና ልዩነቶችን ማቻቻል አስፈላጊ ነው::

ከአንድነት ቀጥሎ ለአንድ የሰላማዊ ትግሉ መሳካት ቁልፍ ተደርጎ የሚጠቀሰው ስነ-ስርዓት (Discipline) ነው:: ብዙ ምሑራን አንድ ሰላማዊት ትግል የአንባገነኖች ትንኮሳ ቢፈታተነውም እንኳን ሰላማዊ ስነ-ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ መካሄድ ይገባዋል በማለት ያሳስባሉ:: እንደ እነርሱ ማብራሪያ አንድ ትግል ፍፁም ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከተካሄድ አንባገነኖች በሐይል ጣልቃ ለመግባት ይቸገራሉ:: ይህም የሚከፈለውን የህይወት መስዋዕትነት በከፍተኛ ደረጃ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሰላማዊው ተቃውሞ ወደ ሐይል አመፅ ከተለወጠ ግን ለአንባገነኖች የሀይል በትራቸውን እንዲያነሱ በር ይከፍትላቸዋል::

ከስነስርአት ጋር በተያያዘ አንድ የኢትዮጵያውያን ታጋዮችን የቅርብ ጊዜ ተሞክሮ መጥቀስ ይቻላል:: ባለፈው አመት አጋማሽ ላይ የጋመውን የሙስሊም ምዕመናን ተቃውሞ ወደ ግጭት እንዲለወጥ መንግስት የተለያዩ ያልተሳኩ ጥረቶችን አድርጓል:: ከዚህ ጥረት ውስጥ የሚጠቀሰው ምዕመናኑ ተቃውሟቸውን በሚያሰሙበት ወቅት የከተማ አውቶብሶችን ከፊታቸው በመደርደር ለጥቃት ማመቻቸቱ ነው፤ ምዕመናኑ ግን ይህን ተንኮል አስቀድመው በመረዳታቸው "አንሰብርም...አንሰብርም" በማለት ስነስርአታቸውን አሳይተዋል:: ከዚህ በተጨማሪም መንግስት አስርጎ ያስገባቸውን በጥባጮች በመገሰፅ፣በማጋለጥና በካሜራ በማንሳት ፍፁም ስነስርአት የተላበሰ ሰላማዊ ትግል በማድረግ ላጥ ናቸው:: ዲሲፐሊን ከዚህ ባሻገር ጥቅም እንዳለው ጅን ሻርፕ እንዲህ ሲል ይገልፃል:- "Nonviolent discipline is extremely important… the stark brutality of the regime against the clearly nonviolent actionists politically rebounds against the dictators' position, causing dissention in their own ranks as well as fomenting support for the resisters among the general population, the regime's usual supporters, and third parties." ይህን ቃል በቃል ስንተረጉመው እንዲህ ይላል፤ "የሰላማዊ ትግል ዲስፕሊን እጅግ ጠቃሚ ነው… አንባገነኑ አገዛዝ ፍፁም ሰላማዊ በሆኑ ተቃዋሚዎች ላይ የሚወስደው የሀይል እርምጃ በራሱ የስልጣን ተዋረድ ውስጥ አለመግባባት በመፍጠር በራሱ ላይ ችግር ከማስከተሉ ባሻገር ለተቃዋሚዎች ከብዙኃኑ ህዝብ ፣ ከራሱ ከአገዛዙ ደጋፊዎች እና ከሌላ ሦስተኛ ወገን የፖለቲካ ድጋፍ ያስገኛል::"

# የኢትዮጵያ ምርጫ. . .

አሯሯጭ መሆኑ የታከታቸው ይመስላሉ:: ምርጫ ሲደርስ ጥቂት አበል እየተቀበሉ ምርጫ ማሟሟቅ የሰለቻቸው ይመስላል:: ስለዚህ 33 ፓርቲዎች የሚሆኑት ከአሯሯጭነት ወደ የምር ተወዳዳሪነት መምጣት አለብን በሚል ፒቲሽን ተፈራርመው "የምህዳር መጥበብ፣ የምርጫ አፈፃፀም ችግር፣ የአስፈፃሚ አካላት ተዓማኒነት" የመሳሰሉ እሳት ጥያቄዎች ላይ እንወያይ ማለታቸውን እየተንከላወሱ ካሉ ጥቂት ጋዜጦች ሰምተናል::

ምርጫ ቦርድ በድንጋጤ አፉ ኩበት እንደሚሆንበት እገምታለሁ:: ያልተለመደ ጥያቄ ነበር:: ለፖለቲካ መሰላቸት ትልቅ ምልክትም ነበር:: የጥያቄው እውነተኛነት ሲመዘንም ሚዛን ይደፋል:: እጅ ታጥቦ ለመብላት ከቀረቡ በኋላ እንደመከልከል ያለ ነው::

መቼስ ምርጫው ላይ ውድድር እንዳይኖር መፈለግ ካልሆነ በስተቀር እንዴት ሚያዝያ ለሚካሄድ ምርጫ ጥቅምት ላይ የጊዜ ይነገራል? እንዴት አይነት ዝግጅትስ ወር ባልሞላ ጊዜ ይካሄዳል? ከምር ግን እዚች ሀገር ላይ ትክክለኛ ምርጫ እንዲደረግ ይፈለጋል? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንነት ተገቢ ነው:: መቼስ ነው ምርጫ በኢትዮጵያ እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው የሚሆነው? ዛሬም ሂድ አትበለው ግን እንዲሄድ አድርገው ኢህአዴግን ያስኬደው ይሆን? አይመስለኝም::

ለዚህ መጣጥፍ ይረዳኝ ዘንድ 33 የፖለቲካ ፓርቲዎች ያዙት የተባለውን አቋም ለማየት ሞክሬ ነበር:: 18 ነጥቦች መስተካከል አለባቸው ወይም እንወያይባቸው ተብለው ተቀምጠዋል:: አስራ ስምንቱን መጥቀስ ባልችልም ለአንባቢያን ፍርድ ይመች ዘንድ ጥቂቱን ልጥቀስ የምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኛ አለመሆን፣ የታዛቢዎች መባረር፣ የህዝብ ታዛቢዎች በመንግስት መመረጣቸውና ከተፅዕኖ ነፃ ያለ መሆናቸው ጉዳይ፣ የሚዲያ አጠቃቀም፣ ተቃዋሚዎች ከህዝብ የሚገናኙበት መንገድ መዘጋቱ፣ የነፃው ፕሬስ ላይ ያለው አፈናና መዝጋት፣ ጥርነፋ . . . የመሳሰሉ ጉዳዮች መዘርዘራቸውን ተመልክቻለሁ::

እንደሚመስለኝ ነፃው ፕሬስ ላይ ያለው አፈናና ፍኖተ ነፃነት እንዳትታተም የሚደረገው ጥረት ብቻውን ቢታይ እንኳን ኢህአዴግ ነፃ፣ ፍትሐዊና ገለልተና ምርጫ እንዳይኖር መፈለጉን ያሳያል::

የዚህ ሁሉ መፍትሄ ያለው ግን በቅድሚያ ገዥው ፓርቲ እጅ ላይ ነው:: ምርጫ ቦርድም ሰፊ ውይይት እንዲካሄድ መፍቀድ ይገባዋል:: የ33 ፓርቲዎች ጥያቄ ተዘሎ የሚታለፍ አይመስለኝም:: የመጨረሻው መፍትሄ ያለው ግን ተቃዋሚዎች ዘንድ ነው:: እሱን ግን አልናገርም::

# “በምርጫው እንሳተፋለን የሚል አቋም ላይ አልደረስንም”

## አቶ ገብሩ ገ/ማርያም (የመድረክ አመራር)

**የቀድሞ የፓርላማ አባልና የመድረክ አመራር ከሆኑት ከአቶ ገብሩ ገ/ማርያም ነብዩ ኃይሉና ዳዊት ሰለሞን ጋር በመጪው ምርጫና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቆይታ አድርገዋል፤መልካም ንባብ።**



ጥያቄ፡- አምባገነን ስርዓት ባለበት አገር በምርጫ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብለው ያምናሉ?

አቶ ገብሩ፡- የእኔ እምነት ምንም ያህል አፋኞችና ጨቋኞች ቢሆኑ፣ ምንም ያህል ለህዝብ ድምጽና ዋይታ መልስ መስጠትና ጆሮሯቸውን ማዋስ ባይችሉም፣ በእነዚህና በሌሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የምንገኝ ቢሆንም በሰላምና በሰላም ብቻ እንዚህን አምባገነኖች መታገል ተገቢ ነው የሚል ነው። በተለይ አሁን በምንገኝበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያለው የትግል አማራጭ ይህ ነው። በዚህ አማራጭ ትግል ደግሞ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በተለይም በአረቡ አለም የህዝብ እምቢ ባይነት ምን ሊያስከትል እንደሚችል በተግባር ታይቷል። የታህሪር አደባባይ ህዝብ ያመጣውን ለውጥ በአይናችን ያየነው ይመስለኛል። ትግሉ አልፎ አልፎ የሰው ህይወትን ጠይቋል። እንዲህ አይነት ድርጊት የአምባገነኖች ባህሪ ነው። የእነ ሙባረክ መባረር ምንጩ የህዝብ እምቢ ባይነት ነው። የግብፅ ህዝብ ወደ አደባባዩ በመውጣት ወደ ቤቴ አልመለስም በማለት ድንኳኑን ተክሎ የአምባገነኖቹን መጨረሻ እስከ ሚመለከት ትልቅ ዋጋ ከፍሏል። ሰላማዊ ትግል አምባገነኖችን ከስልጣቸው እንዲወገዱ ያደረጋቸዋል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ።

ጥያቄ፡- ሰላማዊ ትግል አምባገነኖችን እንደሚያወርድ በብዙ ቦታዎች ተመልክተናል። ነገር ግን በአረቡ አለም የተደረጉት የሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴዎች ከምርጫ ጋር የተገናኙ አልነበሩም። እነ ሙባረክ በምርጫ ብዙ ጊዜ አጭበርብረው በኃይል ለብዙ አመታት ገዝተዋል። የወረዱት ግን በሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ እንጂ በምርጫ አልነበረም። ኢህአዴግ በ21 ዓመታት የአገዛዝ ዘመኑ አራት ምርጫዎችን አካሂዷል። ነገር ግን በእነዚህ ምርጫዎች ድምጽ እየተጭበረበረ ሰዎችም በዚሁ ጠንቅ እየተገደሉ ዘልቋል። ገዢው ፓርቲ ድምፅ እያጭበረበረና ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በምርጫ እየተሳተፉችሁ እስካሁን ተጉዟችኋል። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል?

አቶ ገብሩ፡- አሁን የተነሳው የሙባረክ መንግስትም ቢሆን ከ30 አመት በላይ መግዛት የቻለው በምርጫ ስም ነው። እኛም አገር ላለፉት 21 ዓመታት በተለይም የምዕራቡን አለም ወዳጅነት ለማግኘትና ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ሆያ ሆዬ የሚዘፈንበት የምርጫ ወቅት ነበር። ይህንን እኛም ሆንን ህዝባችን ጠንቅቀን እናውቃለን። ሆኖም ግን እኛ የምርጫ ፓርቲ ነን። ምርጫው እውነተኛና ተአማኒ ባይሆንም በምርጫው በመሳተፍ ምን ማድረግ እንደምንችል የ1997 ምርጫ እንዳሳየን አስባለሁ. . .

ጥያቄ፡- ይቅርታ. . . በትክክልም በምርጫ 97 ጥሩ መነሳሳት ነበር። ነገር ግን የምርጫው ውጤት በህዝቡ የለውጥ ጥያቄ ላይ ምን ያመጣው ለውጥ አለ?

አቶ ገብሩ፡- በእኔ እምነት የንቃተ ህሊና ለውጥ አምጥቷል። ህዝቡ መሣሪያ ፈርቶ ዝም ያለ ቢሆንም የዚህ ህዝብ ዝምታም እምቢታ ነው። “ዝም ያልኩት ተቀብዬህ አይደለም” ማለት ነው ለእኔ። ዝም ብለህም የምትሰራው ነገር አለ። በ97 ምርጫ ህዝቡ ያመጣው ለውጥ በጣም ከፍተኛ ነበር። ያኔ በህብረት ስር የነበርን ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ጋር ባደረግነው ድርድር ያስቀመጥናቸው አምስት ነጥቦች ለዚያ ምርጫ በመለቀቃቸው ከፍተኛ መነሳሳት ሊፈጠር ችሏል። አሁንም የአደረጃጀት ስልታችንን የተሻለ አድርገናል። በመድረክ ዙሪያ በመሰባሰብ በ1997 የተፈጠረው ስህተት ምን እንደነበር በማጥናትና የኢህአዴግ የጭቆና ስፋት ምን ያህል ነበረ? አሁንስ ወዴት እየሄደ ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ገምግመን መድረክን በቅንጅትነት ከመሠረትን በኋላ አሁን ወደ ግምባርነት አሸጋግረነዋል። ይህ አንዱ ትልቅ ስራ የተሰራበት ነው። መድረክን ወደ ግምባርነት ያሸጋገርነው ከመሬት ተነስተን ዝም ብለን አይደለም። ለሦስት ዓመታት ያህል የተለያዩና እጅግ አወዛጋቢ በሆኑ በዚህ አገር ጉዳዮች ላይ ተነጋግረናል። የአለም አቀፍ ሁኔታ እየተቀየረ ነው። ሌላው ቀርቶ የአገራችን ሁኔታም ተቀይሯል። የኢህአዴግ መሪዎችም ከመለስ ህልፈተ ህይወት በኋላ መፈክራቸው ተለውጦ አንድና አንድ ብቻ ሆኗል። የህዝብ ንቃተ ህሊና እየጨመረ ነው። ወጣቶች በአገራቸው ጉዳይ እየተሳቡ መጥተዋል። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ተጣምረው በሚታዩበት ሁኔታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በርትተው መስራት የሚገባቸውን ስራ ከሰሩ ሰላማዊው ትግል ፍሬ የማያፈራበት ምክንያት አይኖርም።

ጥያቄ፡- በተለይም ከ1997 በኋላ የምንመለከታቸው ነገሮች ተስፋ ሰጪ አይደሉም። የፖለቲካው ምህዳር የጠበበት፣ ነፃ ሚዲያ የኮሰሰበት፣ ሲቪክ ማህበራት እንዲከስሙ የተደረገበት ሁኔታ ነው ያለው። በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ስለ ምርጫ ማሰብ ተገቢ ነው?

አቶ ገብሩ፡- ማሰባችን አሁንም አግባብ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ ትክክል ናቸው። ነገር ግን እንደ አንድ ፖለቲከኛ በአገሬ እነዚህ ነገሮች መኖራቸው ለበለጠ ትግል እንድነሳሳ ያደርገኛል። በመርፌ ቀዳዳም ቢሆን ትግሉ መቀጠል አለበት። የፖለቲካ ህጋዊ ትግሉ የመርፌ ቀዳዳ ያህል የጠበበ ቢሆንም የተፈጠረችውን ቀዳዳ ተጠቅሞ መታገል ተገቢ ነው። ስለዚህ እነዚህ ሁኔታዎች የሉም ማለት አይደለም። ነገር ግን ይህ ነገር ቢኖርም ኢህአዴግን የምትሰራውና የምታወራለት ልማት የህዝቡን እምነት ያገኘ አይደለም በማለት እንታገለዋለን። ምንም እንኳን ብልጭልጭ ነገሮችን በማሳየት ልማታዊ መንግስት ነኝ ለማለት የሚደፍር ቢሆንም የልማቱ ውጤት ህዝቡ ኪስ ውስጥ መግባት አለመቻሉን እንነግረዋለን። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ዋጋ ግሽበቱን ከሁለት ወደ አንድ ዲጂት እንደሚያወርዱት ተናግረው ነበር። ነገር ግን ግሽበቱ እየባሰበት እንጂ ሲቀንስ አልተመለከትነውም። እኛ ግን ይህንን የሚለወጥ አቅም ያለን በመሆኑ በትግላችን እንቀጥላለን።

ጥያቄ፡- ብዙዎች አሁን ባለው ምርጫ መሳተፍ ለአገዛዙ እውቅና እንደመስጠት ይቆጥሩታል። በምርጫው ከመሳተፍ በፊትም የምርጫ ምህዳሩ ለሁሉም የተመቻቸ እንዲሆን መታገል እንደሚገባ ይናገራሉ። ይህንን አስተያየት እርስዎ እንዴት ይመለከቱታል?

አቶ ገብሩ፡- “ወደ ምርጫው እንገባለን” በማለት በዚህ ወቅት የተናገረ የለም። መድረክ የምርጫ ቦርድ አዳማ ላይ ባካሄደው ስብሰባ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በመሆን አበክሮ የተከራከረው በዚህ ምክንያት ነው። ቦርዱ “መነጋገር ያለብን በምርጫ ሰላማዊነት ላይ ነው” ሲል እኛ ደግሞ “ከምርጫው ስሌዳ በፊት መደረግ ያለባቸው ነገሮች አሉ” በማለት ብዙ ነጥቦችን ዘርዝረናል። አዳማ ላይ ሆነን ከ66 ፓርቲዎች ውስጥ 34 ፓርቲዎች በመሰባሰብ ተፈራርመን አዲስ አበባ ከተመለሰን በኋላ ጊዜያዊ ኮሚቴ በማቋቋም ጥያቄያችንን አቅርበናል። ከዚህ ውጪ በምርጫው እንሳተፋለን የሚል አቋም ላይ አልደረስንም።

ጥያቄ፡- ዞሮ ዞሮ ለምርጫ ቦርድ ያስቀመጣችሁት ቅድመ ሁኔታ አለ። ያስቀመጣችኋቸው ጥያቄዎች ምላሽ ካላገኙ የምታሳልፉትና የምትወስዱት እርምጃ ምንድን ነው?

አቶ ገብሩ፡- እንደ አንድ ዲሞክራቲክ ተቋም ምርጫ ቦርድ ራሱን መለስ ብሎ ይመለከታል የሚል እምነት አለኝ። በግሌ ተቋሙ የቀረቡለት ጉዳዮች የአገር ጉዳይ በመሆናቸው መለስ ብሎ ይመለከታቸዋል የሚል እምነት አለኝ ይህንን ነገር ባያደርግ የምንወስደውን እርምጃ ደግሞ የምናሳውቀው ጊዜው ሲደርስ ይሆናል።

ጥያቄ፡- አቶ ገብሩ የማስተርስ መመረቂያ ጽሁፎን ሲሰሩ በኢትዮጵያ ምርጫ ስርዓትና ችግሮች ዙሪያ ሰፊ ጥናት ማድረጎን እናውቃለን። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያን ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ መስመር ለማስገባት ምን ማድረግ ይበጃል ይላሉ?

አቶ ገብሩ፡- የማስተርስ መመረቂያ ጽሁፌን የሰራሁት ኢትዮጵያ የምትከተለውን የምርጫ ሲስተም በመመልከት ነው። ኢህአዴግ ቀደም ብሎ ከጫካ ሲገባ ራሱን ስልጣን ላይ ማቆየት የሚችል የምርጫ ስርዓት ለመከተል ፈልጓል። ስለዚህ ይህንን ስርዓት ይዞት መጥቷል። በነገራችን ላይ ፈረንጆቹ The winer takes all “አሸናፊ ሁሉንም ይወስዳል” የሚሉትን የምርጫ ስርዓት ነው በአሁኑ ሰዓት እኛ እየተከተልነው የምንገኘው ይህ የምርጫ ሲስተም አንግሎ ሳክሰን የሚል መጠሪያ አለው። ሌሎች የምርጫ ስርዓቶች ደግሞ “ተመጣጣኝ” እና “ድብልቅ ተመጣጣኝ” የሚሰኙ አሉ። የምንከተለው የምርጫ ሲስተም በግልጽ ለህዝብ ቀርቦ ከዚህኛው ይሄኛው የተሻለ ነው በሚል ይሁንታ ያገኘ አይደለም። በአንድ አገር ፖሊሲዎች የሚወጡባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ። እዚህ ሂደት ውስጥ አልፈው በመጨረሻም ውጤት ሆነው ይወጣሉ። ሌላው ግሩፕ ታጉሪ የሚሰኘው ነው። ሦስተኛ ወጥ ከፍተኛ ግምት የሰጠሁት ኤሊት ቲጉሪ ይሰኛል። ጥቂት ልሂቃን ይሰበሰቡና ሃሳባቸውን ይሰጡበታል። የኢህአዴ ፖሊሲ ሦስተኛውን የተከተለ ነው። የኢህአዴግ ቲጉሪ ብቻ ናቸው ፖሊሲዎቹን የሚያወጧቸው ለምሳሌ የመጀመሪያው የፓርላማ አፈጉባኤ አቶ ዳዊት ዮሐንስን ለምንድን ነው ይህንን የምርጫ ስርዓት የተከተላችሁት ተብለው ሲጠየቁ የፖለቲካ መረጋጋትና ቶሉ ወደ ስራ መግባት በመፈለጋችን ነው ብለው ነበር፡፤ ነገር ግን የፖለቲካ መረጋጋት በምርጫ ስርዓት ብቻ አይመጣም። ይህ አንድ ክፍል ብቻ ነው። ለፖለቲካ መረጋጋት የሚያስፈልጉ ወደ 11 የሚጠጉ ነጥቦች አሉ የሽግግሩ ዘመን ቻርተር እኮ ኢህአዴግ ጫካ ሆኖ ጽፎት ያመጣውን ነው በቀጥታ ተግባር ላይ እንዲውል ያደረገው። ቻርተሩን እንዲጸድቅ ካደረጉ በኋላ ዋና ዋና ቦታዎቹን እራሳቸው ተቆጣጠሩት። መከላከያ ውጪ ጉዳይ ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሌሎች ቁልፍ ቦታዎች ወሰዱ። በዚያን ወቅት የነበሩ ፓርቲዎች የኢህአዴን ሂደት የተገነዘቡ አይመስለኝም። እኔ በአንድ ወቅት ኦነጎች ሊወጪ ነው በማለት አንድ ዘመዴ ሲነግረኝ አትወጡ። በማለት ነገርኳቸው። ነገር ግን እነርሱ በጣም ቀላል በመሆኑ እንመለሳለን ማለታቸው ተነገረኝ። ከተመለሱ ጥሩ ግን ከህጋዊ መንገድ መውጣት ብዙ የሚመከር አይደለም። ስለዚህ ኢህአዴግ ብቻውን ወስኖ እኮ ነው የመጣው። ሌሎች ፓርቲዎች ቻርተሩ ሲረቀቅ መሳተፍ ስለመቻላቸው እርግጠኛ አይደለሁም። ኢህአዴጎቹ በተለይም በጣም ቅርብ የሆኑት ከመጀመሪያው ተዘጋጅተው ይዘውት የመጡትን በህዝቡ ላይ ጭነዋል። ነገር ግን ይህ ተገቢ ባለመሆኑ መነጋገር ይኖርብናል። እነርሱ ለምንነግራቸው ነገር ጆሯቸውን ደፍነው አስር ጊዜ የታላቁ መሪያችን ራዕይ ራዕይ እያሉ መናገራቸው ለአገር አይጠቅምም። አቶ መለስ በመቃብሬ ላይ ብቻ ነው እነዚሁ ነገሮች የሚቀየሩት በማለት ሲነግሩን የቆዩትን ዛሬም እኛ በመቃብራችን ላይ ብቻ ማለት ከጀመርን የት ነው የምንደርሰው?

ጥያቄ፡- እንግዲህ ኢህአዴግ ወይም ህወሓት በጫካ ያወጣው የምርጫ ህግ ለ21 ዓመታት የአገሪቱ የለውጥ ጉዞ ላይ እንቅፋት ስለ መፍጠሩ ነግረውናል። ይህንን በምን አይነት መልኩ መቀየር ይቻላል?

አቶ ገብሩ፡- ቅድም ያነሳኋቸው የምርጫ ሲስተሞች የራሳቸው ችግሮች አሉባቸው። አንዳንድ ምሁራን እኛ የምንከተለው የምርጫ ስርዓት ለማጭበርበር ያመቻል ይላሉ። ከዚህ ውጪ የምርጫው ስርአት ችግሮች እንዳሉበት በሂሳብ ስሌት ማሳየት ይቻላል። ለምሳሌ 50,000 ህዝብ ባለበት የምርጫ ጣብያ አቶ “A” የሚባልን ሰው 20,000 ሰው ቢመርጠው አቶ “B” ደግሞ 18,000 ሰው ቢመርጠውና አቶ “C” በ12,000 ሰው ቢመረጥ፤ አቶ“A” አሸናፊ ይሆናል። አቶ“A”ን ያልመረጡት ሰዎች ድምፅ ግን 30,000 ይመጣል። ነገር ግን አሸነፈ የሚባለው 20.000 ድምጽ ያገኘው ነው። የአንግሎ ሳክሰን የምርጫ ስርዓት ትልቁ ችግር ይህ ነው። ይህንን በውል መረዳት ይኖርብናል። ዴሞክራሲውን ኢህአዴግ እኮ ከመጀመሪያው አልፈለገውም። ለምዕራባዊያኑ ደጅ መጥኚያነት ለማቅረብ እንጂ ከልቡ አይደለም። ተዘጋጅቶበት የመጣውም ከዚህ አንፃር ነው። ህገ መንግስቱ ውስጥም ቢሆን ብዙ ችግሮች አሉ። እኛ ከኢህአዴግ ጋር ስንደራደር ለማንሳት ሞክረናል። “ህገ መንግስቱንና ሌሎች ከህመንግስቱ ጋር መሄድ ያልቻሉትን እንዴት ትፈታለህ?” በማለት ጠይቀናል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ግን ጠንክሮ ከመታገል ውጪ የተለየ አማራጭ የለም። ወጣቶችን ማደራጀትና ህዝቡን ማንቃት ያስፈልገናል። የምናፈራው ወጤት ዝም ብሎ ኮፒ መሆን የለበትም። እኛ ያልነውን ብቻ የሚቀበል ሳይሆን አንብቦ ተረድቶ ውጦና ሰልቅጦ ነገሩን በደንብ አውቆት በራሱ የሚተማመን ውጤት መምጣት አለበት።

ጥያቄ፡- የምርጫው ስርዓት ለአንድ ወገን በሚጠቅም መልኩ ተዘጋጅቷል፤ ነገር ግን የህዝቡ ድምፅ እንዲበታተን በማድረግ ረገድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ አሸን መፍላትስ አስተዋፆ አላደረገም? ለምንድን ነው አንድ አይነት የፖለቲካ አላማ ያላቸው ፓርቲዎች

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# በሙት "ሌጋሲ" የተዋጡት ጠ/ሚኒስትር

ብስራት ወ/ሚካኤል

afrosonb@gmail.com



ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ያደረጓቸውን በርካታ አሉታዊ ነገሮች ለመጥቀስ በቂ ጊዜና ቦታ ባይኖራቸውም ሰውየውን "መልአክ" ለማስመሰል ኢቴቪ እና ሌሎቹም የመንግስት የፕሮፖጋንዳ ማሽኖች የተለያየ ሙከራ አድርገዋል፡፡ መለስ ሲሞቱ ኢህአዴግ በራሱ መቆም እስከማይችል ድረስ በመለስ ተክለ ስብእና ተከልሎ መኖሩን የሚያረጋግጡ ክስተቶች ተስተውለዋል፡፡ ለዚህም አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃ/ማርያምን በዋቢነት ማየት በቂ ነው፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በ47 ዓመታቸው ራሳቸውን መሆን የቻሉ አይመስሉም፡፡ ስለዚህ ተፈጥሯዊውን ትክክለኛ ሰው ለመፈለግ በፋኖስ እንደባከነው ፈላስፋ እኛም ጧፍ አሊያም ሳምባዲና ይዘን ትክክለኛውን ኃ/ማርያም ደሳለኝን ለመፈለግ መገደዳችን አይቀርም፤ ራሳቸውን ሆነው ስናገኛቸውም "ኢዮሪካ" እንላለን፡፡ በተለይ የማይሞቱ ይመስሉ የነበሩት መለስ ከዚህ ዓለም መሰናበት ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ አቶ ኃ/ማርያም ራሳቸውን ሆነው መቅረብ አልቻሉም፡፡ ለዚህም ማረጋገጫ ይሆነን ዘንድ ጥቂት ማሳያዎችን እንምዘዝ፡፡

## ከንቱ መወድስ

የአቶ መለስ ሞት ይፋ ከተደረገ በኋላ በወቅቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ኃ/ማርያም እንደሟቹ የፈንጅና የቦንብ ጢስ እንዲሁም የጥይት አረር ያላሸተቱ በመሆናቸውና በኃይማኖት የታነፁ መሆናቸው ከአቶ መለስ በተሻለ ሊያስተዳድሩ እንደሚችሉ ይወራላቸው ነበር፡፡

ሰውየው በኃይማኖት ረገድም "የሐዋርያት እምነት" ተከታይ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ይገለፃል፡፡ ይሄንንም እሳቸው በአንድ ወቅት "ምዕራፍ" ከሚባል መጽሄት ጋር ባደረጉት ቆይታ አረጋግጠዋል፡፡ እርሳቸው በሚከተሉት ኃይማኖት ዘወትር የሚደመጥ የክርስቶስን ከፍ የሚያደርግ መወድስ አለ፤ "ዘላለማዊ ክብርና ለኢየሱስ" የሚል፡፡ ጠንካራ ኃይማኖተኛ ናቸው የሚባሉት አቶ ኃ/ማርያም በቤተዕምነታቸው የለመዷትን ቃል ዘለዓለማዊ ላልሆኑት ለሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ያላቸውን አድናቆት ለመግለጽ ቃላት ቢያጥራቸው "ዘለዓለማዊ ክብርና ሞገስ ለመለስ" የሚል ከንቱ መወድስ አቅርበው አረፉት፡፡ ይህ ንግግር ሰውየው ክርስቶስን ከመለስ ጋር መሳለመሳ ያስተካከሉበት ነበር፡፡ አምላካዊ መወድስን ለፖለቲካ ሽቀጥ ማዋላቸው በርካታ ክርስቲያኖች ቅር ከማሰኘቱም ሌላ የአቶ መለስ አምላኪ አስመስሏቸዋል፡፡

## "የእምባ አድርቅ" መፅናኛ

የሟቹ ግብዓተ መሬት እንደተፈፀመ በባለስልጣናቱ ከተረጋገጠ በኋላ ያኔ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትር የተባሉት አቶ ኃ/ማርያም ለህዝቡ በተናጥል በሚመስል መልኩ የእምባ አድርቅ መፅናኛ ግብረ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እዚህ ላይ "እምባ አድርቅ" የሚባለው የሟች ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ ለሐዘንተኞችም ይሁን ልቅሶ ሊደርሱና ሊያፅናኑ ለመጡ እንግዶች የሚሰጥ የሚበላና የሚጠጣ ነገር ነው፡፡ የዚህ መፅናኛ ግብረ መልስ ደግሞ ሊያፅናና የመጣውን አሊያም ለሐዘንተኞቹ (ለሟች ቤተሰቦች) መልካም መፅናናትን ለተመኙ የሚሰጥ የ "እናመሰግናለን" ምላሽ መልዕክት ነው፡፡

ያኔ አቶ ኃ/ማርያም ድርጅታቸው ኢህአዴግንና "መንግስትን" ወክለው አስገራሚ የሆነ የእምባ አድርቅ መፅናኛ ግብረ መልስ ንግግር አድርገዋል፡፡ ነሐሴ 28 ቀን 2004 ዓ.ም የአቶ መለስ ብሔራዊ ሐዘን መጠናቀቁን ይፋ ባደረጉበት ወቅት "የተከበራችሁ አምባሳደሮች፣ የተከባራችሁ በሰላማዊ ትግል በሀገር ውስጥ ያላችሁ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ የተከበራችሁ የጐዳና ተዳዳሪዎች . . ." ብለው ያልተገባ ዝርዝር ነገር መናገራቸው ግርምትን ፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል፡፡ አቶ ኃ/ማርያም ከውጭ ዲፕሎማቶችና መሪዎች ውጭ ያሉትን ኢትዮጵያውያን "የተከበርከው የሀገራችን ህዝብ" ማለት ተስኗቸው ሳይሆን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማማለል ያደረጉት የየዋህ ሙከራ ነበር፡፡

እዚህ ላይ አቶ ኃ/ማርያም "የጐዳና ተዳዳሪዎች" ብለው ማመስገናቸው "አዲሱ ሰውዬ የተጣለውንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያስታውሱ ናቸው" የሚል አስተሳሰብ ለመፍጠር ያቀናበሯት ነች ፡፡ እዚህ ላይ ማንም ሰው ወዶና ፈቅዶ የጐዳና ተዳዳሪ መሆን የሚፈልግ እንደሌለና ይልቁንም "ባለዕራዕይ መሪ" እያሉ በሚያሞካሹዋቸው ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም አባሎቻቸው በፈጠሩት "የመንግስት ሌቦች" ስርዓት ዜጐች ለጐዳና ተዳዳሪነት ህይወት እንደበቁና እየበቁ እንዳለ የገባቸው አይመስልም፡፡ የዛሬው ጠቅላይ ሚኒስትር ያኔ አቶ መለስ በየመድረኩ ለሰው ልጆች ክብር ያላቸው ለማስመሰል "የተከበራችሁ ወጣቶች፣ የተከበራችሁ ሴቶች፣ የተከበራችሁ ወንዶች፣ አረጋውያን አዛውንቶች፣ የተከበራችሁ የድርጅታችን አባላትና የልማት ሰራዊት . . ." ያሉትን የኮረጁት አቶ ኃ/ማርያም ምስጋና ሲደረድሩ አምሽተው ነበር፡፡





## ከአስኬማ አልባ ክህነት በኋላ

እውነት ለመናገር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ሀገሪቱን ለመምራት በድርጅታቸው ኢህአዴግ አመራሮች ፈቃድ ከነ ሙሉ ክብራቸው፣ ጥቅማቸውና ግዴታቸው ጋር በጠ/ሚኒስትርነት ተሹመዋል ማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በጠቅላይ ሚኒስትርነት ከተሾሙ በኋላም ራሳቸውን ሆነው ከመገኘት ይልቅ ሟቹን ለመምሰል ሲጥሩ እየተስተዋለ ነውና፡፡ በተደጋጋሚም "የአቶ መለስን ራዕይ እናሳካለን፣ እሳቸው የጀመሩትንና የወጠኑትን በሙሉ እናስፈፅማለን" እያሉ የሚጠበቅባቸውን የራሳቸውን ተሰጥዖና ድርሻ ተግባር ላይ ለማዋልም ሆነ አሻራቸውን ለማኖር የተዘጋጁ አይመስሉም፡፡

አቶ ኃ/ማርያም በሙት መንፈስ በመመራት ጥሩና መጥፎውን ሳይለዩ እንደወረደ እንደሚያስፈፅሙ በይፋ በየመድረኩ መግለፃቸው የተሰጣቸው ስልጣን ምሉዕ እንዳልሆነና በሌጋሲ ማስፈፀም ሰበብ ከጀርባ ሆኖ የሚመራ ዋነኛ አካል እንዳለ ሳያቁት አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ስልጣናቸው አስኬማ አልባ ክህነት ሆኗል ማለት ነው፡፡

ኃ/ማርያም በጠቅላይ ሚኒስትርነት ከተሾሙ በኋላም ራሳቸውን መሆን እንዳልቻሉ በቅርቡ በፓርላማ የመንግስትን አቋምና በማብራራት በቀረቡበት ወቅት አንፀባርቀዋል፡፡

በወቅቱ ፓርላማ ውስጥ ሆነው አቶ መለስ ያደርጓቸው የነበሩት እንቅስቃሴዎች፣ ቃላትና ንግግር ላየ አቶ ኃ/ማርያም መለስን መስለው እንደተወኑ ለመረዳት አይቸገርም፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት ጥያቄ ከቀረበላቸው በኋላ መልስ ሲሰጡ በንግግር ወቅት የፊት አዟዟራቸው፣ የማጅራታቸውን ቀኝ ጐን መዳበሳቸው፣ መነፅራቸውን በተደጋጋሚ ከፍ ለማድረግ መሞከራቸው፣ የመብት ጥያቄን አንስተው በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ የሚያቀርቡትን በመፈረጅና በማስፈራራት "እሳት እንደመንካት ነው" በማለት አቶ መለስን ሆነው ተውነዋል፡፡

ልክ እንደ አቶ መለስ በፓርላማ ከፈረዱና ካስፈራሩ በኋላ በወሎ ገርባ አካባቢ ኃይማኖታዊ የመብት ጥያቄ ያነሱ የሙስሊም ማኅበረሰብ ላይ ያለፍርድ ቤት ሞት በመበየናቸው ዜጎች ህይወታቸው አልፎአል፤ የቆሰሉም አሉ፡፡ አቶ መለስ የሽግግር መንግስቱ ፕሬዘዳንት እንደሆኑ በ1985 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው የተገደሉ፣ የቆሰሉ፣ የተሰወሩ እንደነበሩ አይዘነጋም፡፡ አቶ ኃ/ማርያምም ወደ መንግስት መሪነት ብቅ ካሉ ጀምሮ ድሮ ከሚታወቁበትና ከሚነገርላቸው ከራሳቸው ሙሉ ስብዕና ወጥተው በቁም እያሉ ሟቹን ሆነው እየታዩ ይገኛሉ፡፡

በርግጥ መልካም ተሞክሮንና ድርጊትን ወስዶ ከራስ ጋር ማስማማት ብልህነት ቢሆንም አቶ ኃ/ማርያም ግን ከነ አሰስ ገሰሱ አቶ መለስን ለመሆን መሞከራቸው ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍላቸው ይችላል፡፡ አሁን ባለው አካሄድ አቶ ኃ/ማርያም ራሳቸውን ሳይሆን ሟቹን አቶ መለስን ለመሆን መሞከራቸው በሙት ጥላ ስር እንዲወድቁና ማንነታቸውን እንዲጥሉ ያደረጋቸው ይመስላል፡፡ ይህ ሂደት የሚቀጥል ከሆነ የራስ ማንነት ቀውስ (personal identity crisis) ውስጥ በመግባት ከፍተኛ የጤና መቃወስ ሊገጥማቸው ስለሚችል ከአሁኑ አስበውበት ራሳቸውን ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ለማንኛውም አቶ ኃ/ማርያም ራሳቸውን እስኪሆኑ ድረስ በመለስ "ሌጋሲ" ውስጥ ተሰውረው ከመኖር ውጪ አማራጭ የላቸውም፡፡

## በምርጫው እንሳተፋለን የሚል . . . ከገፅ 9 የዞረ

ወደ አንድነት መምጣት ያልቻሉት?

<u>አቶ ገብሩ</u>፡- ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ትልቅ አስተዋጾኦ አድርጓል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መብዛት አንዳንዶቹ እንደውም ከአንድ ሰው በስተቀር ከኋላቸው ሰው የሌላቸው ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በተነሳው ንፋስ ተጠቅመው የተመሰረቱ ነገር ግን የረባ ነገር መፍጠር ያልቻሉ ናቸው፡፡ ኢህአዴግ ፓርቲዎቹ እንዳይሰባሰቡና እንደተበታተኑ እንዲቀሩ ታትሮ ሰርቷል፡፡ እንዴት አድርጌ መካከላቸው ልግባ ማለቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ አሁን መድረክን የገጠመውም ይህ ነው፡፡ መድረክ ሲመሰረት የነበሩ ሁለት ፓርቲዎች ወጥተዋል፡፡ ይህ ለምን እንደተፈጠረ አላውቅም፡፡ ስድስታችን እስካሁን ድረስ ቀጥለናል፡፡ በእኔ እምነት የመድረክ አጠቃላይ ሁኔታ ጥሩ ነው፡፡ እዚህ ደረጃ የደረስነውም ብዙ ነገሮችን በመመርመር ነው፡፡ በቅርቡም የመድረክን ማኒፌስቶ ለማውጣት ዝግጅት ጀምረናል፡፡ የፓርቲዎች መብዛትና መለያየት የህዝቡን ድምጽ መክፈሉ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ ይህንን ነገር ፈጥሯል፡፡ ሊቀናጁ፣ አንድነት ሲፈጥሩና ህብረት ሲመሰርቱ የፖለቲካ ባህላችን መቻቻልንና መከባበርን ባለመልመዱ ሁልጊዜም ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ የእኛ የፖለቲካ ባህል ገና ያልበሰለ ነው፡፡ ሁላችንም ከአንድ ማህበራዊ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ የመጣኝ በመሆኑ የገዢው ፓርቲ ሴራ ተጨምሮበት መበታተኑ ተከስቷል፡፡ የኢህአዴግ ጎሳ ፓለቲካም የፓርቲዎቹን ቁጥር ወደ 100 ቤት እንዲደርስ አድርጓል ስለዚህ እነዚህን ማሰባሰብና በአንድነት ወደ ህዝቡ እንዲቀርቡ ማድረግ አስቸግሯል፡፡

ጥያቄ፡- መንግስት ወይም ኢህአዴግ ከመድረክ ጋር ለመደራደር መጀመሪያ መድረክ የምርጫ ስነ ምግባር አዋጁ ላይ መፈረም ይገባዋል እያለ ነው፡፡ በመሠረቱ የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡን የማዘጋጀት ስልጣን የነበረው ማን ነው?

አቶ ገብሩ፡- ምርጫ ቦርድ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ኢህአዴግ ይህንን የስነምግባር ደንብ ይዞ ከመምጣቱ በፊት ምርጫ ቦርድ የራሱን የስነምግባር ደንብ ጽፎልን መጥቶ ነበር፡፡ እኛ ረቂቁ ላይ አስተያየታችንን በመፃፍ መለስን፡፡ ከዚያ በኋላ ኢህአዴግ ደግሞ ራሱ እንዳመጣው አይነት በማድረግ ይዞት የተነሳው ኢንስቲቲውት ፎር ዴሞክራሲ ኤንድ ኢሌክቶሪያል አሲስታንስ(IDEA) ከተሰኘ የውጪ አገር ተቋም ነው፡፡ እንዲህ አይነት የምርጫ ደንብ አለ እርሱን እንስጣችሁና ተወያዩባት በማለት ያመጣው ፡፡ ይህ ሰነድ በአጠቃላይ ገጽታው ሲታይ ሦስት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ነገሮችን ይዟል፡፡ የምርጫ አስተዳደር፣ የምርጫ ታዛቢዎችን ጉዳይና የምርጫ አስፈፃሚዎችን ጉዳይ ይዟል፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ የምርጫ ስነ መግባር ደንብን አካቷል፡፡ ኢህአዴጎቹ ሁለቱን ብቻ ከዚህ ውስጥ በማውጣት ይዘው መጡ፡፡ እኛ ከፈረንጆቹ ጋር ተነጋግርነው እንዳለ በሁሉም ጉዳዮች አንድንነጋገርበት ነውና አንድ ጉዳይ ላይ ብቻ አንነጋገርም፡፡ ሦስቱም ይጨመሩና ሙሉ በሆነ መልኩ እንነጋገርበት ነው ያልናቸው፡፡ መጥታችሁ አልፈራማችሁም ስነምግባር. . . ስነ ምግባር እያሉ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያደንቁሩት እንግዲህ በዚህ ነው፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ ይህንን አምጥተው ለምርጫ ቦርድ በዚህ መሠረት አድርግ አሉት፡፡ ይህንኑ በመውሰድም ከፓርቲዎች ጋር በመፈራረም ቴሌቭዥንም አመራሮች ሲፈራረሙ አሳዩ፡፡ ነገር ግን የአንድ ሰሞን ወሬ ከሆነ በኋላ አሁን ደግሞ ወደ መድረኩ በማምጣት እየደሰኮሩበት ይገኛሉ፡፡ ይህንኑ ደንብ ምክር ቤት በመውሰድም ህግ አድርገው አውጥተውታል፡፡ ህግ ሆኖ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣ ወዲህ እኛ ሰላማዊ ትግል የምናካሂድ ፓርቲ ስለሆንን በህጉ እየታገዛን ነው የምንሄደው፡፡ ስለዚህ ይህንን ካልፈረማችሁ የሚባለው ምክንያት አንዳንድ ጊዜ "እቃ… እቃ ጨዋታ" ይመስለኛል፡፡ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚመጣም አይደለም፡፡ ዛሬም ከፈለጉ ሦስቱን በመጨመር በቀሩት ላይ መነጋገር እንችላለን፡፡ ምርጫው የተሳካና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን እነዚያን የቀሩትን በማምጣት መነጋገር ተገቢ ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን በአግባቡ ተጠቅሞ ቢያገለግለን ይህ ሁሉ ባልተፈጠረ ነበር፡፡ ትልቁ ችግር ኢህአዴግ ተቋማትን ለማቋቋም እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ ተቋማቱ የተቋቋመበትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጡ ግን አይፈቅድላቸውም፡፡ ምዕራባዊያኑ ተቋማቱ የት አሉ ስለሚሉ ግን ኢህአዴግ ይኸው ተቋቁመዋል በማለት ለፖለቲካ ፍጆታው ይጠቀምባቸዋል፡፡

ጥያቄ፡- ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን አባል እንድትሆን በቅርቡ ተመርጣለች፡፡ አባል መሆኗ የአገሪቱ መንግስት የሰብአዊ መብት አጠባበቁን ስለማሻሻሉ እንደ ማስረጃ መቅረብ ይችላል?

<u>አቶ ገብሩ</u>፡- ሁለት ኢትዮጵያ እያየን ይመስለኛል፡፡ አንደኛዋ ኢህአዴግ እርዳታዎችን ለማግኘት ለፈረንጆቹ የሚያሳያቸው ኢትዮጵያ ነች፡፡ ሀለተኛዋ ደግሞ ባለጉዳዩ ህዝባችን የሚያያትና የሚያውቃት ርሃብ ችግር የበዛባት እስር ቤቶች በጋዜጠኞችና በፓርቲ አባላትና መሪዎች የተሞሉባት፣ የህግ የበላይነት የማይከበርበትና ሰብአዊ መብት የሚረገጥባት ኢትዮጵያ ናት፡፡ ስለዚህ ፈረንጆቹ በጥልቀት ነገሮችን ማየት አይፈልጉም፡፡ ከፈረንጆቹ ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች ስንገናኝ መንግስት የሚያሳያችሁን ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ ያለውን ለመመልከት ሞክሩ እላቸዋለሁ፡፡ አሁን መመረጧ በእኔ እምነት ኮሚሽኑ ውስጥ ኢትዮጵያን እንዲወክሉ የሚደረጉት ሰው ብዙ ነገር እንደሚማሩ ይሰማኛል፡፡ ኢህአዴግ የሚሰራውን ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን በራሱ ላይ ውጤት ይኖረዋል ባይ ነኝ፡፡ የሚወከለው ሰው የተባበሩት መንግስታትን የሰብአዊ መብት ድንጋጌ በደንብ አድርጎ ሊያነብና ሊረዳ "የእኔ መንግስት ልክ አይደለም" በማለት ለመምከር ይሞክራል ወይም በዚያው ሊከዳ ይችላል፡፡ በማለት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

# መንግስት ያመቻቸው የሞት መንገድ

ዳዊት ሰለሞን

**ከገሃነም እሳቱ ማምለጫ መንገድ አጥታ የቆየችው ረሂማ በሰማችው አዲስ ነገር ሁለቱ ጆሮዎቿ እንደ ቀስት ተገተሩ:: ስለ አዲስ አበባ በአለፍ ገደም ከመስማት ውጪ በከተማይቱ የምታውቀው ዘመድ የሌላት ረሂማ ከእናቷ ተማክራ ጥቂት ጥሪት ተቋጥሮላት ለባለቤቷ የጉዞዋን ታሪክ ሳትነግረው ከመንደሯ ልጅ ጋር አዲስ አበባ ገባች**

"መዲና መሐመድ ትባላለች በ15 ዓመቷ ወደ ዱባይ ለስራ ሄዳ አሰሪዋ እግሯ ላይ አሲድ ደፍታባት ከፎቅ ላይ ወርውራ ጥላታለች:: አሁን ዱባይ ሆስፒታል ህክምና ላይ ናት፤ ህክምና በአስቸኳይ ያስፈልጋታል፤ የኢትዮጵያውያንን እርዳታ እየጠየቀች ነው፤ የምትችሉ በዚህ ስልክ 00971557255198 እየደወላችሁ እርዷት::" ይህ ተማፅኖ በቅርቡ በማህበራዊ ድረገፆች በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተሰራጨ ነበር:: መዲና መሐመድ አሁን በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ባይታወቅም እንደርሷ ከ18 አመት በታች ሆነው ወደ አረብ ሀገራት የሚጓዙ ህፃናት ሴቶች በየቀኑ ኢትዮጵያን ለቀው ይወጣሉ:: ህፃናት ሴቶቹ ለስራ ሀገር ለቀው ሲሰደዱ የድርሻውን ገንዘብ የሚያስከፍለው የኢህአዴግ መንግስትን በአፍላ እድሜያቸው ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ወደ አረብ ሀገራት የሚጎርፉት ሴት ህፃናት ጉዳይ ያሳሰበው አይመስልም::

ባለፈው አመት የካቲት ወር መላውን አለም ያስደነገጠ ዘግናኝ ዜና ከወደ ሊባኖስ ተደምጦ ነበር:: አለም ደቻሳ የተባለች ኢትዮጵያዊት የነገ ህይወቷን ለማሳመር በማሰብ እንደ ብዙዎቹ የአገሯ ልጆች የአረቡን አለም ተቀላቅላለች:: ሊባኖሳዊው የአለም ደቻሳ ቀጣሪ ግን ያደረሰባት ግፍ ሳያንስ ከለላ ለማግኘት ከሄደችበት የኢትዮጵያ ኤምባሲ በራፍ ላይ በመኪናው እየጎተተ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ፈጽሞባልታ:: ጥቃቱ የተፈፀመባት ምስኪኗ አለም የሚደርስላት ወገንና ጥብቅና የሚቆምላት መንግስት አጥታ ተስፋ ቆረጠች፤ እናም ህክምና በምትከታተልበት ሆስፒታል በተነጠፈላት አንሶላ ራሷን አንቃ አስከፊውን ህይወቷን በአስከፊ ሁኔታ ደመደመች ::

ለቀሪው አለም ዜናው የሚሰቀጥጥ ይሁን እንጂ በአረቡ ሀገራት ለስራ ፍለጋ የሚያመሩ እህቶቻችን የሚደርስባቸው መራር ጥቃት ለኛ ለአበሾቹ አዲስና እንግዳ ነገር አይደለም:: አስገራሚው ነገር እህቶቻችን ሞት አለበት የተባለውን መካከለኛው ምስራቅ ለመቀላቀል የሚያደርጉት ጉዞ ከፊት ይልቅ በየዕለቱ እየጨመረ መምጣቱ ነው:: ምናልባትም ለኢትዮጵያዊያኑ በአረብ ሀገራት ያለው ሰቆቃ ማባሪያ ስለማጣቱ በዚህ ገጽ ልብ ሰባሪን ታሪኮችን ማስፈር ተገቢ ነው::

ረሂማ ሐሰን ትባላለች፤ ዕድሜዋ 19 የትውልድ ስፍራዋ ደግሞ ሰሜን ወሎ ነው:: ለብዙ ጊዜያት እንዴት ወደ አገሯ ለመመለስ እንደበቃች የምታውቀውና የምትመልሰው ነገር አልነበራትም:: አጋር የተባለ አገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ከኤርፖርት አስተዳደር ጋር በፈጠረው የስራ ግንኙነት ተረክቧት ህክምና እንድታገኝ ከረዳት በኋላ በዙሪያዋ ምን የተፈጠረ እንደሆነ በመጠኑ መለየት ጀምራለች:: ረሂማ ለስራ ካቀናችባት ባህሬን እንዴት ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሰች አሁን የቤተሰብ ያህል እየተንከባከቧት የሚገኙትን የአጋር በጎ አድራጎት ድርጅት ሠራተኞች ተገቢውን እንክብካቤ ማድረጋቸው አሁን ለሚታይባት ለውጥ ትልቁን አስተዋፅኦ አበርክቷል::

ከድርጅቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የረሂማ ዘግናኙ የህይወት ታሪክ የሚጀምረው ከተወለደችበት ቀዬ ነው:: ወላጅ አባቷን በህፃንነቷ በሞት በማጣቷ ከእናቷ ጋር የሦስት ታናናሽ ወንድሞቿን ህይወት የማቆየት ፈተና ወደቀባት:: ዕድሜዋ ለትምህርት ቢደርስም እናት የማጀቱን ስራ እንድትጋራቸው በማሰብ ወደ ትምህርት ቤት ሊሰዷት አልፈቀዱም:: ወንድሞቿ ያገኙትን የቀለም እድል በቤተሰቧ ላይ ያጠላው ድህነት ከእናቷ አለመማር ጋር ተደማምሮ የቀለም ለዛ ነፈጋት:: ረሂማ ተፈጥሮ የደቀነችባት የመጀመሪያው መሰናክል ሴት ሆና መፈጠሯ እንደሆነ ታስባለች:: ይህንን ደግሞ ማምለጥ አልቻለችምና ተሸነፈች:: ሁለተኛው ፈተናም ይህንኑ ሴትነቷን በመከተል የተደቀነ ነበር:: የ12 ዓመት እንቦቃቅላ ህፃን ሳለች በመኖሪያ ጎጆዋ ከተለመደው ወጣ ያለ ግርግር መለየት ጀመረ:: የመንደሩ ሽማግሌዎች በዚያች ደሳሳ ጎጆ መለስ ቀለስ ማለት አበዙ:: እናትም አባትም አድርጋ የምትመለከታቸውን ወላጅ እናቷን ስትፈራ ስትቸር ምን የተከናወነ እንደሆነ ጠየቀቻቸው "ነገ ሰርግሽ ነው" አሏት:: የሰማቸውን ለማመን ብትቸገርም አማራጭ ስለሌላት አስከፊውን የህይወት ምዕራፍ ከመጀመር ያለፈ አማራጭ አልነበራትም::

የልጅነት ወግ ያላየችው ረሂማ ለሌላ መከራ እናቷ አሳልፈው እንደሰጧት ተረዳች:: ባለቤቷ ከእርሷ በዕድሜ ሦስት እጥፍ የሚበልጥ ጎልማሳ ነው:: በማጀትና በምግብ እጦት የተደቆሰው እንጭጭ ሰውነቷ ቀንበር በመጎተትና በሬ በመጥመድ የደረጃውን የባለቤቷን ሰውነት መቋቋም አልተቻለውም:: የምትመራው ህይወት ከሲኦል ወደ ገሃነም እሳት ተሸጋገረ:: በተለይ አዳሯን አምርራ ተጠየፈችው:: ከሦስት የስቃይ አመታት በኋላ የተጎራበተቻት አንዲት የአገሯ ልጅ ወደ አረብ አገር ለመሄድ ወደ አዲስ አበባ ለማምራት መዘጋጀቷን ሹክ አለቻት:: ከገሃነም እሳቱ ማምለጫ መንገድ አጥታ የቆየችው ረሂማ በሰማችው አዲስ ነገር ሁለቱ ጆሮዎቿ እንደ ቀስት ተገተሩ:: ስለ አዲስ አበባ በአለፍ ገደም ከመስማት ውጪ በከተማይቱ የምታውቀው ዘመድ የሌላት ረሂማ ከእናቷ ተማክራ ጥቂት ጥሪት ተቋጥሮላት ለባለቤቷ የጉዞዋን ታሪክ ሳትነግረው ከመንደሯ ልጅ ጋር አዲስ አበባ ገባች::

ምንም እንኳን ዕድሜዋ 15 አመት ቢሆንም ለእርሷ ግልጽ ባልሆነላት መንገድ ዕድሜዋ 18 ዓመት እንደሞላ ተደርጎ በጎረቤቷ በኩል በተዋወቀችው ደላላ አማካኝነት ፓስፖርት ለማውጣት በቃች:: ወደ አረብ አገር ከሚወስዳት ኤጀንሲ ጋር ያገናኛት ይኸው ደላላ በአዲስ አበባ መጠጊያ ዘመድ እንደሌላት በመረዳቱ ጉዞዋን እንደሚያፋጥንላት ቃል በመግባትና በተለያየ መንገድ በመደለል የወሲብ አምሮቱን ሲወጣባት ከረመ:: የደላላው መጫወቻ የነበረችበት ጊዜ ተገባዶ ወደ ባህሬን አቀናች:: በባህሬን አየር መንገድ ኢትዮጵያዊያን ከተቀበሏት በኋላ ቀጣሪዋ እስኪወስዷት ድረስ ያሟን ኤጀንሲ ቢሮ ውስጥ ለሦስት ቀናት ለማደር ተገደደች:: ከሦስት ቀናት በኋላ የመጣው የረሂማ ቀጣሪ ገና እንደተመለከታት እንዳልወደዳት ባሳያት ብትረዳም አብራው ከመሄድ ውጪ አማራጭ አልነበራትም::

ከኢትዮጵያ ሳትወጣ የተነገራት ልጅ የሌላቸው ባለትዳሮች ቤት እንደምትገባ ቢሆንም የመጀመሪያውን ቀን ያሳለፈችው ስድስት የቤተሰብ አባላት ባሉበት ቤት ውስጥ ነበር:: ቀጣሪዋ በእጇ የሚገኘውን ፓስፖርት በመረከብ በአንድ ሳጥን ውስጥ ሲቆልፍባት ተመልክታለች:: የቀጣሪዋ አባት፣ ወንድምና እህት በየተራ እየተቀባበሉ እየወሰዷት የመኖሪያ ቪላቸውን እንድታፀዳ፣ ምግብ እንድታበስልና ልብሶቻቸውን እያጠበች እንድትተኩስ ያደርጓት ጀመር:: እነዚህ ስራዎች ለእርሷ እንግዳ በመሆናቸው የተነሳ የምትፈጽማቸው ስህተቶች ድብደባ፣ ስድብ፣ የደሞዝ ቅጣት እንዲደርስባት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: በአንድ ማለዳ ያጋጠማት ለየት ያለ ነገር ግን በአዲስ አበባ ለመገኘቷ ምክንያት ሆኗል::

ከመጀመሪያው ዕለት አንስቶ የተፈታ ፊት ሊያሳያት ያልፈቀደው ቀጣሪዋ ለጊዜው ትዝ በማይላት ጥፋት የተነሳ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ወደ ውጪ ገፍትሮ ይጥላታል:: በአደጋውም ጥርሷ እረግፏል፤ እጆቿ እና አንድ እግሯ ተሰብረዋል:: ከሁሉም በላይ ህሊናዋን ለበርካታ ቀናት ስታ ቆይታለች:: ወደ አገሯ የተሸኘችውም በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ነው:: አሁን ረሂማ በህክምና ጥበብ የተሰሩ ጥርሶች ተገጥመውላታል:: የተሰበሩት እጆቿ እና እግሯ መንቀሳቀስ ጀምረዋል:: የወላጅ እናቷንና የትውልድ መንደሯን ስም ደጋግማ ታነሳለች:: ነገር ግን በፍፁም ወደ ሰሜን ወሎ የመመለስ ፍላጎት የላትም::

ይህ አይነቱ ታሪክ የረሂማ ብቻ አይደለም፤ ሆኖም አዳዲሶቹ የአረብ አገራት ተጓዥ ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች ሊያጋጥሟቸው እንደሚችል ቢያውቁም የሞቱን መንገድ ወደ ጎን ለመተው አልፈቀዱም:: እናም ባገኙት አማራጭ ሁሉ ወደ አረብ ሀገራት ይተማሉ:: የኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤት በሦስት ቀናት ዕድሜ ፓስፖርት ለሚጠይቀኝ አቀርባለሁ በማለት እንዳልፎከረ በአሁኑ ሰዓት ጠያቂዎቹን ከሦስት ወራት በላይ መቅጠር ግድ ብሎታል:: የዚህ መንስኤው ደግሞ የአረብ አገራት ተጓዦች ቁጥር አስደንጋጭ በሆነ መልኩ በብዙ እጥፍ መጨመሩ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ::

## ዘመናዊ የኮንትራንት ባርነት

ኢትዮጵያውያን እንደ አገር የምንኮራበት በቅኝ ያለመገዛት ታሪካችን በዘመናዊ የኮንትራት ባርነት ከተደረፈ ረዘም ያሉ አመታት ተቆጥረዋል:: ባለፉት አስርት አመታት በመካከለኛው ምስራቅ የተገኘው የነዳጅ ዘይት ሀብት አገራቱን በኢኮኖሚ እንዲመነደጉ አብቅቷቸዋል:: በአረብ አገራት የሚገኙ ዜጎች ከነዳጅ ሀብቱ ተካፋይ መሆናቸውም ዝቅተኛ ተብለው በሚወሰዱ ስራዎች ላይ ለመሰማራት ያላቸውን ተነሳሽነት ገድሎታል:: የስራ ዕድል በስፋት ባልተፈጠረባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ አገራት የሚኖሩ ሴቶች በአረቦቹ የተናቁ ስራዎችን ለመስራት አጋጣሚውን እንደ መልካም ዕድል በመቁጠር መትመም ጀመሩ:: የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነም በአረብ ሀገራት ከ200,000(ከሁለት መቶ ሺ.ህ) በላይ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ይገኛሉ:: ከነዚህ ውስጥ ከ95% በላይ የሚሆኑት የተሰማሩ በቤት ሠራተኝነት ነው::

ምንም እንኳን ኢትዮጵያዊያኑ የቤት ሰራተኞች በዋናነት ወደ ኩዌት፣ ጆርዳን፣ ሳውዲ አረቢያና ሊባኖስ የሚያቀኑት በህጋዊ መንገድ ቢሆንም በቀጣሪዎቻቸው መብቱ ሊከበርለት እንደሚገባ ሠራተኛ ሳይሆን እንደ ባሪያ መታየታቸው አልቀረም:: ገና የቀጣሪዎቻቸውን ቤት እንደረገጡ ፓስፖርታቸው ይወሰዳል፣ ከወሰዳቸው ኤጀንሲ ወይም ከቤተሰቦቻቸው እንዳይገናኙ ስልኮች ይቆለፉባቸዋል:: ቴሌቪዥኖችን መመልከት እንደማይችሉ ይነገራቸዋል:: ደሞዛቸውን በየወሩ አያገኙም:: የረሂማን ገጠመኝ ማንሳት ለዚህ ማሳያ ይሆናል:: ረሂማ በሀዘንና በቁጭት ተሞልታ "ለአንድ አመት ያህል የሰራሁበትን ደሞዝ አልሰጡኝም" በማለት የደረሰባትን በደል ትተርካለች::

መንግስት ለወጉ ያክል የኮንትራት ውል እንዲሞላ የሚያደርግበት አሰራር ቢኖረውም፣ በተለይ በቀጣሪዎቹ ዘንድ ኮንትራቱ ለመከበሩ የሚከታተልበት መንገድና አቅም የለውም:: ለዚህም በዋንኛው ምክንያት በሚበዙት የአረብ አገራት የኢትዮጵያ መንግስት ኤምባሲዎችን አለመክፈቱ እንደሆነ ታዛቢዎች ያስረዳሉ:: በቆንሲላ ደረጃ የተከፈቱ ቢሮዎችም ለሚፈጠሩ ችግሮች ያላቸው ተደራሽነት ከቁጥር የሚገባ አይደለም::

## ወገኛው ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

በአረቡ አለም በሴት እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ለመቀነስ ይረዳል በማለት ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የተለያዩ መመሪያዎችን በማውጣት በኤጀንሲዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ለማድረግ ሞክሯል:: የኤጀንሲ ፈቃድ በመውሰድ ሴቶቹን ወደ አረብ አገራት የሚወስዱት ደላሎች እውቅና ማግኘት እንደሚገባቸው መመሪያው ከመጥቀሱም ባሻገር ሴቶቹ ኢትዮጵያን ከመልቀቃቸው አስቀድሞ ካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ በመገኘት ጠቃሚ ያላቸውን ትምህርት እንዲወስዱ ያስገድዳል::

መስሪያ ቤቱ ትምህርቱን ለአንድ ሳምንት፣ ለአራት ቀን በመጨረሻም ለሦስት ቀናት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በአሁኑ ሰዓት የትምህርቱን ጊዜ በአንድ ቀን ብቻ እንዲወሰን አድርጓል:: "በአረብ አገር ጉዟቸው ከሚያጋጥማቸው አዲስ ነገር ጋር በፍጥነት እንዲላመዱ ይረዳል" የተባለው ትምህርት በራሱ ብዙ ችግሮችን ያዘለ መሆኑ አስገራሚ ያደርገዋል::

ብዙዎችም ትምህርቱ በዘመቻና በስሜት የተጀመረ እንጂ በቂ ጥናት ያልተደረገበት ስለመሆኑ ይናገራሉ:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶች በአንድ ጠበብ ያለ አዳራሽ ውስጥ እንዲታጨቁ ተደርገዋል:: በሰው ብዛት የተጨናነቀው አዳራሽ በቂ አየር ማስገባት የሚችል ባለመሆኑ በታመቀ አየር ተሞልቷል:: አዲስ ሰው ወደ ውስጥ ሲገባ በቤቱ የታመቀው መጥፎ ጠረን አቀባበል ያደርግለታል:: ሙቀቱና ምቾት የማይሰጠው አጠቃላይ ሁኔታ ሴቶቹ የሚሰጠውን ትምህርት እንዲከታተሉ የሚያስችል አይደለም:: አስተማሪዎቹ ወደ አረብ አገር የሚጓዙ ሴቶች ሊጠቀሟቸው የሚገቡ የንፅህና መጠባበቂያ ቁሳቁሶችንና ሞዴስ እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ያስተምራሉ:: ነገር ግን እነዚህን ቁሳቁሶች ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ባለማዘጋጀቱ አሰልጣኖቹ ከመንገደኞቹ የጥርስ ቡርሾችንና ሳሙናዎችን፣ ሞዴሶችንና ዲዩድራንቶችን "እባካችሁ አንድ ጊዜ ስጡን" በማለት ይለምናሉ:: የትምህርቱ የመጨረሻ ማሳረጊያ በአረብ አገር እንግልት የደረሰባቸውን፣ በአሳሪዎቻቸው በመደፈርና ከፎቆች ላይ ተወርውረው ጉዳት የደረሰባቸውን እንስቶችን ታሪክ የሚያሳይ ነው ዶክመንተሪ ፊልም ነው:: ከገጠሪቱ የአገራችን ክፍሎች የመጡት አብዛኞቹ በአዳራሹ ውስጥ የተገኙት ሰልጣኞች በዚህ ወቅት በመሪር ለቅሶ ይሞላሉ:: ነገር ግን ፊልሙን መመልከታቸው ከጉዟቸው የማስቀረት ጉልበት ያለው አይመስልም:: በዕለቱ ያነጋገርናቸው በዛ ያሉ ሴቶች ጉዟቸው አይቀሬ ስለመሆኑ ነግረውናል::

የሚበዙት ሴቶች ዘመናዊ የመፀዳጃ ቤቶችን አጠቃቀም አያውቁም፣ አልጋ እንዴት መነጠፍ እንዳለበትም ምንም አይነት ልምድ የላቸውም፤ ልብስ ተኩሰውም አያውቁም:: እንዲህ አይነት ሴቶች ከአገር ወጥተው ቋንቋውን ከማያውቁት ቀጣሪ ጋር እንዴት ሊግባቡ እንደሚችሉ ማሰብ በራሱ አዕምሮን ይፈትናል:: ወገኛው ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ግን "እያስተማርኩ ነው" ይለናል::

# አፈናው ከበረታ ገና በ“ፓፒረስ” ላይ እንጽፋለን!

ብሩክ ከበደ

ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ የምዕራባውያኖቹን ቀልብ ለመሳብ የሶሻሊዝም ካባውን በብርሃን ፍጥነት አውልቆ የመናገርና የመፃፍ መብትን “ሲፈቅድ” አስቦበትና ቆርጦ እንዳልነበር በዛወቅትም ሆነ አሁን ፕሬሱ ላይ የሚያደርሰውና እያደረሰ ያለው ችግር በቂ ምስክር ነው፡፡ ለስልጣናቸው መደላደልና ለርዳታ ፍጆታ ሲሉ “ፈቅደናል” ማለታቸው ያፀደቁትንም ሆነ የሕሊናን(equity) ሕግ እንዲደፈጥጡ አስችሏቸዋል፡፡

ሕዝብ የማወቅና የማሳወቅ መብቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲገፈፍ በየወቅቱ የተለያዩ “ውሃ አይቋጥሬ” ምክንያቶች እየተፈጠሩ አፋኝ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በዚህ ተቃርኖአዊ አያያዝም በርካታ ጋዜጠኞች ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ተሰደዋል፣ ራሳቸውን አጥፍተዋል፡፡ ምንም ነገር ባልተሟላለትና በማይሟላለት ነፃ ፕሬስ ዙሪያም ለተሰባሰቡ ጋዜጠኞች ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች ማህበር ከአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀዳሚ የሆነውን ሽልማት ለኢነጋማ (አቶ ክፍሌ ሙላት ይመሩት ለነበረው ማህበር) መስጠቱ በዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ሳይበገሩ ይሰሩ ለነበሩት የነፃው ፕሬስ አባላት እውቅና የሰጠ ነበር፡፡

ሕዝብ እንዲመሩት ይሁንታ ያልሰጣቸው አምባገነን ገዢዎች ከሕዝባቸው የሚነሳውን ጥያቄና ቅሬታ በፍፁም ማድመጥም ሆነ ማንበብ ስለማይፈልጉ፣ እነሱ ብቻ የሚናገሩትና የሚያስቡት በጭብጨባ ፀድቆ በመሳሪያ ኃይል ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ካላቸው ፍላጐት ስላላቸው፣ ለዚህ እኩይ አላማቸው የማይተባበረውን ነፃ ፕሬስ የጦር ያህል ይፈሩታል፡፡

በተለይ በአምባገነኖች ዙሪያ የተኮለኮሉ ሆድ እንጂ ሚዛናዊ ህሊና ያልፈጠረባቸው ግለሰቦችና ቡድኖች በግል ያካበቱት በዘረፋ የተገኘ ሀብት እንዳይነካባቸው ስለሚፈልጉ ዋንኛ የፕሬስ ጠላት ሆነው በፊት መስመር ይሰለፋሉ፡፡ ሟቹ ጠቅላይ ሚ/ር “የመንግስት ሌቦች” ያሏቸው አይነቶች ለዚህ በቂ ማስረጃ ናቸው፡፡

እኚህ ሟች ጠቅላይ ሚ/ር አፋኝ ህጐችንና ደንቦችን የማውጣት ሥራ አይመለከታቸውም እንዳንል ሀገሪቷን ለ21 አመታት ብቻቸውን እንደመሯት ሰዎቻቸው በሚገባ ነግረውናል አሁንም እየነገሩን ነው፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ ለድምፅ ወያኔ ሬዲዮ የተለያዩ ጽሁፎቹን የሚያቀርቡ፣ አዲስ ራዕይ መጽሄትን (ከአሁን በኋላ የምትታተም አይመስለኝም) የሚያዘጋጁ፣ በደርግ ጊዜም አዲስ አበባ ድረስ የፃፉትን መጽሐፍ በድብቅ ልከው ያሳተሙ፣ የኢህአዴግን ፖሊሲና ርዕይ (ራዕይ አይደለም ርዕይ ነው፡፡ የሁለቱ ትርጉም የማይገናኝ ነው)፣ የሪፖርተሩን አማረ አረጋዊን ጨምሮ ለሌሎቹም በረሀ ላይ የጋዜጠኛነት ኮርስ ሰተዋል የተባለላቸው መለስ ዜናዊ የጽሁፍ ነፃነትን የሚገድብ አዋጅና መመሪያ ለምን ያወጡ እንደነበር በርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ሙያው ስለሚያስፈልገው ጥበቃ በቂ ግንዛቤም እየነበራቸው ሆነብለው ፀረ ፕሬስ አቋም ማራመዳቸው የስርአታቸው ገበና በነፃው ፕሬስ አባላት ለህዝብ እንዳይጋለጥ በመስጋታቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰውየው ከሳቸው ውጪ ማንም ልቆ እንዲወጣ ፍላጐት እንዳይወጣ ከነበራቸው ተፅእኖ አድራሽነት የመነጨ ሊሆንም እንደሚችል ለመገመት ይቻላል፡፡

ነፃው ፕሬስ የሀገራችንን ህዝብ የማወቅና የማሳወቅ መብቱና ኃላፊነቱ በየጊዜው ከሚወጡ አዳዲስ የማጥበቢያ ብሎም የማጥፊያ አዋጅና ደንቦች ውጪ ከምርጫ97 በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል ተከርችሞ ቆይቶ እንደገና ብልጭ ቢልም አፈናው ግን አሁንም የሚያሰራ አልሆነም፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ስውር የአፈና አሰራር ምናልባት አቶ በረከት “ከጫካ ጀምረን ምስጢር ጠባቂ ነን” ያሉት ውጤት ሊሆን ይችላልና አንድ ቀን ይፋ እስከሚሆን መጠበቅ ነው፡፡

አሁን ደግሞ ቀ.ኃ.ሥ በ1930 ዓ.ም አጋማሽ ለሀገራቸው እውቀት መዳበር ሲሉ የተከሉትና አሁን በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኘው ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ለፕሬስ አፈና ተጨማሪ ኃይል ሆኖ ብቅ ማለቱ ሁሉንም ወገን ያስገረመ ብቻ ሣይሆን ያስደነገጠ ሆኗል፡፡ ለመሆኑ ፕሬስን በተዘዋዋሪ የማፈን “ድንቅ” ብልጠት የማንትሆን? መቼስ ቻይናዎች ይህቺን አያውቋትም!!

በሟቹ የኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዝዳንትና ታጋይ በነበሩት አቶ አሰፋ ማሞ ባለቤት ሥራ መሪነት የሚመራው ተቋም እንደስሙ “ብርሃንንና ሠላምን” ማምጣት ተስኖት ወደ ፊት በትውልድ ዘንድ አጠያያቂ በሆነ የእንቢተኝነት አቋሙ ፀንቷል፡፡ ተቋሙ ለሕዝቦች የማወቅ መብት በፅናት የቆመ ቢሆን ምንኛ የታደለ ነበር፡፡ ይሄኔ በጮሌዎች የታሸውን ምላሽ እንዲሰጥ የታዘዘው የነጮች ተቋም ቢሆን ኖሮ የሥራ ኃላፊዎቹ ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው በለቀቁ ነበር፡፡ ለዚህ ይሆን በገና ድርዳሪው “እጆቹን ለነጮቹ መስቀሉን ለጥቁሮቹ!” ያለው?

መንግስታዊው የህትመት ተቋም አንዴ “የቆዩ ደንበኞች ሥራ ስላለብኝ አዲሶችን አልቀበልም (ፍኖተ ነፃነት ከድርጅቱ ጋር መሥራት ከጀመረ አመት ሞልቶታል)” ሌላ ጊዜ ደግሞ “ወቅቱ ት/ቤት የሚከፈትበት ጊዜ በመሆኑ በመጽሐፍት ህትመቶች ተወጥሬያለሁ” የሚሉና መሰል ሰንካላ ምክንያቶችን እየሰጠ የሚያፈገፍግበትን ሁኔታ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ም/ሀላፊ አቶ ሽመልስ ከማል ተቀብለው አንፀባርቀውለታል፡፡ “ጐሽ እንዲህ ነው እንጂ” ብለውለታል፡፡

ገዢው ፓርቲ (ኢሕአዴግ) ይኸን ቢያስብም ሳምንታዊው የህትመት ኮታቸው ከሃያ ሺህ በላይ የደረሰው ፍኖተ ነፃነትና (ይኸ ጋዜጣ የፓርቲ ልሳን ነው ቢባልም ነፃ ጋዜጦች በጠፋበት ሀገር እንደ አማራጭ ሆኖ የወጣ ጋዜጣ ነው፡፡ ለዚህም ተፎካካሪ ፓርቲው ሕዝባዊነቱን አረጋግጦበታል፡፡) ፍትሕ ጋዜጣ ራሳቸውን ችለው ማተሚያ መሣሪያ እስከሚተክሉ ድረስ የዲሞክራሲና ፍትህ ነፃነት የተጠማ ህዝባቸውን ጩኸት ሊጋሩ በመጽሄት መልክ ተመልሰው መጥተዋል፡፡ የመጽሄቱ ህትመትም በሌላ ማተሚያ ቤት የሚከናወን መሆኑን አንባቢ ልብ ልትል ይገባል፡፡ በጋዜጣ ከሆነ ከተወሰነ የጋዜጣ ገጽ በላይ ማተም የሚችለው ብርሃንና ሠላም ብቻ መሆኑንም በዚህ አጋጣሚ ልገለጽልህ እወዳለሁ፡፡ የሚገርመው ግን የህዝብ ጉዳይ በጋዜጣ ሆነ በመጽሄት መልክ ቢቀርብ ህዝባዊነቱ ይገፈፋል እንዴ? የምታውቁ ካላችሁ ወዲህ በሉኝ፡፡

ጽሁፌን ከማጠቃለሌ በፊትም ግን አንድ ጉዳይ ማንሳት ፈለኩ፡፡ በሀገራችን ታሪክ የዘመናዊነት መሠረትን የጣሉ፤ ሞታቸው አስደንጋጭ ሆኖ ለህዝባቸው ሳይነገር አደባባይ ሳይታዩ ሦስት ዓመት ሙሉ “አሉ” እየተባሉ የመሩት እምዬ ምኒልክ በዘመናቸው በህትመት ማሽን ሣይሆን በእጅ እየተፃፈ በቤተ መንግስታቸው በጧት ይደረስ እንደነበረው ጋዜጣ ወይንም ከክርስቶስ ልደት በፊት ጥንታውያኖቹ ምስሮች (ግብፆች) በዓባይ ወንዝ ከሚያለሙት ዛፍ መሰል ተክል ግንድ ላይ በሚልጡት ልጥ በሚያዘጋጁት ፓፒረስ የተሰኘ የጽሑፍ ወረቀት መረጃን ለህዝብ ለማቀበል እንገደድም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አንዴ ቁልቁል እንድንወርድ ከተፈረደብን፡፡ ዕድሜ ለሰው ልጅ እውቀትና ዲሞክራሲ ተሚጋች ህዝቦች ሀገራቸው ለዜጐቻቸው ምቹ እንድትሆን ለማድረግ በሚያደርጉት ያላሳለሰ ጥረት ዩቲዩብ፣ ቲዩተር፣ ፌስቡክና ሌሎች ሕዝባቸው የተለያየ ጉዳዮችን እያነሳ የሚወያይባቸው ድረገፆችን ስላበረከቱልን በእጅጉ እያመሰገናቸው ቀደምቱን የጽሑፍ ወረቀት ለፓፒረስን የምንዘነጋው አንሆንም፡፡

ሕዝባችን ሞባይል እንደማይጠቀሙት ሰሜን ኮርያዎች፣ የተለያዩ ማህበራዊ ድረገፆች እንደተነፈጉት ቻይናዎችና፣ በቅርቡ ሞባይል ሲፈቀድላቸው እንደፈነጨት ኩባዎች ወዘተ ከመሆኑ በፊት ራሱን ነፃ ማውጣት ያለበት አሁን ነው፡፡





# ጣይቱ የጠለቀችበት የአዲስ አበባ 125ኛ ዓመት አከባበር

## “ጣይቱ ብጡል የኢትዮጵያዊነት ሐብል”

በብዙአየሁ ወንድሙ

ስለአዲስ አበባ መቆርቆር ስናነሳ ቅድሚያ የምናስታውሰው እቴጌ ጣይቱን ነው፡፡ በመቀጠል እምዬ ምኒልክን . . . እያለ ይሄዳል፡፡ ይህ ያለፈ የአባት እናቶቻችን ታሪክ ነውና ማንም ሊሽረውና ሊቀይረው አይችልም፡፡ በእርግጥ ኢህአዴግ የወደፊቱን የልጆቻችንን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የቀደምት አያቶቻችንን ታሪክ ለመቀየር ሲሰራ ለአመታት ተመልክተናል፡፡ በምትኩም ሌላ ያልነበረን ታሪክ እንደነበር ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ጥሩንም መጥፎውንም ያለፈ ታሪክ በነበረው እውነተኛ ታሪክነቱ መቀበሉ ተገቢ ነው፡፡ ለመጪውም ትውልድ እውነተኛ ታሪክን የማስተላለፍ ግዴታ አለብን፡፡

አመቱን ሙሉ በተደጋጋሚ የምንሰማው ዜና አዲስ አበባ የተቆረቆረችበትን 125ኛ ዓመት ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኗን ነው፡፡ በዓሉ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን የሁሉም አፍሪካዊ በዓል ተደርጐ ሊታይ ይገባል፡፡ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ዋና ከተማም ነችና፡፡ በዓለም የዲፕሎማቶች መቀመጫነትም በ3ኛ ደረጃ እንዳለች ይነገራል፡፡ ይህቺን ተወዳጅና ተፈላጊ ከተማ ለቆረቆሩልን ቀደምቶቻችን ዘለዓለማዊ ክብር ይገባቸዋል፡፡ በንፁህ ኢትዮጵያዊነት ስሜት በተገቢው ጊዜ በተገቢው ሥፍራ ስለቆረቆሩልንም ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ በመነሻዬ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለአዲስ አበባ ከተማ መቆርቆር ትልቁ ድርሻ የእቴጌ ጣይቱና የእምዬ ምኒሊክ እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ይገልፃሉ፡፡

አዲስ አበባ የተቆረቆረቺው ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት በነበሩት ዘመን መንግስት ነው፡፡ ቀደም ሲል የንጉሱ መቀመጫ እንጦጦ ተራራ ላይ ነበር፡፡ ዛሬ በውድ ዋጋ የምንገለገልበት ፍል ውሃ ያኔ እንደማንኛውም ምንጭ ይፈስ ነበር፡፡ በአካባቢው ድንቅ አበቦችም ይበቅሉ ነበር ይባላል፡፡ ከእንጦጦ ወርደው ፍልውሃንና አካባቢውን ለመጐብኘት የመጡት ጣይቱ ብጡል አይተው የማያውቁት ድንቅ አበባ ተመለከቱ፤ አካባቢው ምን ይባላል ብለው ሲጠይቁ የፍል ውሃ በየቦታው ፊን ፊን እያለ መፍሰስ ፊንፊኔ እንደሚባል ተነገራቸው፡፡ የምን ፊን ፊኔ ነው “አዲስ አበባ ነው እንጂ” በማለት ያንን የተመለከተቱትን ድንቅ አበባ አተኩረው እንዳዩ ይነገራል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አካባቢው አዲስ አበባ ተብሎ መጠራት እንደጀመረ ታሪክ ያስረዳል፡፡ እቴጌ ፊንፊኔ አካባቢ እየተዛዋወሩ ሲጐበኙ ሚኒሊክ ሐረር ነበሩ፡፡

እቴጌ ጣይቱ ለአዲስ አበባ ስም ማውጣት ብቻ ሳይሆን ምኒልክ ቤተመንግስታቸውን ከእንጦጦ ወደ አዲስ አበባ እንዲያዞር አቀዱ፡፡ ምኒሊክ ከሐረር ሳይመለሱ በ1879 ህዳር 9 አዲስ አበባ ላይ ቤት አሰርተው ጠበቋቸው፡፡ ምኒሊክም ሲመጡ የቦታውን ምቹነት ከተመለከቱ በኋላ ቤተመንግስታቸው ከእንጦጦ ወደ አዲስ አበባ እንዲወርድ ወሰኑ፡፡ ታላቁን ቤተመንግስት አሰሩ፡፡ አዲስ አበባ ለ125 ዓመት በየጊዜው አዲስ እየሆነች ሄደች፡፡ እነሆ ዛሬ የአገራችን፣ የአህጉራችንና የዓለማችን ድንቅ ከተማ ሆና ቀጥላለች፡፡

እቴጌ ጣይቱ የምትታወቀው አዲስ አበባን ስም በማውጣትና አዲስ አበባ ከተማን በመቆርቆር ብቻ አይደለም፡፡ በጥሩ የቤት እመቤትነት፣ በዲፕሎማሲ ሥራና በጦር አበጋዝነትም ነው፡፡ እቴጌ የምታዘው 3ሺ ሠራዊት ነበራት፡፡ በአደዋ ጦርነት ወቅትም የውጊያ ቀጠና ተስቷት ተዋግታለች፡፡ በተሰጣት የውጊያ ቀጠና የጣሊያን ጦርን ደምስሳለች፡፡ የአደዋ ጦርነት መነሻው የውጫሌው ውል አንቀጽ 17 መፍረስ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ጽንሰ ሐሳብ ኢትዮጵያ ከየትኛውም አገር ጋር ግንኙነት ማድረግ ብትፈልግ በጣሊያን መንግስት በኩል ማለፍ አለበት የሚል ነበር፡፡ ውሉ በእርጋታ ሲታይ የአገሪቱን ሉዓላዊ ነፃነት የሚገፍ በመሆኑ ቁጣን ቀሰቀሰ፡፡ በዚህ ምክንያት የሁለት አገር ተወካዮች ተቀምጠው አንቀጹን ለማሻሻል ተስማሙ፡፡ የኢትዮጵያን ተደራዳሪ ቡድን በመሪነት ይዘው የተቀመጡት ብልሀተኛ ናቸው የሚባሉት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ /አባመላ/ ነበሩ፡፡ የጣሊያን ተወካዮችና የኢትዮጵያ ተወካዮች በአንቀጹ ላይ ለአንድ ሳምንት ተደራደሩ፡፡ በተለይ ጣሊያኖች አንቀጹን አሻሽለን እያሉ የሚያመጡት ሐሳብ ከመጀመሪያው ጽንሰ ሐሳብ ምንም ያልተለየ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ተደራዳሪዎቹ ሊስማሙ አልቻሉም፡፡

እቴጌ ጣይቱ ከሚደነቁበት ባህርያቸው አንዱ ጥሩ የቤት እመቤት መሆናቸው ነው፡፡ እቴጌ ባለቤታቸው አፄ ምኒሊክ ቤታቸው ሲገቡ እንደ ቤት እመቤት ከመቀበልና ከማስተናገድ ውጪ የሥራ ጉዳይ አንስተው የንጉሱን የእረፍት ጊዜ እንዲነካ አይፈልጉም ነበር ይባላል፡፡ የጣሊያንና የኢትዮጵያን ድርድር በቅርብ ይከታተሉ የነበሩት እቴጌ ጣይቱ የተደራደሪው ቡድን አባል ለመሆን ይፈልጋሉ፡፡ ምኒሊክ ቢሮአቸው ሲገቡ እንደማንኛውም ባለጉዳይ አደግድገው ጉዳይ አለኝ ንጉሱን አገናኙኝ ብለው ጠየቁ፡፡ ተፈቅዶላቸው ይገባሉ፡፡ በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ጉዳይ በሚደራደረው ቡድን ውስጥ አባል ሆነው መደራደር እንደሚፈልጉ ንጉሱን ይጠይቃሉ፡፡ አፄ ምኒልክም ፈቅጄልሻለሁ ሄደሽ ተደራዳሪ ይሏታል፡፡ እቴጌ ጣይቱ ሄደው ከተደራዳሪው ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ጣሊያኖች ደነገጡ፡፡ የተለያየ ቃላት እያቀረቡ ተደራዳሪውን አታለው በቀድሞውን መልክ ለማፅደቅ ይሞክሩ የነበሩት ጣሊያኖች እቴጌን በቀላሉ ሊሸውዳቸው እንደማይችሉ ተረዱ፡፡ ይሁን እንጂ ለእቴጌ የተለየ ክብርና ሙገሳ በማቅረብ 8 ቀን ተነጋግረን ልንግባባ አልቻልንም ነበር፤ አሁን ግን እርስዎ በመምጣትዎ መፍትሄ እናገኛለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን በማለት ለመሸንገል ሞከሩ፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ የሄዱበትን መንገድ ሐሳባቸው ምን እንደሆነ እቴጌ ጠየቁ፡፡ ጣሊያኖቹም ሲመልሱ ‹‹አንቀጹ እንዲህ እንዲሻሻል ወይም እንዲህ ተብሎ ተሻሽሎ እንድንስማማ ሐሳብ አቅርበን ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ሊቀበል ባለመቻሉ ልንግባባ አልቻልንም›› በማለት አስረዱ፡፡ ጀግናዋ እቴጌ ጣይቱ አጭርና ግልጽ ውሳኔ ወሰኑ፡፡ “አንቀጹ የሚሻሻልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለውም፡፡ እንድንግባባ ከፈለጋችሁ መፍትሄው አንድ ብቻ ነው፡፡ አንቀጹን ሙሉ በሙሉ አውጥቶ መጣል ነው፡፡ በዚህ የማትስማሙ ከሆነ ድርድሩ እዚህ ይቆማል፡፡” በማለት ተደራዳሪውን ይዘው ተመለሱ፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሠረት የአደዋ ጦርነት ተከተለ፡፡ ጣይቱ ብጡል የድርሻቸውን ተወጥተው ኢትዮጵያ ድል አደረገች፡፡ እቴጌ ጐበዝ ዲፕሎማትም የጦር አበጋዝም ነበሩ፡፡ ከፍተኛ የፖለቲካ ተሳትፎም ነበራቸው፡፡

በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ሆቴል የከፈቱም ናቸው፡፡ ይህ ፒያሳ ላይ የሚገኘው ጣይቱ ሆቴል መንግስት በሙዚየምነት ተንከባክቦ ለሚመጣው ትውልድ ማሳለፍ ነበረበት፡፡ ታሪክን በማጥፋት የሚከሰሰው ኢህአዴግ ጣይቱ ሆቴልን በሙስና በማይመጥን ዋጋ እንደተሸጠ ለብዙ ጊዜ መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ይታወቃል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሆቴሉን የገዙት ባለሀብት የምግብ ዓይነት በሚያሳየው ዝርዝር ላይ የጣይቱንና የምኒሊክን ፎቶ መጠቀም የሚያስመሰግነው ነው፡፡ ምናልባትም ሆቴሉን ታሪኩንና የነበረውን ውበት ይዞ ቢቆይ የገቢ ምንጭ ሊሆነው እንደሚችል ይመከራል፡፡

ሐሳቤን ለማጠቃለል የአዲስ አበባ ከተማ ቆርቋሪ እቴጌ ጣይቱ ልጅ የላትም፡፡ ልጃቸው መልካም ሥራዋና ታሪኳ ነው፡፡ ለሰራቺው ሥራ ውለታ ይገባታል፡፡ ልትዘከር ይገባል፡፡ ጣይቱ ብጡል የኢትዮጵያዊነት ሐብል ናት፡፡ ለዚች ለታላቅ ሴት እስከ ዛሬ በስሟ ሐውልትም አልቆመላትም፡፡ ስለ አዲስ አበባ 125ኛ ዓመት ሲወራ ለዚች ድንቅ ሴት ምንም ሲባል አልሰማም፡፡ እንዲያውም ክብረ በዓሉን ለተራና ለርካሽ ፕሮፓጋንዳ ለመጠቀም ሲሞክር ይሰማል፡፡ ስለዚህ የበዓሉ መክፈቻ ዕለት የጣይቱ ብጡል ሐውልት የሚመረቅበት ቢሆንስ?

# ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አፈና በስተጀርባ?

ዳንኤል ተፈራ

ማክሰኞ ጥቅምት 27 ቀን 2005 ዓ.ም ማታ የእለቱን የዜና እወጃ ተከትሎ አንድ ድንገተኛ ፕሮግራም ከተፍ አለ፡፡ ይሄውም ያለምንም ማስታወቂያ ከተፍ ያለው ዝግጅት ‹‹የዴሞክራሲ ተቋማት ሚናና የአስፈፃሚ ተቋማት ኃላፊነት›› በሚል ርእስ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት የተካሄደ ውይይት ነበር፡፡ የውይይቱ አሰናጅ ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሲሆን አባዱላ ገመዳ አወያይ ሆነዋል፡፡ የስርዓቱ ዋና ዋና ባለስልጣናትም ታድመዋል፡፡ ም/ጠ/ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ የስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይ ፀሃዬ ፣ የኢትዮ ቴሌኮሙ ዶ/ር ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል፣ ‹‹እንባ ጠባቂ›› ወ/ሮ ፎዚያ አማን፣ ዋና ኦዲተር ገመቹ ዱቢሳ፣ ም/ከንቲባ አባተ ስጦታው ከታደሙት መካከል ናቸው፡፡

የውይይቱ መንፈስ ጠቅለል ተደርጎ ሲቀርብም በኢትዮጵያ ውስጥ እግር አውጥቶ ሲራመድ የሚታየውን ብልሹ አሰራር፣ ሙስናና ዝርፊያ እንዲሁም ህዝብ ላይ በሹማምንቱና ስራ አስፈፃሚዎች እየደረሰ ያለውን ማንገላታትና ምሬት ማእከል ያደረገ እንደነበር ለማወቅ ይቻላል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የስርዓቱ ሰዎችንም ያስጨነቃቸው ይመስላል፡፡ ከህዝቡ ጥቅምም በላይ ለሚያልሙት ስልጣናቸው ጎርፍ መሆኑ እንደማይቀር ሳይገለጥላቸው አልቀረም፡፡ ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል የሚሉት አይነት ነው ስብሰባው፡፡

በግሌ ያስደነቀኝ ግን መለስ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ድምፃቸው ተሰምቶ የማይታወቅ ባለስልጣናት አሁን በአደባባይ በድፍረት መናገር መጀመራቸው ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተርና የህወሓቱ አቶ አባይ ፀሃዬ ናቸው፡፡ ‹‹በቅርንጫፍ ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ የሙስና ግንዱ ላይ መረባረብ ነው፡፡ ቅርንጫፉን ብቻ ነክተን የምንተው ከሆነ ለውጥ አይመጣም፡፡መልካም አስተዳደራችንም እየተንፏቀቀ ነው…›› ሲሉ ዝሆን ዝሆን የሚያካክሉ ጠብደል ሙሰኞች በስርዓታቸው ውስጥ እንደመሸጉ እንቅጩን ተናግረዋል፡፡ የመልካም አስተዳደር እጦትና ሙስናውን በየእለቱ የኑሯችን መኮሰስ ላይ የምናየው ስለሆነ ንግግራቸው እውነት ነበር፡፡ የእንባ ጠባቂ ተቋም ወ/ሮ ፎዚያ ህዝብን የሚያስለቅሱ ባለስልጣናትና ስራ አስፈፃሚዎች የህዝብ ብሶት ሲነሳባቸው ከፍ ዝቅ አድርገው እንደሚልኳቸውና ‹‹ምን ታመጣላችሁ!›› በማለት እንደሚያባርሯቸው በድፍረት ተናግረዋል፡፡

**የስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተርና የህወሓቱ አቶ አባይ ፀሃዬ ናቸው፡፡ ‹‹በቅርንጫፍ ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ የሙስና ግንዱ ላይ መረባረብ ነው፡፡ ቅርንጫፉን ብቻ ነክተን የምንተው ከሆነ ለውጥ አይመጣም፡፡መልካም አስተዳደራችንም እየተንፏቀቀ ነው…›› ሲሉ ዝሆን ዝሆን የሚያካክሉ ጠብደል ሙሰኞች በስርዓታቸው ውስጥ እንደመሸጉ እንቅጩን ተናግረዋል**

በአጠቃላይ የኢትዮጵያውያንን የኑሮ ጫናና የህዝቡ መነሳቀል ምክንያት ምን እንደሆነ የተካሄደው የባለስልጣናቱ ውይይት ማክሰኞ ማታ ሲቀርብ ተከታትፎ ነበር፡፡ ለምን ተከታተሌ አንልም፤ ራሳቸው የሰሩት ስለሆነ፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ‚ዎ የማክሰኞውን የኢቲቪ ድንገተኛ ዝግጅት ሲከታተል ያስታወሰው ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም ዜና ላይ ይሄው ውይይት ተቀንጭቦ መቅረቡን ነበር፡፡ እሁድ ጥቅምት 25 ቀንም ሙሉው እንደሚቀርብ ማስታወቂያ ተለፍፎለታል፡፡ እንደተባለው እሁድ የኑሮ ሸክም የበዛብንና የብልሹው አስተዳደር ምሬት እየተፋን ያለን ሁሉ አሰፍስፈን ብንጠብቅም በማስታወቂያው መሰረት ሊቀርብ አልቻለም፡፡ አንዲት ባለቀጭን ድምፅ ጋዜጠኛ ቀርባ ይቅርታ በመጠየቅም እንደማይተላለፍ አረዳችን፡፡ ለምን?

ረቡዕ ህዳር 5 ቀን 2005 ዓ.ም የወጣችው ሰንደቅ ጋዜጣ የባለስልጣኑ ውይይት ማስታወቂያ በተነገረበት ቀን ቀርቶ ለምን የአሜሪካ ምርጫ በሚጧጧፍበትና የብዙዎቻችን ቀልብ ባልተሰበሰበበት ማክሰኞ ማታ ያውም በድንገት ተላለፈ? ስንል ለነበርን ሁሉ እንደ ሰንደቅ ጋዜጣ መልሱ ‹‹የባለስልጣናቱ ውይይት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተቆራርጦ ባልታሰበ ሰዓት ቀረበ›› ይለናል፡፡ ‹‹ሳንሱር›› ተደርጎ ማለት ነው፡፡ የኢህአዴግ ባለስልጣናትም በንዴት ቡን ብለው የኢቲቪ ሹማምንትን ማብራርያ እንደጠየቁ ከጋዜጣዋ አንብበናል፡፡ ኦኦኦ. . .ግሩም ነው፡፡

ከዚህ በፊት እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተቃዋሚዎች በሚያሰናዱት ፕሮግራምም ሆነ መግለጫ ላይ ቀርቶ አያውቅም፡፡ ከመጀመርያው እስከ መጨረሻው የቀዳውን ፕሮግራም ግን ወስዶ መደርደርያ ላይ ያስቀምጠዋል ወይም ለሌላ አካል ያቀብለዋል፡፡ ትንሽ ደግ ከሆነ ደግሞ ትንሸዬ ቆርጦ በሦስት ሰዓቱ ዜና ላይ ያቀርበዋል፡፡ በእርግጥ የባለስልጣናቱ ውይይት የተቆረጠበትና የተቃዋሚዎች መግለጫ የሚቆረጥበትን መንገድ ማወዳደር ተገቢ አይደለም፡፡ እናቱ ገበያ የሄደችበትና እናቱ የሞተችበት እኩል ያለቅሳል ይሆንብናል፡፡ የባለስልጣናቱ ውይይት በአንፃሩ ሰፊ ሽፋን አግኝቶአልና፡፡ ኢቲቪ የባለስልጣናቱን ውይይት ያፈነበትና የቆራረጠበት ዜና ከሰንደቅ አንብበናል፡፡ እኛ ደግሞ ከአፈናው ከበስተጀርባ ምን እየተሰናዳ ነው? እንላለን፡፡ ከኢቲቪ አፈና ጀርባስ ምን አለ?

ቀለል ያለ መላምት አንድ፡- የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር የሆኑት አቶ በረከት ስምኦን በቅርብ ርቀት በሚቆጣጠሩት ኢቲቪ በኩል የጉልበት ፍተሻ እያካሄዱ ይሆን? ማለትም በህወሓትና ብአዴን መካከል ያለውን ፍጥጫ የሚያመላክት ይመስላል፡፡ ብአዴኖች ህወሓቶች ላይ ያላቸውን ጉልበት ለማሳየት ተፈልጎ ይሆናል ማለት ነው፡፡ መቼስ ኢቲቪ በራሱ የባለስልጣናቱ ወቅታዊ ውይይት ላይ ማጉላላት ሲፈጽምና የመተላለፊያ ሰዓቱን እንደፈለገው ሲያደርግ የብሮድካስት ወይም ኤዲቶርያል ፖሊሲውን ተከትሎ ነው ብሎ ማሰብ አጉል የዋህ መሆን ነውና፡፡ ከዚህ በፊትም ኢቲቪ የሚታወቀው እንደዚህ አይነት የባለስልጣን ውይይቶችን በተደጋጋሚ እስኪታክተን በማራገብ ነበርና፡፡

አልያም በመላምት ሁለት ስንመለከተው የኢቲቪ ኃላፊ የሆኑት የህወሓት ሰው ጉልበታቸውን ለማሳየትም ይሆናል፡፡መለስ በነበሩ ጊዜ ከነበረው አሰራር ለየት ባለ መልኩ ባለስልጣናቱ ‹‹ሙሰኞችን እናውድም፣ ፀረ-መልካም አስተዳደሮችን እንመንጥር›› ማለታቸው አዲስ ሆኖባቸውም ሊሆን ይችላል፡፡ ማን ያውቃል ኢቲቪ ከዳንሰኞች አንዱ ይሆን እንዴ?





# የአንድነት ብሔራዊ ም/ቤት ለሁለት ተከታታይ ቀናት ከፍተኛ ግምገማ አካሄደ

## -ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ወደ ትግሉ ተመልሰዋል

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ብሔራዊ ም/ቤት ለሁለት ተከታታይ ቀናት ባደረገው ስብሰባ ከፍተኛ ግምገማ ማከናወኑን ከብሔራዊ ም/ቤቱ ያገኘነው መረጃ አመለከተ፡፡

ከም/ቤቱ ባገኘነው መረጃ መሠረት “የፓርቲው ሊቀመንበር ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የፓርውን የስምንት ወር የሥራ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ የፓርቲውን ቋሚ ኮሚቴዎች እንቅስቃሴ የገመገመ ሪፖርት ከመቅረቡም በላይ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች እንደ ግለሰብ ገምግሞ ደረጃ የተሰጠበት ሪፖርት በመነሻነት ቀርቦ ም/ቤቱ ውይይት ማድረጉ ተገልፆአል፡፡

ብሔራዊ ም/ቤቱ ከዚህ በፊት ለሥራ አስፈፃሚው በሰጠው መመሪያ መሠረት፤ ሥራ አስፈፃሚው ራሱን ገምግሞ የቀረበ ሲሆን ም/ቤቱ የእያንዳንዱን ቋሚ ኮሚቴ እንቅስቃሴና ሰብሳቢዎችን እንደ ግለሰብ ከገመገመ በኃላ ስለቀጣዩ የትግል አቅጣጫ መመሪያ መስጠቱ ተጠቁሟል፡፡” በማለት ተገልፆዋል፡፡ ግምገማው ከዚህ በፊት ከተለመደው ለየት ባለ ሁኔታ ጠንካራ እንደነበረ የም/ቤቱ አባላት ያስረዳሉ፡፡ “በአብዛኛው ፓርቲዎች የሥራ አስፈፃሚውም የማዕከላዊ ኮሚቴውም ሰብሳቢ የየፓርቲው ሊቀመናብርት ሲሆኑ ውይይቶቹም ብዙ ጠንካራና የተለያዩ ሐሳቦች የማይንሸራሸርበት ነው፤ ከፓርቲው ሊቀመንበርና ከሥራ አስፈፃሚው የተለየ ሐሳብና መከራከሪያ ነጥብ አግኝቶ ሐሳቡን በነፃ የሚገልፅ ግለሰብ ከተገኘ በጠላትነት ይፈረጃል” የሚሉት አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች “በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ይህ አሰራርና ፍረጃ የለም” ይላሉ፡፡

አስተያየት ሰጪዎቹ እንደሚሉት “የአንድነት ብሔራዊ ም/ቤት የራሱ ሰብሳቢና ፀሐፊ አለው፡፤ የፓርቲው ሊቀመንበርም ሆኑ የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚዎች እንደማንኛውም የብሔራዊ ም/ቤቱ አባል ተሰብስበው ሐሳባቸውን ያንሸራሽራሉ፡፡ የም/ቤቱን ውሳኔና መመሪያ ተቀብለው ይተገብራሉ፡፡ ማንኛውም የም/ቤቱ አባል ሐሳቡን ያለምንም መሸማቀቅ ሐሳቡን ማቅረብ ይችላል፡፡ ከቀረቡት ሐሳቦች ያሸነፈውና ተቀባይነት ያገኘውን ሐሳብ ተቀብሎ ይወጣል፡፡ ይህ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እጅግ ጠቃሚ ነው” ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በተያያዘ ዜና በሞት፣ በሥራ ዝውውርና በተለያየ ምክንያት በተጓደሉ የብሔራዊ ም/ቤቱ አባላት ምትክ ዘጠኝ አመራሮችን ተክቷል፡፡ ከተተኩት ውስጥ አምስቱ ተለዋጭ አባላት የነበሩ ሲሆኑ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ለብሔራዊ ም/ቤቱ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት አራቱ በቀጥታ ከአባላት ተመርጠው ብሔራዊ ም/ቤቱን ተቀላቅለዋል፡፡ ከአባላት በቀጥታ የተቀላቀሉት አቶ አበበ አከሉና አቶ ተስፋዬ ረታ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ለረጂም ዓመታት ፓርቲውን በድርጅት ጉዳይ ኃላፊነትና በም/ፕሬዝዳንትነት ሲመሩ ቆይተው ከ8 ወር በፊት በራሳቸው ውሳኔ ከመደበኛ አባልነት ውጭ ከብሔራዊ ም/ቤቱ ራሳቸውን አግልለው የቆዩት ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ወደ ብሔራዊ ም/ቤቱ ተመልሰዋል፡፡ ከምርጫው በኋላ አንዳንድ የፓርቲው አባላት ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት “ኢ/ር ግዛቸው ራሳቸውን ከአመራር በማግለላቸው ቅሬታ ተሰምቶን ነበር፡፡ ኢ/ር ለዚህ ፓርቲ ህለውና ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል፣ አሁን ወደ አመራሩ በመመለሳቸው ደስታ ተሰምቶናል፡፡ እሳቸውን ጨምሮ ሌሎች አባላት ወደ ም/ቤቱ የተቀላቀሉት ጠንካራ ታጋዮች ናቸው፡፡ ፓርቲው የበለጠ ጠንክሮ ይቀጥላል ብለን ተስፋ እናደርጋለን” በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

# ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ የመወዳደሪያ ምልክት ላለመውሰድ ወሰኑ

## - ለኢህአዴግ የድርድር ጥያቄ ሊቀርብ ነው

በ2005 ዓ.ም ለሚደረገው የአዲስ አበባ ከተማና የአካባቢ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ከፓርቲዎች ጋር ለመነጋገር በአዳማ ከተማ ምርጫ ቦርድ በጠራው ስብሰባ ፒቲሽን የተፈራረሙት የ34 ፓርቲዎች ህብረት ለየምርጫ ችግሮች ሳይፈቱ የመወዳደሪያ ምልክታቸውን እንደማይወስዱ በአንድ ድምጽ መወሰኑ ታወቀ፡፡

ፓርቲዎች ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ጽ/ቤት ባደረጉት ስብሰባ “በአንድ ድምጽ ወስነዋል” ተብሎአል፡፡

የዚህ የ34 ፓርቲዎች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑትን የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሐፊና የመድረክ ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ አስራት ጣሴ በጉዳዩ ዙሪያ ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡን መልስ “እውነት ነው፡፡ ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም መኢአድ ጽ/ቤት ፓርቲዎቹ ተሰብስበን ነበር፡፡ ያለፈውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ተነቦና መጠነኛ መሻሻል ተደርጐበት ፀድቋል፡፡ ሰነዱ የሁሉም ፓርቲዎች ሰነድ ሆኖ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ የኮሚቴው የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ 18 ነጥቦችን የያዘ ጥያቄ ለምርጫ ቦርድ መቅረቡን፤ ለአገር ውስጥና ለውጭ ሚዲያዎች ጋዜጣዊ መግለጫዎችንና ቃለ ምልልስ መደረጉን ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጐበት በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው ያከናወናቸው ተግባራት አድናቆትን አግኝቷል፡፡” ብለዋል፡፡

በመቀጠልም አስራት ሲናገሩ “ኮሚቴው ዕለት በዕለት ለሚያከናውነው ተግባር የገንዘብ ወጪ ያስፈልጋል፡፡ ለትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለስልክ፣ ለጽህፈት ሥራ፣ ከክልል ለሚመላለሱ የክልል ፓርቲዎች አባልና አንዳንድ ወጪ ስለሚያስፈልግ ለውይይት ቀርቦ ውይይት ተደርጐበታል፡፡ የወጪው አስፈላጊነት ታምኖበታል፡፡ ጥናት ተደርጐበት ፓርቲዎች እንደአቅማቸው የሚከፍሉበት ሁኔታ ተጠንቶ ለሚቀጥለው ስብሰባ እንዲቀርብ ስምምነት ላይ ተደርሷል” ብለዋል፡፡ በማያያዝም “የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፀሐፊ አቶ ነጋ ጠርተው አነጋግረውናል፡፡ ተፈራርማችሁ ባታመጡም ቦርዱ ፓርቲዎችን ለማወያየት እቅድ ይዞ ነበር፡፡ ይህንን ያህል ማጯጯህ ለምን አስፈለገ? የቦርዱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ከአገር ውጪ ስለአሉ ነው፡፡ ሲመጡ ያነጋራችኋል” ብለውናል፡፡ እኛ ደግሞ ምን እንደ ጮህን ነግረናቸዋል፡፡ በ2002 ዓ.ም የተደረገውን የዝርፊያ ምርጫ የተመለከተ ከዚህም በላይ ብዙ ማለት እንደሚቻል አስረድተናቸው ተመልሰናል” በማለት አብራርተዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ አስራት ሐሳባቸውን ሲያጠቃልሉ “ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገው ስብሰባ ከተነሱት አብይ ጉዳዮች አንዱ የቀረበው ጥያቄ ለምርጫ ቦርድ ብቻ ሳይሆን ለኢህአዴግም ይቅረብ የሚል ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ እስከሚታወቀው ድረስ ገለልተኛ አቅም ያለውና ፍቃደኛ ሆኖ ችግሮች ይፈታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ለሚቀጥለው ስብሰባ አንድ ሰንድ ተዘጋጅቶ ኢህአዴግ ከፓርቲዎች ጋር እንዲደራደር ጥሪ ይቅረብለት የሚል ሐሳብ ቀርቦ በአንድ ድምጽ ፀድቋል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት ኮሚቴው የመደራደሪያ ሰነዱን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ኢህአዴግም ኃላፊነት ተሰምቶት ከፓርቲዎች ጋር ይነጋገራል ብለን እናምናለን፡፡” ካሉ በኃላ “ፓርቲዎቹ በአገራን ባልተለመደ ሁኔታ በአዲስ ምዕራፍና በአዲስ የፖለቲካ ባህል በመከባበር፣ በመደማመጥ፣ በመተማመንና በመግባባት በመስራት ላይ ናቸው” ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት “ምርጫ ቦርድና ኢህአዴግ የፓርቲዎችን ህብረት ለማፍረስ ቀንና ሌሊት እየሰሩ ናቸው፡፡” ሲሉ ይናገራሉ፡፡ አስተያየት ሰጪዎች እንደሚሉት “ኢህአዴግ የፓርቲ አመራሮችን እየነጣጠለ ማስፈራራትና ለመከፋፈል አመራሮቹ በመካከላቸው አለመግባባት እንዲፈጠር እየሰራ ሲሆን፤ ምርጫ ቦርድ በበኩሉ እንዲሁ አንዳንድ የፓርቲ አመራሮችን በተናጥል እየጠራ አመራሩን ለመከፋፈልና የተለያዩ ደብዳቤዎችን በማዘጋጀትና በመበተን ፓርቲዎችን ለማሸማቀቅና ከጥያቄያቸው እንዲቆጠቡ እያደረገ ይገኛል፡፡” ሲሉ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

# ኢህአዴግና የምርጫ ዋዜማ ጉራማይሌ ትዕይንቶች

ቀለሙ ሁነኛው

kelemhun@yahoo.com

የኢህአዴግ ሹሞች ነጋ ጠባ አታሞ የሚደልቁላት አዲስ አበባ በምርጫ ዋዜማ ላይ ትገኛለች፡፡ በ1997 ዓ.ም በቅንጅት ፍቅር የከነፈው የአዲስ አበባ ህዝብ ኢህአዴግን በምርጫ ካርዱ በዝረራ ከጣለው በኋላ በተከሰተው ውዝግብ የከተማዋ የምርጫ ፕሮግራም ከአገር አቀፍ ምርጫ ጋር መለያየቱ ይታወቃል፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ 2005 ዓ.ም ምርጫ የአዲስ አበባን ሕዝብ ሊፈትን ወራት ቀርተውታል፡፡

በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሞት ማግስት የሚካሄደው ይህ ምርጫ ለኢህአዴግም ሆነ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ብርቱ ፈተና ሊሆን እንደሚችል አይጠረጠርም፡፡ በተለይም በአቶ መለስ ሞት ማግስት የኢህአዴግ የ"ቁጩ" ዲሞክራሲና የሕልውናው ቀጣይነት ጉዳይ በእሳት የሚፈተንበት ትዕይንት ሊከሰት ይችላል፡፡

በምርጫ 97 ሽንፈት መሠረቱ የተናጋው ኢህአዴግ የዲሞክራሲን አንገት መቅሊያ ጎራዴውን ከማህደሩ መዝዞ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በመከታተፍና የሕዝብን ድምጽ በመዝረፍ በ2002 ዓ.ም 99.6% የፓርላማ ወንበርን ተቆጣጥሮ "አውራ ፓርቲ" መሆኑን ቢለፍፍም ሕዝቡ ግን እንደ "ውራ"(ውዳቂ) ፓርቲ ነው የሚያየው፡፡ ህዝቡ በገዢው ፓርቲ ላይ የነበረው የቀድሞው ጥላቻ ይበልጥ እየጨመረ መጥቷል፡፡

በምርጫ ዋዜማ ኢህአዴግ እንደ እስስት መልኩን መቀያየር ልማዱ ነው፡፡ አመለ ሸጋ መሆን ይዳዳዋል፡፡ "የአዛኝ ቅቤ አንጓች" እንዲሉ በህዝብ ፊት ሩህሩህ ለመምሰል ይሞክራል፡፡ ይህንን ብልጣ ብልጥነቱን ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ለምርጫ ቅስቀሳ በየጉራንጉሩ የሚላኩትን ካድሬዎቹን "ምርጫ ሲደርስ ከእግራችን ስር መነጠፍ ይቃጣችኋል፡፡ ጉብ ቂጥ ትላላችሁ፡፡ እንደ ጉም የማይጨበጥ ባዶ ተስፋ ሰንቃችሁ፣ እንደ ልክስክስ ውሻ ነጋ ጠባ ከመንደራችን አትጠፉም፡፡ በጮሌነታችሁ ያታለላችሁትን ጥቂት የህዝብ ድምፅ በመቶ እጥፍ እያበዛችሁ `አሸነፍን` ትሉና በምርጫ ማግስት የጭቃ ጅራፋችሁን ትሰነዝሩላችሁ፡፡ ያ የቀድሞው አጋንንት ተመልሶ በእጥፍ ይሰፍርባችኋል . . ." ሲል ሲያንጓጥጣቸው መስማት በየ 5 አመቱ የሚከሰት ጉራማይሌ ትዕይንት ነው፡፡

የአዲስ አበባ ምርጫ ኢህአዴግን ክፉኛ ያሳስበዋል፡፡ የምርጫው ውጤት የኢህአዴግን በሕልውናው የመቀጠል ያለመቀጠል ጉዳይ ላይ ብርቱ ተፅዕኖን ማሳረፍ የሚችል ነው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫው የ1997 ዓ.ም ምርጫ ውጤት ያስከተለው መዘዝ በኢህአዴግ ዝክረ ታሪክ ውስጥ ብርቱ ጠባሳን ጥሎ ያለፈ መሆኑ ነው፡፡

ኢህአዴግ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ፍፁም አምባገነን ሆኖ ብቅ ማለቱ ከህዝቡ የተሰወረ አይደለም፡፡ በምርጫ 97 ማግስት በኢህአዴግ የበቀል እርምጃ እና በውስጣቸው በተፈጠረ ሽኩቻ የተፍረከረኩት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሕዝብ ዘንድ አመኔታን ያጡበት ወቅት በመሆኑ ለ2002 ዓ.ም ምርጫ አንዳችም ጉልበት አልነበራቸውም፡፡ ኢህአዴግም የማጭበርበሪያ ጭምብሉን አጥልቆ የምርጫው መም ላይ ያለ ተፎካካሪ ሮጦ ማሸነፍ ቢችልም በሕዝብ ልብ ውስጥ ከቶም መግባት አልቻለም፡፡ ዛሬም ቢሆን ሕዝብን የሚያስተዳድረው በፍቅር ሳይሆን በታንክና በመድፍ እያስፈራራ ነው፡፡ ፓርቲው አቶ መለስ ቀጥቅጠው በሰሩት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርከብ ላይ ተሳፍሮ የህዝብ ማዕበል አንድ ቀን በሚያናወጠው ባህር ላይ መንሳፈፉን ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ፓርቲው ከፊቱ ብርቱ ጋሬጣ ሲደቀን እንደ መርከብ ካፒቴን አቅጣጫውን ለማስቀየር እኩይም ይሁን ሰናይ ሀሳብ ሰንቀው ብቅ የሚሉት አቶ መለስ ዛሬ ከኢህአዴግ ጋር የሉም፡፡ ላለፉት 21 ዓመታት ሁሉን ነገር አቶ መለስ ጫንቃ ላይ ጥለው የራሳቸውን ሕይወት ሲያደላድሉ የነበሩት ሹማምንት በሰውዬው ድንገተኛ ሞት በብርቱ ተሸብረዋል፡፡ "የመለስ ራዕይ፣ የመለስ ሌጋሲ" እያሉ የሙት መንፈሳቸውን (ghost sprit) ለመጥራት ቢሞክሩም ዛሬ ትናንትን መሆን አይችልም፡፡ ሞትን በትንሳኤ ድል ነስቶ አለምን እየገዛ የሚገኘው የክርስቶስ ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነው፡፡ ኢህአዴጎች ምንም ያክል ቢመኙ የአቶ መለስ ሙት መንፈስ መለኮታዊነት ሊላበስ አይችልም፡፡

> በአምሳሉ የቀረፀው ምርጫ ቦርድ ሌላኛው የኢህአዴግ "አጋር ድርጅት" ነው፡፡ በገዢው ፓርቲ ታማኞችና አጎብዳጅ ሎሌዎች የተደራጀ በመሆኑ ፍፁም ገለልተኛ አለመሆኑን የማይገነዘብ ዜጋ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ኢህአዴግ ስልጣን ላይ እያለ ነፃና ገለልተኛ ምርጫ በኢትዮጵያ ይካሄዳል ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው፡፡

በአዲስ አበባ የ2005 ምርጫ ኢህአዴግ በአቶ መለስ የሙት መንፈስ ሕዝብን ለማማለል የመጠቀሙ ጉዳይ ጥርጥር የለውም፡፡ "የህዳሴው መሀንዲስ፣ ያልሞተው ጀግና መሪ፣ ለዘላለም የሚታወስ የክፍለ ዘመናችን ድንቅ መሪ" በሚሉ ቃላት የተንቆጠቆጡ ቅስቀሳዎች በቅርቡ ዳግም የአዲስ አበባን አድባር እንደሚያናውጣት ይታወቃል፡፡ አስከሬናቸውን በድብቅ ለ35 ቀናት ቤልጂየም ብራስልስ በሚገኘው የሴንት ሉዊስ ሆስፒታል አቆይተው፤ ለ13 ቀናት ደግሞ 21 ዓመታት በነገሱበት የ4 ኪሎው ቤተመንግስት በአደባባይ አጋድመው ቀጣይ እድሜያቸውን ለማራዘም ሌት ተቀን የሞኙ ሩጫ የተሯሯጡት ሹማምንት ዛሬም ለምርጫው ቅስቀሳ የመለስን ስም ከመጠቀም የሚያግዳቸው አንዳችም ሀይል አይኖርም፡፡

ምርጫ በመጣ ቁጥር የማይገመጥ የተስፋ ዳቦ የሚያድለው ኢህአዴግ ለ2005ቱ የአዲስ አበባና ለአካባቢ ምርጫ የቀድሞ የቅስቀሳ ዘዴዎቹ ከቶም አያዛልቁትም፡፡ ቀደም ሲል ምርጫ ሲቃረብ የአብዛኛውን አዲስ አበቤ ልብ የሚያንጠለጥለው ከመኖሪያ ቤት ጋር በተያየዘ ህገወጥ ግንባታዎችን ሕጋዊ ለማድረግ ቃል በመግባት ነበር፡፡ "የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰጣችሁና ሕጋዊ ትሆናላችሁ" የሚል የማይጨበጥ ጉም፡፡ ምርጫውን "አሸነፍኩ" በተባለ ማግስት ግን ለመራጩ ህዝብ የተገባው የተስፋ ቃል በአደባባይ ይሰረዝና ነዋሪውን ከቀዬው ማፈናቀል ይጀመራል፡፡

የዘንድሮው ግን ትንሽ ለየት ይላል፡፡ አሁን እየተተገበሩ ያሉትን ሁኔታዎች ስንመለከት ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ምርጫ እንደማያሸንፍ ከወዲሁ ያረጋገጠ ይመስላል፡፡ በእርግጥም በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ አይችልም፣ ያሸነፈበትም ጊዜ የለም፡፡ በአቶ መለስ የሙት መንፈስ የሚደረገው የምርጫ ቅስቀሳም ወንዝ አያሻግረውም፡፡ ሕዝቡንም በሚሻር ቃል ኪዳን ማታለሉ ያረጀ "እርድና" ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ብቸኛው አማራጭ ቀድሞ የተካነበትን የድምፅ መስጫ ኮሮጆዎችን ቀድሞ በተጭበረበረ ካርድ መሙላትና ድርጅታዊ ሥራ በመስራት የድምፅ ቆጠራውን በራሱ ካድሬዎች ማስወረር ላይ ማተኮር ይሆናል፡፡ ለዚህም ይመስላል ከአቶ መለስ አስከሬን ሥርዓተ ቀብር ማግስት በአዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተሞች "ህገ ወጥ ግንባታ" በሚል በዶዘር ሳይቀር የድሃውን ህዝብ ቤት ማፍረስ የተያያዘው፡፡ ነዋሪው የሚቹን ጠቅላይ ሚ/ር ፎቶ ግራፍ ይዞ በመውጣት "የአቶ መለስ አይን ሳይፈስ ቤታችንን አታፍርሱ! . . ." ቢልም ሰሚ ባለማግኘቱ የሀይል እርምጃ ለመውሰድ ተገድዶ እንደነበር የቅርብ ሳምንታት ትዝታዎቻችን ነው፡፡ ለወትሮው ምርጫ ሲቃረብ እንደ እስስት መልኩን የሚቀያየረው ኢህአዴግ ህዝብን ክፉኛ መድፈር እንደለመደው በታንኩና በመድፉ መተማመኑን በገሀድ የሚመሰክር ነው፡፡

በአምሳሉ የቀረፀው ምርጫ ቦርድ ሌላኛው የኢህአዴግ "አጋር ድርጅት" ነው፡፡ በገዢው ፓርቲ ታማኞችና አጎብዳጅ ሎሌዎች የተደራጀ በመሆኑ ፍፁም ገለልተኛ አለመሆኑን የማይገነዘብ ዜጋ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ኢህአዴግ ስልጣን ላይ እያለ ነፃና ገለልተኛ ምርጫ በኢትዮጵያ ይካሄዳል ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው፡፡

በሌላ በኩል ኢህአዴግ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በሰበብ አስባቡ እየወነጀለ አባላትና ደጋፊ እንዳይኖራቸው የሚያደርስባቸው ወከባ እጅግ እያየለ መጥቷል፡፡ ፓርቲዎቹ ወደ ህዝቡ ወርደው የሰነቁትን ራዕይና ግብ እንዳያሳውቁ የሚፈጥራቸው ጋሬጣዎች እየበዙ ነው፡፡ ገንዘብ ከፍለው የሆቴሎችን አዳራሽ በመጠቀም ከህዝብ ጋር እንዳይወያዩ በምስጢር ያሰማራቸው ደህንነቶች ባለሃብቶቹን ያስፈራራሉ፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው የኢህአዴግ ብቸኛ መሣሪያ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከኢህአዴግ "የአድገናል፣ ተመንድገናል" በሬ ወለደ ሀተታ ውጭ አይዘገብባቸውም፡፡ ከፍትህ ጋዜጣ ሥርዓተ ቀብር በኋላ በኢትዮጵያ የነፃው ፕሬስ ህልውና አክትሞለታል ማለት ይቻላል፡፡ መንግስትን በጋዜጣ መተቸት ፈጣሪን የመገዳደር ያህል እየተቆጠረ መጥቷል፡፡

የመድረክ አባል የሆነው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ከሐምሌ 2003 ዓ.ም ጀምሮ በራሱ ልሳን (ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ) ወደ ህዝብ መድረስ ቢችልም ጋዜጣዋ ከህትመት ውጭ እንድትሆን ተደርጓል፡፡ አሁን ባላት ቅርፅ ብልጭ ድርግም እያለች ብትወጣም ኢህአዴግ በገፍ ካሰማራቸው የደህንነት አባላት ጋር ድብብቆሽ በመጫወት ነው፡፡

ኢህአዴግ እንዳለፉት ምርጫዎች በአገሪቱ የሚገኙ ሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ ታቦት እያጀቡት ቤተ መንግስት እንዲያስገቡት ይፈልጋል፡፡ ምርጫ በመጣ ቁጥር የትግሉ መስመር ላይ ለመሰለፍ የማያፍሩ አንዳንድ "ወፍ ዘራሽ" ፓርቲዎች ከጌታቸው ከኢህአዴግ የሚወረወርላቸውን ትርፍራፊ ለመልቀም ውር ውር ማለት ይጀምራሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ለገዢው ፓርቲ ጥሩ ጭምብል ነው፡፡ የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፊ መሆኑን ለመስበክ ይመቸዋል፡፡

የሰሞኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች (መድረክን ጨምሮ) ምርጫው ላይ ላለመሳተፍ በጀመሩት መንገድ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ከምርጫ ፕሮግራም ቅስቀሳ በፊት ከገዢው ፓርቲ ጋር ፊት ለፊት ተነጋግረው መተማመን ላይ የሚደርስባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በውል ተለይተው ህዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተለይም የመድረክ አባል የሆነው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ይህን የምርጫ ወቅት እንደ ጥሩ አጋጣሚ መጠቀም አለበት፡፡ በግፍ የታሰሩት የፓርቲው አመራሮችና አባላት እንዲፈቱ መታገሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመላ አገሪቱ በፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚደረገው ወከባና እንግልት የሚቆምበትን ሁኔታ ከኢህአዴግ ጋር መደራደርም ያስፈልጋል፡፡ ፓርቲው ከብዙ ፍትጊያና ውጣ ውረድ በኋላ በሁለት እግሩ ቆሞ ድምፁን ለህዝብ የሚያሰማበት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሕትመት እንዲፈቀድ ኢህአዴግን ማስገደጃ ሰዓቱ አሁን ነው፡፡ በኢህአዴግ ክርን እየተደቆሱ በምርጫ እሱን ለማጀብ የሚሹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለአፍታ ቆም ብለው ራሳቸውን ቢፈትሹ ይበጃል፡፡ ኢህአዴግ ያለ አንዳች ተቀናቃኝ ብቻውን እንዲወዳደር ማድረጉ ግዙፍ ፖለቲካዊ ትርፍ ይኖረዋል፡፡ እንደ ቀበሮ ባህታዊ ለፈረንጆቹ ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል ተኳኩሎ መቅረብን የሚወደውን ኢህአዴግ እንደ ብቅል ፀሐይ ላይ ማስጣት፣ ገመናውን ገልጦ ማሳየት በሕዝብ ዘንድ የሚያስገኘው ጠቀሜታ በምርጫው ከመሳተፍ በላይ ነው፡፡

# የ21ኛው ክፍለ ዘመን ገናና ሠላማዊ የተቋውሞ ሂደት

**ካሊድ ሃምዛ - ከአዲስ አበባ**

ይህች ዓለማችን ከተፈጠረችበት ማግስት ጀምሮ በየክፍለ ዘመናቱ በርካታ ጨቋኝ መንግስታትና ግለሰቦችን አስተናግዳለች፡፡ እነኚህ ጨቋኝ መንግስታትና ግለሰቦች የበርካቶችን ህይወት ፣ አካል እንዲሁም ስነ-ልቦናላይ ታላቅ ጉዳት አድርሰዋል ፡፡ እነኚህን ጨቋን መንግስታትንና ግለሰቦችን ለማስወገድ ተጨቋኞች በርሃ ለበርሃ ተንከራትተዋል ፣ በገዛ ሀገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ ታይተዋል ፣ ሳይወዱ በግዳቸው ስርዓቱን ለመገርሰስ ጠምንጃ መዘዋል ፣ህይወታቸውን ገብረዋል ፣ ለእስራትም ተጋልጠዋል ሌሎችንም ስቃዮች አሳልፈዋል ፡፡ አንዳንድ ተጨቋኞች ግን ስቃዩ እያንገበገባቸው ለዜጎቻቸው በማሰብ ፣ ለሃገርም በመቆርቆር ሰለማዊ የትግል ሂደትን በመምረጥ ጨቋኞችን ዘርረዋል፣ ለጥያቄያቸውም ተገቢውን መልስ አግኝተዋል ፡፡ በሰላማዊ የተቋውሞ ሰልታቸው ከሚጠቀሱት የተጨቋኞች መሪ መካከል የህንዶቹ ማህተማ ጋንዲና የደቡብ አፍሪካውያን አባት የሆኑት ኔልሰን ማንዴላ ይጠቀሳሉ ፡፡ የአፓርታይድ ስርአት አራማጅ የነበሩት ነጮች በማን አለብኝነት የጥቁሮችን መሬት በመዝረፍ ጥቁሮችን በገዛ መሬታቸው ባሪያና ባይተዋር አድርገዋቸዋል፡፡ ደቡብ አፍሪካውያን ጥቁሮች እስከ ተወሰነ የትምህርት ክፍል ካልሆነ መማር አይፈቀድላቸውም፣ ከነጮቹ ጋር አይገበያዩም ፣ በገዛ ሀገራቸው ያለፍቃድ መተላለፍ አይችሉም፣ ሌሎችም በርካታ ኢ-ሰብዓዊ የሙብት ጥሰቶች ይደርሱባቸው ነበር፡፡ ይህንንም ስርዓት የተቃወሙ በገፍ ታስረዋል ፡፡ እንደ አውሮፓውያኖቹ አቆጣጠር በ1952 ወርሃ የካቲት ይህ የግፍ ስርዓት መቆም አለበት በማለት በፊትአውራሪው ኔልሰን ማንዴላ አማካኝነት ሰላማዊ የሆነ ተቋውሞ ማሰማት ችለው ነበር ይሁንና በአስተሳሰብ የተበለጠው ቀኝ ገዢ ፊትአውራሪውን ኔንሰን ማንዴላን ጨምሮ በሰላማዊው ተቋውሞ የተሳተፉ 8500 ሰዎችን ወደ ዘብጥያ አውርዷዋል ፡፡ ፊታውራሪው ሌንሰንም ማንዴላም ሆኑ ማህተማ ጋንዲ ቋኞቻቸውን የማታ የማታ አሸንፈዋል ዝንተ ዓለምም በሰላማዊ የተዋውሞ ታሪካቸው ሲዘከሩ ይቆያሉ ፡፡ የዛሬው ፁሁፌ ስለ ኔንሰን ማንዴላም ሆነ ስለ ማህተመ ጋንዲ ሰላማዊ የተቋውሞ ሂደት ለመተረክ ሳይሆን በይፋ ከጥር 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በሰላማዊ የትግል ስርዓት ውስጥ እየተሸጋጋረ ስላለው የኢትዮጲያ ሙስሊሞች የተቀዋውሞ ሂደት ነው ፡፡

## ሰላማዊ የተቋውሞ ሂደት በአወሊያ

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አግንበው ለተነሷቸው 3 መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ማለትም

1. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) አመራሮች በሙሉ የህዝበ ሙስሊሙ ውክልና የሌላቸው በመሆኑ በህዝበ ሙስሊሙ ነፃነት በሚመረጡ አመራሮች ይተኩልን
2. በመጂሊስ አማካኝነት በኢትዮጲያ ሙስሊሞች ላይ በግድ እየተጫነ ያለው የአህባሽን አስተሳሰብ የማጥመቅ ዘመቻ ይቁምልን
3. አወሊያ የህዝበ ሙስሊሙ ነፃ ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል መጅሊስ እጁን ያንሳ

ለሚሉት ግልፅና ሃይማኖታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ማዕከል በመሆን መንግስት በይፋ ይህንን ተቋም ሀምሌ 6/2004 ዓ.ም እስከ አጠቃበት ቀን ድረስ ምዕመናን በማሰባሰብ በመፍትሄ አፈላላጊው ኮሚቴ በኩል በተደረገው ትግል የትኩረት አቅጣጫዎች ማዕከል ነበር- አወሊያ ፡፡ የካቲት 26/2004 ዓ.ም በፊት "ጥያቄችሁ ግልፅና ተቋማዊ ነው፡፡ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡" በማለት የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲናገር ቢከርምም፣ የካቲት 26/2004 ዓ.ም በኋላ ምክንያቱ በቅጡ ባላልታወቀ ሁኔታ ይህንን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ በአሸባሪነትና በፅንፈኝነት ፈረጀው፡፡ ትግሉን የፅንፈኞች ፣ሸሪዓዊ መንግስት ለማቋቋም የሚጥሩ በማለት ሰይመውታል ፡፡ ከጥር 2004 - ጀምሮ እስከ ሐምሌ 06/2004 ዓ.ም በተደረገው የአወሊያ ተቋውሞ በርካቶች ተሳትፈዋል ፡፡ ሚያዝያ 12/2004 ዓ.ም በተደረገው ተቋውሞ ከአንድ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ተገኝቷል ፡፡ እነዚህ የተቋውሞ ሂደቶች ያለ አንዳች ዕክል ጠጠር እንኳን ሳይወረወር በሰላም ተጠናቅቀዋል ፡፡ ይህ ሳምንታዊ የተቋውሞ ሂደት በሚደረግበት ወቅት ሀገራችን የምታስናግደው ዓለም አቀፍ ስብሰባ በሚኖርበት ጊዜ የሚዘለልበት አጋጣሚ ነበር ፡፡ ምናልባት ወደ አወሊያ የሚመጣው የፖሊስ ሃይል ወደ ፕሮግራሙ ያቅና በሚል እሳቤ ፤ ነገሩ ቢመጣም እንኳን ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ከመታዘብ ውጪ ቢዚ የሚያደርገው ስራ አያጋጥመውም ነበር ፡፡ ከ አንድ ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ መመሪያውን ሲሠጡ የነበሩ ድንቅ የሰላም አንባሳደሮች ከቶ በምን ምክንያት ነው የአፍሪካ አንድነት ስብሰባን ለመደናቀፍ ሞክረዋል የሚባለው ፡፡ እስቲ የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረድ አንድ ከከተማ መውጫ አካባቢ ላይ የሚከናወን የተቋውሞ ሂደት ብሎም የአፍሪካ አንድነት ስብሰባ ከሚከናወንበት ቀን ቀድሞ የነበረ በምን ምክንያት ነው ስብሰባውን ሊያደናቅፍ የሚችለው? በጊዜው ግን የህዝበ ሙስሊሙ መፍትሄ አፈላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ አብበከር አህመድ እንዲህ ሲሉ ተናግረው ነበር << ሃገራችን ኢትዮጵያ ከነገው ቀን ጀምሮ የአፍሪካ አንድነት ስብሰባን ታስተናግዳለች እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ይህ ስብሰባ በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ እንሻለን>> ፡፡ አወሊያ ላይ ሲደረግ የነበረው ተቋውሞ ፍፁም ሰላማዊ የነበረና መሪዎችም ጭቆናው ቢበዛ እንኳን ትግሉ ሰላማዊ እንዲሆን አበክረው የሰበኩበት ነው ፡፡

## ሰላማዊ የትግል ሂደት በአንዋር መስጂድ

ሐምሌ 06/2004 ዓ.ም በይፋ የአወሊያ ተቋውሞ ከተቋረጠበት በኋላ የአንዋር መስጂድ በርካታ ሰዎችን ያሳተፈ ሰላማዊ የትግል ጉዞን አሳይቷል እያሳየም ይገኛል ፡፡ የህዝበ መስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ከመታሰራቸው ከ ሰባት ቀን አስቀድሞ ህዝበ ሙስሊሙን በማናቸውም አይነት መንገድ ሰላማዊ የተቋውሞ ሂደትን እንዲከተል ቃል ያስገቡበት ቦታም ነው ፡፡ የአንዋር መስጂድ ህዝበ ሙስሊሙ ሰላማዊ መሆኑን የሚያሳየው የነጩ ምልክት ተቃውሞ ያስተናገደ ብሎም የህዝብ ድምፅ አለመስማት አደጋ እንዳለው የቢጫ ምልክትን ለገዢው ፓርቲ ያመላከተበት እንዲሁም እጆች ታስረዋል ፣ የዝምታ ተቋውሞ ፣ የድምፅ ተቋውሞ ፣ የታሰሩት ኮሜቴዎች ንፅሃውያን ዜጎች መሆናቸውን ዳግም በታየው የነጩ ባንዲራ ተቋውሞ ያስተናገደ የተቋውሞ ቦታ ነው ፡፡ ሰላማዊ የተቋውሞው በተቀሩት የአዲስ አባባ መስጂዶች እንዲሁም በክፍለ ሀገራት ተከናውኗል፡፡ ለምሳሌ በደሴ ፣ በከሚሴ ፣ በሃረር ፣ በድሬዳዋ ፣ በአፋር፣ በወሊሶ ፣ በወልቂጤ፣ በሻሸመኔ ፣በጂማ፣ በአዳማ፣በኮንቦልቻ፣በደጋን ፣ በገርባ ፣ በጎንደር ፣በወራቤ ፣ በዲላ ፣ በሌሎች ከተሞችም ብሎም በሰሜን አማሪካ ግዛት ውስጥ ባሉት ስቴቶች ኦሃዩ ፣ ዲሲ ፣ ቨርጂኒያ ፣ሲያትል፤ በአፍሪካ ግብፅ እና ሱዳን እንዲሁም በኤሲያ በሳውዲ አረቢያና በዱባይ ሰላማዊ የሆኑ ድምጾች ተሰምተዋል ፡፡

## በሁለቱ ክብረበዓሎች የታየው ሰላማዊ የትግል ሂደት

በሁለቱም ክብረ በዓሎች በመላ ሀገሪቱ ቁጥሩ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ በሰላማዊ መንገድ ተቋውሞውን አሰምቱዋል ፡፡ የኢድአል - ፈጥሩ በነጩ ባንዲራ የተሸጎጠጎጠ ሲሆን ፡፡ የኢድአል - አድሃው ቢጫው ባንዲራ አንግቦ የህዝብ ድምፅ አለመስማት አደጋ እንዳለው ለገዢው ፓርቲ ማሳሰቢያ ሰጥቶበታል ፡፡ ኮሚቴው ይፈታ ፣ ምርጫው ህገወጥ ፣ ምርጫው የካድሬ ፣ ምርጫው የአህባሽ ፣ አሸባሪ አይደለንም ፣ የታሰሩት ይፈቱ ፣ ዳግም ምርጫ በመስጂዳችን፣ የኢትዮጲያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ ህንፃ ላይ ኢትቪ ውሸታም ኢቲቪ ሌባ የሚሉት ከተንፀባረቁት ህብረ ዝማሬዎች መካከል ከፊሎቹ ነበሩ ፡፡ ገዢው ፓርቲ በህዝቡ ገንዘብ ከውጭ በማምጣት እዚህ የሚገጣሙትን የቢሾፍቱ ባሶችን ደርድሮ ሰላማዊ ተቋውሞውን ወደ ሁከት ለመቀልበስ ቢጥርም በህብረ ዝማሬ ተቃዋሚው << ባስ አልሰብርም... >> << ባስ አንሰብርም... >> << ባስ አንሰብርም ... >> ብሎ አሳልፎታል ሹፌሮችም አመስግነዋል ፡፡

## በገዢው ፓርቲ ለሰላም ወዳዱ ሙስሊም የተሰጠው ምላሽ

በሰላማዊነቱና የጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን ሲመሰከርለት የነበረው የህዝበ መስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ በሽብርተኝነት ተጠርጥሮ ለእስር ተዳርጉዋል ፡፡ በማዕከላዊና አሁን በቃሊቲ ያለአግባብ እስሩን እያስተናገደ ይገኛል ፡፡ በቃሊቲ እስር ቤት ከሁለት ዓመት በላይ የታሰሩት ስዊድናውያኖቹ የሃን ፐርሽንና ማርቲን ሺብዬን ስለ እስር ቤቱ እንዲህ ብለዋል << ይህ እስር ቤት ምርኮኛ እንጂ የአንድ የሃገሪቱ ዜጋ ወይንም የህግ ታራሚ የሚገባበት ቦታ አይመስልም ቁንጫው ፣ አይጡ ፣ የንፅህና ጉድለቱ አረ ምኑ ቅጡ ... ሁሉ ነገሩ ለዜጋ የሚገባ እስር ቤት አያስመስለውም ... >> ፡፡ ከቶ በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ታይቶ ለማይታወቅ እንደዚህ አይነቱ ሰላማዊ የትግልና የተቋውሞ ሂደት የሚገባው ይህ ነው ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍርድ ማሰሪያን በቴሌቪዥን እንጂ በአይኑ በብረቱ አይቶ የማያውቅ አንድ ግለሰብ እንዴት በሽብርተኝነት ይጠረጠራል ፡፡ ለኔ ይህ አዋጅ ምስኪኑን የኢትዮጵያ ህዝብ በምንም አይነት መልኩ የማይመለከተው ነው ፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ በሚመሩት ድንቅ ኮሚቴዎች አማካኝነት ከሃይል ይልቅ መንግስትን በመማፀን ፣ ነጭ ባንዲራ በማውለብለብ ፣ የድምፅ ተቋውሞ ሲገፋ የዝምታ ተቋውሞን በመምረጥ ፣ሺዎች ተንበርክከው እያለቀሱ፣ እጆቻቸው ታስረዋል የሚሉ መልክቶችን እያስተላለፉ በየሳምንቱ ተቋውሞ ያሰሙ ንፁሃውያን ዜጎች ለእስራት ፣ለእንግልት፣ለሞት ተጋልጠዋል ፡፡ መንግስት በሃይማኖቱ ላይ በግልፅ ጣልቃ በመግባት የልማት ሥራዎችን መስራት ሲገባው የልማት ስራዎችን አሸንቀንጥሮ በመጣል ምርጫን በቀበሌ በማከናወን ህዝበ ሙስሊሙን የማይወክል ሰው፣ የህዝበ ሙስሊሙን ይሁንታ ያላገኘ ሰውን በመሪነት ላይ አስቀምጧል ፡፡ በኢቲቪ ፣ በኤፍ.ኤም 98.1 እንዲሁም በ ዛሚ ኤፍ.ኤም የሙስሊሙን ጥያቄ የመገልበጥ ብሎም ሰላማዊ የሆኑት ኮሚቴዎች የመተቸትና የመዝለፍ ተግባር ተፈፅሟል አሁንም እየተፈጸመ ይገኛል፡፡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፣ በፓርቲው መፅሔት አዲስ ራዕይ ጥያቄውን የመገልበጥና ወደ ሌላ አጀንዳ የማዞር ሂደት ተስተውሏል በአሳሳ፣ በገርባ እንዲሁም በደጋን ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ህይወት ጠፍቱዋል፡፡ በአጠቃላይ ጥያቄውን ባቀረቡ ወንዶች፣ሴቶች፣አረጋውያን ላይ ጉዳት እንግልትና እስራት ደርሷል፣ መስጂዶች ተደፍረዋል፣ ለሙስሊሙ ህብረተሰብ መረጃ የሚያደርሱ ጋዜጦችና መፅሄቶች ከታገዱ ወራትን አስቆጥረዋል፣ የሙስሊሙን ጥያቄ ሲዘግቡ የነበሩ ጋዜጠኞች ለስደት ተጋልጠዋል ፡፡ ሌሎችም ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ተፈፅመዋል ፡፡ የኋላ ኋላም መንግስት እየፈጠረ ባለው የሙብት ጥሰት በሰላማዊ የትግል ሂደት ውስጥ ግልፅ የነበሩት ሦስቱ ጥያቄዎች ሁለት ተጨምሮውባቸው ወደ አምስት አድገዋል ፡፡

1. በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ንፁህን ኮሜቴዎችና አላግባብ የታሰሩ ንፁህን ዜጎች ይፈቱ
2. በአሰሳ፣በገርባእንዲሁምበደጋንሰላማዊየሆኑዜጎችንህይወት የቀጠፉት የመንግሰት አካላት ለፍርድ ይቅረቡ የሚሉ ናቸው ፡፡

ጽሁፌን የምቋጨው ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም በጥባጭ ካለ ውሃ አይጠራም በሚለው የኢዲስ ታይምስ ቁጥር 7 ፅሁፋቸው ነው ፡፡ << ህጋዊ መብትን በግልም ሆነ በህብረት መጠየቅ ሽብርተኛ አያደርግም ፤ ሽብርተኛ የሚያደርገው መብታቸውን የሚጠይቁትን መግደል፣መደብደብና ማሰር ነው ፤ ዓለማዊውን ስርዓት የማይነካውን ፣ከአምላኬ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የመረጥኩትን መንገድ አክብሩልኝ ፤በሌላ መንገድ ወደ አምላኬ እንድሄድ አታስገድዱኝ ማለት ሽብርተኝነት አይደለም፤ ሽብርተኝነት የሚሆነው በሰዎች ላይ ባዕድ የሚሉትን ዕምነት መጫን ነው ፤ ሽብርተኝነት የሚሆነው አትጫኑብኝ እያለ በሰላማዊ መንገድ የሚጮኸውን ሰው መደብደብ ፣ማሰርና መግደል ነው ፤ ሽብርተኝነት የሚሆነው የሰዎችን ቅዱስ ቦታ በጥይትና በደም ማርከስ ነው ሽብርተኝነት የሚገለጠው ሰላሜን ጠብቁልኝ እያለ በሚጮኸው ሰው ሳይሆን ጉልበቱን ብቻ ተማምኖ ሰላምን በሚያደፈርሰው ነው ፡፡>>

የነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ያስጠለለቻውን
ኢትዮጵያ አላህ (ሱ.ወ) ሰላምዋን ይስጣት !!!
ድል ለተጨቆኑት ኢትዮጵያውያን ሁሉ !!!



ፍኖተ ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ፍኖተ ነፃነት ህዳር 18 ቀን 2005

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 63 | ዋጋው፡- 6 ብር